**የጥናቱ አጠቃላይ መግቢያ**

በቤተ ክርስቲያናችን እንደ ሚታወቀው ልዩ ልዩ ዓይነት ጥናቶች የሚዘጋጁ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ አንዳንዶች የቅዱሳን የመጽሐፍት ጥናት(textual)፣ የቅዱሳን ህይወት ጥናት(authobiographical)፣ በወቅታዊ ነገሮች ላይ ያተኮረ የርዕስ ጥናቶች (topical) እና ሌሎችም ዓይነቶች ናቸው።

በዚህ መሠረት ይህ በርዕሶች ላይ ያተኮረ ጥናት አማኞች (ቤተ ክርስቲያን) በግልም ይሁን በህብረት በየቀኑ እያለፉበት ባሉባቸው የህይወት ተግዳሮቶች እና በረከቶች ጥናት በተደረገ መሰረት የተዘጋጀ ነው። ምክንያቱም የጌታ ቃል ዘመኑን እንድንዋጅ ስለሚያስተምረን ይህንን ጥናት ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኗል (1ዜና 12:32፣ ማቴ 16:3፣ሮሜ 13:11፣ ኤፌ 5:16 እና ቆላ 4:5)።

እንዲሁም በተጨማሪ በቤ/ክናችን የአምስት ዓመት ስልታዊ እቅድ (ወ.ደ.አ.ብ-በሚለው ምህጻረ ቃል) እሴቶቻችን ላይ መሠረት ያደረጉ ጥናቶችም ይኖሩታል።

**<u>ከ2018-2022 ከቤ/ክንቷ ስልታዊ ዕቅድ ላይ የተወሰደ</u>**

- ራዕይ (Vision)
  - ወንጌልን እየመሰከርን
  - ደግ ሥራን እየሰራን
  - አንድነትን እየጠበቅን
  - ብዛትን እናያለን
- <u>እሴቶቻችን (Core Values)</u>
  - አምልኮ
  - መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት እና ጸሎት
  - ለጋሥነት
  - የቅዱሳን አንድነትና ኅብረት
  - ወንጌል ሥርጭት እና ደቀመዝሙር ማፍራት
  - ተተኪ ትውልድ
  - መስጠት
  - ቅድስና እና አንድ-ወጥ ህይወት
  - መጽሃፍ ቅዱሳዊ ትዳርና ጠንካራ ቤተሰብ
  - ቤተክርስቲያን ተከላ
  - ግልጽነት

እግዚአብሔር ለህይወታችን የምንጠቀም ጥናቶች ያርግልን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. ከ1ኛ ቆሮንቶስ ጥናት ያገኛችሁትን ጥቅም መስክሩ።
2. ከጥናቱ አጠቃላይ መግቢያ መሠረት ስንት ዓይነት የጥናት ዘዴዎች ሊኖሩ ይችላሉ። ምን ምንድ ናቸው?
3. የሚከተሉትን ጥቅሶች በማንበብ የዚህን ርዕስ ተኮር ጥናቶች አጠቃላይ ዓላማ ምን እንደሆነ ተወያዩ።
   - 1ዜና 12:32
   - ማቴ 16:3
   - ሮሜ 13:11፣
   - ኤፌ 5:16 እና ቆላ 4:5
4. የቤተ ክርስቲያናችን እሴቶቻችን ምን ምንድን ናቸው?
5. ጊዜ ከተረፋችሁ ዛሬን ለጸሎት ተጠቀሙ።

## ክፍል 1

## ጥናት 1

## መሰጠት (Commitment)

### ዓላማ

አማኝ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር የተጠራ እና የእግዚአብሔር መሆኑን ማስገንዘብ

### መግቢያ

በማንኛውም የህይወት መስክ ስኬታማ ለመሆን ፍጹም መሰጠት እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ ብዙዎቻችን እናውቃለን። ብዙ ጊዜ በቂ የሆነ አለመሰጠት የስኬት ጠላት ነው። በመንፈሳዊ ህይወትም እንዲሁ ነው። መሰጠት ራስን ሙሉ በሙሉ ለጌታ መስጠት ነው። ወንድም ኤጳፍራ እና ወንድም ዴማስ እኩል ጌታን ካገኙ የተወሰኑ ዓመታትን አሳልፈዋል። ሁለቱም አንድ ዓይነት የኑሮ ዘይቤ ያላቸው ወንድሞች ሲሆኑ ኤጳፍራ ሳምንታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይሄዳል፣በዝማሬ ያገልግላል፣አስራቱንና ልዩ ልዩ ስጦታዎችን እንደሚገባ ለጌታ ቤት ይሰጣል። ትርፍ ጊዜ ያገኘ ከመሰለው ደግሞ በትህትና እና በንጽሑ ልብ እንዲሁም ባለው እውቀት እና ጸጋ የቻለውን አስተዋጾ ሁሉ ለጌታ ቤት ያደርጋል። ዴማስ ግን እሁድ ጠዋት ሄዶ አምልኮ ተካፍሎ ከመምጣት እና አስራቱን ከመስጠት ውጪ ሌላ ነገር አያደርግም። ከዚህ ውጪ ግን ባለው ትርፍ ጊዜ ሁሉ ብዙ ፊልሞችን ይከታተላል፣ ከጓደኞቹ ጋር ጊዜ ይወስዳል። ለብዙ የስፖርት ዓይነቶች ትኩረት ይሰጣል። እኩል ጌታን እስካገኙ ድረስ የሁለቱ ልዩነታቸው ምንድ ነው?

ስለ “መሰጠት” ከመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ክፍል መጥቀስ የሚቻል ቢሆንም ለዚህ ክፍል ጥናት በአጠቃላይ ለሉቃስ 14:1-35 ሆኖ ከቁ.15-35 የበለጠ አትኩሮት እንሰጣለን። ጊዜው ከበቃችሁ ሙሉውን ክፍል አንብቡ።

### አጭር ማብራሪያ (ሉቃ 14:1-35)

በሉቃስ ወንጌል 14 በመጀመሪያዎቹ 14 ቁጥሮች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ ህይወታቸውን እንዴት ሙሉ በመሉ ለጌታ መስጠት እንደሚችሉ አስተማራቸው። ማለትም ከልማድ ይልቅ ምህረት እና ርህራሄ በተሞላ ህይወት መኖር እንዳለባቸው(14:1-6)፣ ትሁት በሆነ ህይወት ስለ መኖር መርሆ (14:7-11) እና ጸጋ በተሞላ ህይወት ማለትም ምንም ዓይነት ምላሽ ባለመጠበቅ መንፈሳዊ ነገሮችን ማድረግ እንዳለባቸው አስተማራቸው

(14:12-14)።

በሁለተኛው ክፍል ደግሞ (ሉቃ 14:15-35), ህዝቡ በመሉ እንዴት በተለወጠ እና በላቀ የህይወት መሰጠት መኖር እንዳለባቸው እንመለከታለን። ይህ ክፍል በሁለት ይከፈላል። ከቁ.15-24 ከሁሉ በፊት የህይወት መሰጠት ቀዳሚ እንደሆነ የሚናገር ሲሆን ከቁ.25-35 ደግሞ የሰሙትን በተግባር በመግለጽ እውነተኛ የክርስቶስ የደቀ መዝሙርነት ህይወት መኖር እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በአትኩሮት የሚያስተምር ነው።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1) ሉቃ 14:1-14 ስለ ጥሪ የሚያስተምሩ ሶስት ትምህርቶችን አካፍሉ።
2) ሉቃ 14:15-24 ስናነብ ሶስቱ የሥርጉ ተጋባዦች መልሳቸው ምንድ ነበር? ተወያዩ።
3) የሶስቱ ተጋባዦች መልስ ምን እንከን አለበት? ከዚያ በላይስ ምን እንዲሉ ይጠበቅባቸው ነበር?
4) የዚህ ክፍል ምሳሌ ዋና መልዕክት ምንድ ነው? አካፍሉ?
5) በሉቃ 14:28-35 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስንት ምሳሌዎችን ተናገረ? ምሳሌዎቹስ ምን ትምህርት አላቸው?
6) በእነዚህ የመወያያ ጥያቄዎች ያልተነሱ ከጥናቱ ክፍል ለቡድናችሁ ማካፈል የምትፈልጉት ነገር አለ? ምን?
7) አንድ ዓይነት የክርስትና እድሜ እና የህይወት ዘይቤ ቢኖራቸውም ዴማስ እንደ ኤጳፍራ መሆን ያቃተው ለምንድ ነው?ዴማስ የሚያደርጋቸው ነገሮች በራሱ ምን ችግር አለው? ከምሳሌው እና ከሁለቱ ማለትም ከኤጳፍራ እና ከዴማስ ህይወት ምን እንማራለን?
8) በያለንበት ቦታ ሁሉ ራሳችንን እንደሚገባ ሠጥተን ማገልገል እንድንችል ዛሬ እንጸልያለን (ሉቃስ 9:23)።

## መደምደሚያ

የመሰጠት ትምህርት የመጀመሪያው ደረጃ የህይወት ጥሪ ነው። መሉ መሰጠት ማለት አንዱንም የቤቱን ክፍል ሳናስቀር ሙሉውን ቤት እንደማስረከብ ነው። መሉ መሰጠት የላቀ አገልግሎትን ያጠቃልላል። ይህ ጥናት አንድ እርምጃ ወደ ፊት ለመሄድ ይረዳን ዘንድ ጸሎታችን ነው።

# ክፍል 1
# ለእግዚአብሔር መሥጠት
# ጥናት 2
# መባ

## ዓላማ

የእግዚአብሔርን ሥራ ለመስራት በአንድ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ጥላ ስር ተሰባስበው የሚያመልኩ መዕመናን በልባቸው እንዳሰቡና በደስታ ጥሬ ገንዘብ በአምልኮ ወቅት እንዲለግሱ ለማበረታታትና እንዲሁም ልዩ ልዩ ሥጦታዎችን በዓይነት መስጠት ከፈለጉ ዕድሉን ለማሳየት ነው።

## መግቢያ

መባ ለቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ አገልግሎት ይውል ዘንድ እንደ መስዋዕት በአምልኮ ወቅት የሚሰበሰብ በፈቃደኝነትና ፍቅር ላይ የተመሰረተ የምዕመናን የገንዘብ ማሰባሰብ ሲሆን፤ ለሚያስፈልጋቸው አባላት ጥቅም ይውል ዘንድ ልዩ ልዩ ቁሳቁስም ሆነ መኪና መስጠት ከሚፈልጉም ቤተክርስቲያን ትቀበላለች። ይህ ሁሉ በውዴታ፣ በለጋስነትና በፍቅር ሊሆን ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንኑ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡- "እያንዳንዱ ሰው በቅሬታ ወይም በግዴታ ሳይሆን በልቡ ያሰበውን ያህል ይስጥ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ሰው ይወዳል" (2ቆሮ 9:7)።

እግዚአብሔር በዘዳ፡- 16:13-17 ለሕዝበ እሥራኤል፡- "የእህልህን ምርት ከአውድማህ ፤ ወይንህንም ከመጭመቂያህ ከሰበሰብክ በኋላ... ማንም ሰው በእግዚአብሔር ፊት ባዶ እጁን አይቅረብ..." እያለ ያዘዘው እርሱ ራሱ ባርኮ ከሰጠን ሀብትና ንብረት የፍቅር ስጦታ እንድናቀርብለት ፈልጎና ፈቅዶ እንደሆነ እንረዳለን። በዘፀ፡- 35:4-6 ላይም የመባው ዓይነት ምን ምን እንደሆነ በዝርዝር አስቀምጧል።"ሙሴ ለእሥራኤላውያን ማኅበረሰብ ሁሉ እንዲህ አላቸው፤ እግዚአብሔር ያዘዘው ይህ ነው፤ ካላችሁ ንብረት ሁሉ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቅርቡ፤ ፈቃደኛ የሆነ ማንም ለእግዚአብሔር የወርቅ፣የብር፣ የናስ መባ ያምጣ፣ ሰማያዊ፣ ሐምራዊና ቀይ ማግ፣ ቅጭን ሐር፣ የፍየል ጠጉር፣ ቀይ የተነከረ የአውራ በግ ቆዳ፣ እንዲሁም አስቆጣ ቆዳ፣ የግራር እንጨት፣ ለመብራት የወይራ ዘይት፣ ለቅባዐ ዘይቱና ለጣፋጭ ሽታ ዕጣን ቅመም፣ በኤፉዱና በደረት ኪሱ ላይ የሚሆኑ መርገዶችና ሌሎች ዕንቁዎችን መባ አድርጎ ያምጣ"

መባን ማለትም የፈቃዳችንን መስዋዕት ለጌታ ስናመጣ ያለን ነገር ሁሉ እግዚአብሔር በአደራ የሰጠን እንጅ የኛ እንዳይደለ ተገንዝበን ዓላማችንም የእግዚአብሔር መንግስት

በተለይም የአጥቢያ ቤት ክርስቲያን ሥራ እንዲስፋፋና የወንጌል ስርጭት በዓለም ሁሉ እንዲዳረስ (1ቆሮ፡- 9:4-14)፤ ድሆችም ከችግራቸው እንዲላቀቁ ለመርዳት (ገላ፡- 2:10፤ 2ቆሮ፡-8:13-14) ያነጣጠረ ነው።

መባና ልዩ ልዩ ሥጦታዎቻችን ከብሉይ ኪዳን እሥራኤላውያንን ምሳሌነትና (ዘፀ፡- 35:21-29) ከአዲስ ኪዳን የመቄዶንያ ክርስቲያኖችን ምሳሌነት (2ቆሮ፡-8:1-5) በመነሳት በደስታ ልናቀርብ ይገባናል። በይዘት

የአዲስ ኪዳኗ ቤት ክርስቲያን የስጦታዎች ዓይነት በይዘት ስንመለከት ደግሞ ከጥሬ ገንዘብ በአምልኮ ወቅት ከሚሰበሰበው ባሻገር ልዩ ልዩ ለቤት ቁሳቁስነት የሚያስፈልጉ ንብረቶች፤ አልባሳትና መኪናም ሊሆን ይችላል። እነዚህ ነገሮች በተለይም አዲስ ወደ አሜሪካን አገር ለመጡ ክርስቲያን ወእገኖች ማቋቋሚያም ይሁን በተለያየ ቦታ በመጠለያ ውስጥ ለሚኖሩ ሰዎች መርጃ ይውላሉ። ይህም መልካሙን ሥራችንን አይተው ለአምላካችን ክብር እንዲሰጡ የሚያደርግ ሲሆን በተጨማሪም ለወንጌል በር ያስከፍታል።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በመግቢያው መሰረት መባ ምን ማለት ነው ከአስራትስ እንዴት ይለያል?
2. 2ኛ ቆሮ፡- 9:7 ላይ ያለውን አባባል ያብራሩ
3. መበለቲቱ (ሉቃ፡- 21:3-4) የተመሰገነችበት ምክንያት ምን ነበር?
4. የመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት (2ቆሮ፡- 8:1-3) ከአቅማቸው በላይ ወደው የሰጡት በምን ሁኔታ ላይ እያሉ ነበር?
5. በልግስና መስጠትና በሁሉ ነገር ባለጠጋ መሆን ያላቸውን ትሥሥር (መያያዝ) በ2ቆሮ፡- 9:11-15 መሰረት ይዘርዝሩ
6. በዘፀ፡- 35:20-29 ያሉትን የመባ ዓይነቶች ይዘርዝሩ። በአሁኑ ጊዜስ ምን ምን ሥጦታዎችን ማበርከት እንችላለን?
7. የአካይያ ክርስቲያኖች ሌሎችን ለበጎ ሥራ ማነሳሳት የተገለጸው በምን ነበር (2ቆሮ፡- 9:1-2)?
8. የመባና የልዩ ልዩ ሥጦታዎች ፋይዳ (ጥቅም) ምንድን ነው?

***መደምደሚያ***

በማጠቃለያ መባና ልዩ ልዩ ሥጦታዎች ሕዝቡ አምላኩን እግዚአብሔርን በሚያመልክበት ቦታ ማለትም በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚበረከቱ ሲሆን ጥቅማቸውም ለእግዚአብሔር ክብርን ማምጣት የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን መደገፍና ችግረኞችን መርዳት ላይ ያተኮረ ይሆናል።

# ክፍል 1
# ጥናት 3
# ንዑስ ጥናት፡- አስራት

### ዓላማ

እግዚአብሔር ከሰጠን ሁሉ ለእግዚአብሔር ቤት ሥራ እንዲውል ከአስር አንድ መልሰን የመስጠት ትእዛዝ እና የአዲስ ኪዳን መርህን ለማስገንዘብ

### መግቢያ

### አስራት - ትርጉም

ከመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንገነዘበው አሥራት ለእግዚአብሔር የሚሰጥ የእርሻ ምርትና የከብት አንድ አስረኛ ነው። የዕብራይስጥ አቻ ቃሉ ማሴር ሲሆን ጥሬ ትርጉሙም አንድ አሥረኛ ማለት ነው። አሥራት አብርሃም በፈቃዱ ከሰጠውና ያዕቆብ በስለቱ ቃል ከገባው ባሻገር የሕግ ስጦታ ነው። ዘሌ፡- 27:30 – "ከእርሻ ምርትም ሆነ ከዛፍ ፍሬ ማንኛውም ከምድሪቱ የሚገኝ አሥራት የእግዚአብሔር ነው" አስራት ሰው ካገኘው የእህል እና መሰል ምርት እንዲሁም ገንዘብ ላይ አንድ አስረኛውን ቀንሶ ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው ሥጦታ ነው። አስራት ለመጀመሪያ ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሶ የምናየውም በዘፍ፡- 14:20 ላይ ነው። "አብራምም ካመጣው ሁሉ ዐሥራትን ሰጠው" ቀጥሎም ያዕቆብ "… ከምትሰጠኝም ሀብት ሁሉ ከዐሥር እጅ አንዱን ለአንተ እሰጣለሁ" ብሎ እንደተሳለ በዘፍ፡- 28:20-22 ላይ እንመለከታለን።

ጌታ ኢየሱስም በማቴ፡- 23:23 አስራት መስጠትን የሚደግፍ መሆኑን እንገነዘባለን። ምክንያቱም፡- "… እነዚያን (ከአዝሙድ፣ ከእንስላልና ከከሙን አሥራት መስጠትን) ሳትተው እነዚህን (ፍትህን፣ ምህረትንና ታማኝነትን) ማድረግ በተገባችሁ ነበር…" ብሏልና። እሥራኤላውያን የከብቶቻቸውን፣ የምድራቸውን ፍሬና የገቢያቸውን አንድ ዐሥረኛ ለእግዚአብሔር እንዲሰጡ ታዘዋል። የሰው ልጅ በሙሉ አስቀድሞ ከእግዚአብሔር ያልተቀበለው ምንም ነገር የለውም።

## ዐበይት ነጥቦች

### አሥራት የሚሰጥበት ቦታ

እሥራኤላውያን አሥራትን እንዲሰጡ የታዘዙት እግዚአብሔር ስሙ ይጠራበት ዘንድ ባዘዘበት ስፍራ በማደሪያው ድንኳን፤ በቤተ መቅደሱ ነበር (ዘዳ፡- 12:5-6፣26:2) ። በአዲስ ኪዳን አሥራትን የምናስገባው አባል በሆንንበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ነው።

### የአሥራት አሰጣጥ ሁኔታ

ከጅምሩ እስከመጨረሻው ያገኘነው ሁሉ ከእርሱና በእርሱ እንደሆነ ራሳችንን እያስገነዘብን በትህትና አስራታችንን ልንሰጥ ያስፈልጋል።

### በእግዚአብሔር ቤት አሥራት ለምን ተግባር ይውላል?

አስራት የምንሰጠው ለእግዚአብሔር ቤት ሥራ አገልግሎት ሁሉ እንዲውል ነው።

### አስራትን አለመስጠት

በነቢዩ ሚልክያስ ዘመን (ሚል፡- 3:9-12) ፡-“... ዐሥራትና መባ ትሰርቁኛላችሁ፤ እንናንተም መላው ሕዝባችሁም ስለምትሰርቁኝ የተረገማችሁ ናችሁ።” የሚል የእግዚአብሔርን ቃል እናያለን።በዚህም መሰረት አስራትን አለመስጠት የእግዚአብሔርን ሕግ አለመታዘዝና እግዚአብሔርንም መስረቅ እንደሆነ ግልጽ ነው።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ዘፍጥረት 14:19-20፣ 28:20-22 መሰረት ህግ ከመሰጠቱ በፊት አስራትን ስለ መስጠት ምን ያስተምረናል?
2. ዘሌ. 27:30–34፣ዘኍል 18:21 በማንበብ ስለ አስራት መሠረታዊ ህግ/ትዕዛዝ ተወያዩ
3. በ2ኛ ዜና፡- 31:4-5 መሰረት አሥራትን የመስጠት ዓላማ በተመለከተ ምን ተረዳን፣ በዚህስ ክፍል የሕዝቡስ ምላሽ እንዴት ነበር?
4. ሚል 3:7-12 በማንበብ አስራትን በተመከተ የህዝቡ ችግር ምን ነበር? እግዚአብሔር የነገራቸውስ መፍትሔ ምን ነበር?
5. በማቴ፡- 23:23 በማንበብ በአዲስ ኪዳን አስራትን በተመለከተ ምን መርህ እንማራለን?
6. በአሁን ዘመን አስራትን ላለመስጠት ሰዎች የሚሰጡት ምክንያቶች ናቸው የምትሉትን ተነጋገሩ። አስራትስ የት ነው መከፈል ያለበት (ለምሳሌ ወደ ለሌላ ቤ/ክ መላክ)?

7. እስካሁን በተመለከትነው መሰረት አስራታችንን እንዴት እና ለምንድ ነው የምንሰጠው (ባለመክፈል የሚመጣውን ቅጣት ፈርተን ወይስ በፈቃደኝነት፣በደስታ እና በፍቅር?)።
8. አስራታችን ባለመስጠት በእግዛብሔር ሥራ ላይ ምን ተጽዕኖ ሊፈጥር እንደሚችል ተወያዩ?
9. በዛሬው ጥናታችን መሠረት አስራታችንን በፈቃደኝነት፣በታማኝነት፣በደስታ እና በፍቅር እንድንሰጥ እንጸልያለን።

***መደምደሚያ***

አስራት ከምናገኘው ገቢ ሁሉ ከመቶ አሥር እጅ ሲሆን ይህንንም ለእግዚአብሔር ቤት ሥራ በፈቃደኝነት፣በታማኝነት፣በደስታ እና በፍቅር የምንሰጥ ስጦታ ነው።

## ክፍል 1
## ጥናት 4
## ንዑስ ጥናት፡- በኩራት

**ዓላማ**

በዚህ ምድር ላይ ስንኖር እግዚአብሔር ከሰጠን በረከት ሁሉ የመጀመሪያውን (በኩሩን)ለእርሱ መስጠት እንዳለብን ግንዛቤን ለማስጨበጥ ነው።

**መግቢያ**

በኩራት ማለት የመጀመሪያ ሲሆን እሥራኤላውያን፡- “በማሳህ ላይ በዘራኸው እህል በኩራት የመከርን በዓል አክብር… የምድርን ምርጥ ፍሬ በኩራት ለአምላክህ ለእግዚአብሔር አምጣ” ዘፀ፡- 23፡16፣ 19 ተብለው እንደታዘዙ እንመለከታለን። በዚህም መሰረት ነህምያ በዘመኑ (ነህ፡- 10፡34-37) እሥራኤላውያን የሰብላቸውን፣ ከዛፍ ፍሬ የሚያገኙትን፣ የልጆቻቸውን፣ የቀንድ ከብቶቻቸውን፣ የበግና ፍየል መንጋዎቻቸውን በኩራት በዓመቱ የመጀመሪያው ቀን ወደ አምላካቸው ቤትና ወደሚያገለግሉትም ካህናት በሕጉ መሰረት እንዲያመጡ አዟል። ይህም ማህጸን ከፋች የሆነ የሰውም ይሁን የእንስሣ በኩር ማለት ነው።

እሥራኤላውያን አምላካቸው እግዚአብሔር ለስሙ ማደሪያ ይሆን ዘንድ በመረጠው ቦታ ላይ የሚቃጠል መስዋዕቶቻቸውንና ሌሎች መስዋዕቶቻቸውን፤ አስራታቸውንና የእጃቸውን ስጦታ ስእለቶቻቸውንና የፈቃዳቸውን ስጦታዎች ፤ የቀንድ ከብት መንጋቸውን፤ የበግና የፍየል መንጋቸውን በኩራት እንዲያቀርቡ ተነግሯቸዋል (ዘዳ፡- 12፡4-6)።

ስለ በኩራት በአሁኑ ዘመን በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የተለያዩ ዓይነት የመስጠት ልምምዶች ይኖራሉ፡፡ ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱስን **<u>መርህ</u>** ስንከተል ለመጀመሪያ ጊዜ የምናገኘው ገቢ (ለምሳሌ የመጀመሪያ ወር ደመወዝ እና የደመውዝ ጭማሪ ለውጥ አንድ ጊዜ ወዘተ) ለእግዚአብሔር የበኩራት ስጦታችን ልናደርገው እንችላለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በመግቢያው መሰረት በኩራት ማለት ምን ማለት ነው? መቼስ ተጀመረ? (ዘጸ 23፡-16-19
2. በነህምያ መጽሐፍ የተዘረዘሩትን የበኩራት ዓይነትችህ ዘርዝር (ነህ፡- 10:34-37)

3. “እግዚአብሔርን በሀብትህ ከምርትህ ሁሉ በኩራት አክብረው” (ምሳ፡- 3:9) ይህን ሲል ምን ማለቱ ነው?

4. የብሉይ ኪዳን የበኩራት ስጦታ ድንጋጌ ለአዲስ ኪዳን የበኩራት ስጦታ የምንማረው መርህ ምንድ ነው?

5. የየቤተ እምነቶች ልምምዶች የተለያዩ ቢሆንም የበኩራት ስጦታ አድርገን ልናቀርባቸው ስለምንችላቸው ነገሮች ተወያዩ?

6. አንድ አማኝ የበኩራት ስጦታውን ለእግዚአብሔር ሲያቀርብ ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ግኑኝነት ምን ያመለክታል?

7. ከዛሬው ጥናት የተረዳችሁትን ለቡድኑ አካፍሉ።

***መደምደሚያ***

በኩራት በብሉይ ኪዳን ካሉት የመስጠት ዓይነቶች አንዱ ሲሆን፤ በዚህም ዘመን በየቤተ እምነቶች የተለያዩ ዓይነት ልምምዶች ቢኖሩም የበኩራት ስጦታ ከመስጠት መርሆች አንዱ ነው። ስለዚህም የኩራት ስጦታ በዋናነት የሚያመለክተው ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር እና መሰጠትን የሚያሳይ እውነት ነው።

## ክፍል 1
## ጥናት 5
## ንዑስ ጥናት፡- ችግረኞችን መርዳት

### ዓላማ

በጎ ነገር ከማድረግ እንዳትታክቱ ቅዱሳንን ለማሳሰብ (ገላ፡- 6:9)።

### መግቢያ

የዳንነው መልካም ሥራ በመስራት ሳይሆን መልካም ስራን የምንሰራው ስለዳንን እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል (ኤፌ፡- 2:9-10) በግልጽ ያስተምረናል። ይህም ማለት በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርነው እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ስራ የመስራት ተግባር እንድናከናውን ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክፉውን ስራችንን በሞትና ትንሳኤው ዋጋ ከፍሎ በመልካምነት ስለለወጠው ከድህነት በኋላ ሊኖረን የሚኖረው ተግባር መልካም ተግባር ነው። እናም ርህሩሆችና አካፋዮች መሆን ይጠበቅብናል።

የተቸገሩትን መርዳት እግዚአብሔር የሚወደው ተግባር ሲሆን ሰዎች በዚህ ምክንያት በሰማይ ያለውን አምላካችንን እንዲያከብሩ ይሆናል። የበጎ ተግባር ገጽታ የሆነውን ድርጊት የእግዚአብሔር ቃል በያዕቆብ፡-1:27 እንደዚህ ይገልጸዋል፡- “በእግዚአብሔር አብ ፊት ንጹህና ነውር የሌለበት ሃይማኖት ይህ ነው፤ ወላጆቻቸው የሞቱባቸውን ልጆችና ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶች በችግራቸው መርዳት…” ሐዋርያው ጳውሎስም በመልዕክቱ (የሐዋ፡- 20:35) ይህንን እውነታ አትቷል።

ጌታ እንዴት ለድሆች እንደሚያስብም ሆነ ወሮታም እንደሚከፍል የእግዚአብሔር ቃል ሲያስረግጥ፡- “ለድኻ የሚራራ ለእግዚአብሔር ያበድራል፤ ስላደረገውም ተግባር ዋጋ ይከፍለዋል” ይላል (ምሳ፡- 19:17)።

የሉቃ 10:29-37 ባለው ክፍል ስለ እውነተኛ ባልንጀራ ይናገራል። በአጭሩ ማናችንም ብንሆን ተመዝነን ጓድለን እንዳንገኝ ሌሎችን ለመርዳት መትጋት አለብን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በማቴ፡- 25:35-40 መሰረት ጌታ “ተርቤ አብልታችሁኛል፤ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛል ... ? ጌታን ማብላት እና ማጠጣት ይቻላል? ካልሆነ ምንድን ነው?
2. በዘዳግም፡- 15:11 መሰረት “... በዚያ ለሚኖሩ ወንድሞችህ ለድኾችና ለችግረኞች እጅህን እንድትዘረጋ አዝሃለሁ” ይላል። እጅ መዘርጋት ማለትስ ምን ማለት ነው?
3. የቸር ሰውን በረከት በመዝ፡- 41:1-3 መሰረት ዘርዝሩ
4. ሉቃ 10:29-37 መሠረት እውነተኛ ባልንጀራ ማን ነው? እኛስ ምን እናድርግ?
5. በዕብራውያን፡- 13:16 መሰረት እንዳንረሳ የታዘዝነው ምንድን ነው?
6. ያዕቆብ፡-1:27ን በማንበብ ችግረኞችን መርዳት ከአምልኮ ጋር እንዴት እንደተያያዘ ተወያዩበት።
7. ሮሜ፡- 12:13 ችግረኞችን ስለ መርዳት ምን ይላል?
8. በመካከላችን ስላሉት ችግረኞች ምን ማድረግ እንደሚትችሉ ተወያዩ፤አድርጉ። ማንንም ችግረኛ ካለወቃችሁ በመሪዎቻችሁ በኩል አናግሩን።

***መደምደሚያ***

ጠቅለል ባለ መልኩ ስናስቀምጠው የተቸገሩትን መርዳት መልካም ስራ ሲሆን ይህንንም የምናደርገው ለህዝቡ መልካም ስራን በማድረግ አምላካችን ደስ እንደሚለው (ኤር. 32:41) እኛም ደስ እያለን ልናደርገው ይገባል።

# ክፍል 2

# ወጥነት ያለው ሕይወት (“Integrity”)

## ጥናት 6

## ንዑስ ጥናት፡- ወጥነት ያለው ሕይወት

**ዓላማ**

ከእግዚአብሔር እና ከሌሎች ጋር በሚኖረን ግንኙነቶች የማይለዋወጥ ቅንነት የተሞላ ህይወት ምን እንደሆነ ማሳሰብ

**መግቢያ**

“ያለ ነውር የሚሄድ ተማምኖ ይሄዳል፤ መንገዱን የሚያጣምም ግን ይታወቃል” (ምሳሌ 10:9)። እንዲሁም (ምሳሌ 11፥ 1-3) “አባይ ሚዛን በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ ነው፤ እውነተኛ ሚዛን ግን ደስ ያሰኘዋል። ትዕቢት ከመጣች ውርደት ትመጣለች፤ በትሑታን ዘንድ ግን ጥበብ ትገኛለች። ቅኖች ቅንነታቸው ትመራቸዋለች፤ ወስላቶችን ግን ጠማማነታቸው ታጠፋቸዋለች” ይላል።

አማኝ ወደ ጌታ ሲመጣ እንደነበረው ፍቅሩ ሳይቀዘቅዝ ሊኖር ይገባል። እንዲሁም ለአገልግሎት ያለንንም ፍቅር እና ጽናት የተለያዩ ነገሮች ሊያቀዘቅዘውና ሊለዋውጠው አይገባም። ተለዋዋጭ የሆነ ባህርይም ከእግዚአብሔር ህዝብ በምንም ዓይነት መንገድ አይጠበቅም።

በአማርኛችን መፅሐፍ ቅዱስ ቅንነትን አንዳንዴም ፍፁምነት ሲል በኢንግልዝኛ ደግሞ “ኢንተግሪቲ” (Integrity) ይለዋል፡፡ ቅን ማለት በአማርኛ መዝገበ ቃላት ትርጉም መሠረት (1)- በመንፈሱ ጠማምነት የሌለበት። ለምሳሌ፡-ቅን አሳቢ። ቅን ሰው። ቅን ልብ። ቅን ልጅ ይባላል (2)- በጎ ነገር ያለበት ተንኮል የሌለው ልበ ገር ቅን ሰው፣ (3)- ተንኮልና ክፉ ነገር የማያስብ ሰው ብሎ ይተረጉማል፡፡ “ኢንተግሪቲ” (Integrity) የሚለው ቃል ደግሞ (1)- ሐቀኛነት፣ (2-) አንድነት (አንድ አይነት ሆኖ መገኘት) ሙሉነት (ፍፁምነት) (3)- በአቋሙ የሚፀና 4-አስመሳይነት የሌለበት ወይንም ግብዝ ያልሆነ ብሎ ይተረጉመዋል፡፡ እነዚህን ሐሳቦች ይዘን በመፅሐፍ ቅዱስ እይታ ቅንነት የሚሉትን ጥቅሶች በማጥናት ምን ማለት እንደሆነና ምን ውጤት እንዳለው ለመረዳት እንሞክራለን፡

## አጭር ማብራሪያ

አማኝ የተጠራው ያለ ግብዝነት፣የህሊና ወቀሳ እና በማህበራዊ ኑሮውም ለእግዚአብሔር ክብር እና ለሌሎች በረከት በመሆን ያለነቀፋ በመመላለስ እንዲኖር ነው። ይህን የመሰለ አንድ ወጥ ህይወት መኖር ለአማኝ የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ጌታውን የመምሰልና የማንነቱ (Christian Identity) ጉዳይ እና ጥሪ ነው። የእግዚአብሔርን ማንነት ሳይኖሩ በኃይማኖታቸው የተኩራሩ ፈሪሳውያንን የአደባባይና የግል ህይወታቸውን አስመልክቶ ጌታም ሲገስጻቸው “እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ በውጭ አምረው የሚታዩ በውስጡ ግን የሙታን አጥንት ርኩሰትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን ስለምትመስሉ፥ ወዮላችሁ” (የማቴ.23፥27፣ሐዋ 23:3) ይላቸው ነበር። አንድ ወጥ ህይወት ድካማችንን ተረድተን፣ራሳችንን እየመርመርን ከጌታ ዘንድ ወዴት እሄዳለሁ በማለት ባለማስመሰል ህይወት በጸጋው በተደገፈ በቅንነትና፥ በትጋት መኖር ነው። ሁሉን በሚያውቅ ጌታ ፊት ስንመመላለስ አንድ ወጥ ህይወት ምን ይመስላል? ለዚህ ጥያቄ በርከት ያሉ ነገሮችን ከመጽሐፍ ቅዱስ የምናይ ሲሆን፣ እንደ ምሳሌ ጥቅት ነገሮችን እናነሳለን። ይህ ህይወት አካሄድን ከጌታ ጋር ማድረግን፣በፊቱ ሞገስ ማግኘትን፣ ወዳጄ የሚያስብል፣ ጌታ ራሱ እንደ ልቤ ብሎ የሚመሰክርለት ከውጣ ውረድ ነጻ የሆነ የጽድቅ ህይወት ነው። በአጭሩ ያልተወሳሰበ የመንፈሳዊ የህይወት ጉዞ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በቅንነት ስለመመላለስ ብዙ ነገሮችን ያስተምረናል። በከፍታም ሆነ በዝቅታቸው ታሪካቸው ከተጻፉ ሰዎች ታሪክ የምንወስደው ዘመናትን ያለፈ እውነት እንዳለን እናውቃለን። ከአብርሃም ህይወት፥ የሚታይ ነገር ባይኖርም ተስፋው እስኪሞላ ጌታን በቃሉ የመጠበቅ ህይወት ነው። ከዮሴፍ ህይወት በምንም ሁኔታ ውስጥን፥ በመከራ፥ የሥጋ ፍላጎትን በመግዛት፥ ይቅርታን በማድረግ እና በተሰማሩበት በትጋት በመመላለስ እግዚአብሔርን መታዘዝና ማስከበር ነው። ከጴጥሮስ ህይወት ደግሞ፥ ያለፈው ውደቀታችን ሳይዘን ተመልሰን በተጠራንበት መሥመር መገኘት ነው። ከዳዊትና ከሰሎሞን ከውድቀት በመማር በምህረት አምላክ ሥር ራስን ማስቀመጥ። ከሙሴ እንደሱ ትሁት የሆነ የተጠራውን ጉዞ አጥብቆ መያዝና ሩጫን መጨረስ አለበት። ሩት እስከ መጨረሻ እንደጸናች መጽናት ነው። መከራን ከጥፋታችን የተነሳ ሳይሆን በጽድቅና ለእውነት በመቆም በጌታ፣ በገዢዎች ሆነ በኅብረተስቡ ዘንድ ያለነቀፋ ሆኖ የመቀበል ህይወትም ነው። ጳውሎስ ለአግሪጳ ከእሥራቴ በቀር ብሎ እንደመሰከረው ለጥሪያችን መጽናት ነው።

አንድ ወጥ ህይወት ለግብዝነት ስፍራ የለውም። ለጌታ ክብርን፥ለሌሎች በመልካምነት ምሳሌ በመሆን፥ እረፍት እና በረከትን የሚያመጣ ህይወት ነው። በተጨማሪም ጌታ ራሱ

በጠላት ፊት እንኳን ባሪያዬን አየኸው/አየሃት በማለት ደስ የሚሰኝበት ፍጹምና ቅንነት፥ እግዚአብሔርን የመፍራትና ከክፋትም የመራቀ ህይወት ነው (ዘፍ.5:24፤6:24፤ ኢዮብ 1:8፤ ሉቃስ 1:6 ሌሎች ክፍሎችም)።

ኢዮብ ያለፈበት የህይወት ጎዳና ለሁላችንም ባይሆንም ከታሪኩ የምንማረው በቅንነት ስንመላለስ ከሰልፍ ነጻ አለመሆናችንን ነው። በምናልፍበት ነገር ጌታ ለብቻችን አይተወንም። የእርሱ ጣልቃ ገብነት በመንገዳችን ሁሉ ይታያል።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. የጥናቱ ዓላማ ምንድ ነው? ስለአንድ ወጥ ህይወት ያለህን መረዳት ለቡድንህ አካፍል።
2. ምሳሌ 4:23፣10:9 እና 11:1-3 በማንበብ ስለ አንድ ወጥ ህይወት የሚያሳስበን ምንድን ነው?
3. በ1ኛ ጴጥሮስ 3:10-12 ዘወትር ሊኖረን ስለሚገባ የህይወት አካሄድ የተዘረዘሩትን ሀሳቦች ተነጋገሩባቸው (ሉቃስ 6፡ 45)።
4. የማቴ.23፥27፣ሐዋ 23:3 ከእነዚህ ጥቅሶች ስለ አንድ ወጥ ህይወት ምን እንማራለን?
5. በ2ቆሮ 8:21 መሠረት ስለ አንድ ወጥ ህይወት የተረዳኸውን አካፍል?
6. አንድ ወጥ ህይወት እንዳይኖረን የሚያደርጉ ነገሮች ምንድ ናቸው?
7. ከ1ኛ ዜና 29:17 ከዚህ ክፍል ስለ አንድ ወጥ ህይወት ምን ያስረዳል?
8. መዝ 17:1-6፣ 26:1-12 የዳዊት ጸሎትና መዝሙር ምንን ያካተተ ነበር? ምንስ ያስተምረናል?

***መደምደሚያ***

አንድ አማኝ በ እግዚአብሔርና በሰዎች ፊት አንድ ውጥ በሆነ ህይወት የመመላለስ ኃላፊነት አለበት። ንግግራችን እና ተግባራችን አንድ ሊሆን ይገባል። በምሳሌ 10:9 “ ያለ ነውር የሚሄድ ተማምኖ ይሄዳል፤ መንገዱን የሚያጣምም ግን ይታወቃል” ይላል።

# ጥናት 7

## ቀጣይ፡- ወጥነት ያለው ሕይወት

### ዓላማ

ከእግዚአብሔር እና ከሌሎች ጋር በሚኖረን ግንኙነቶች የማይለዋወጥ ቅንነት የተሞላ ህይወት ምን እንደሆነ ማሳሰብ

### መግቢያ

"አንድ ወጥነት" እና "ቅንነት" ብዙ ግንኙነት ያላቸው ቃላቶች ናቸው። አንድ ወጥ ህይወት ለግብዝነት ስፍራ የለውም። ለጌታ ክብርን፥ለሌሎችም በረከትን የሚያመጣ ህይወት ነው። እንዲሁም ጌታ ራሱ በጠላት ፊት እንኳን ባሪያዬን አየኸው/አየሃት በማለት ደስ የሚሰኝበት ፍጹምና ቅንነት፥ እግዚአብሔርን የመፍራትና ከክፋትም የመራቀ ህይወት ነው (ኢዮብ 1:8-22 ሌሎች ክፍሎችም)።

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. በ1ኛ ነገስ 9:4-5 መሰረት ስለ ቅንነት የተማራችሁትን በስፋት ተወያዩ። "ቅን" መሆን ማለት ምን ይመስላችኋል? እንዲሁም "ቅንነት" ከአካሄድ ጋር ይያዛል ማለት ነው?

2. በኢዮብ 2:3 መሰረት ኢዮብ በአግዚአብሔር የተመሰገነበትን ምክንያት በዝርዝር ተነጋገሩ?

3. በኢዮብ 2:9-10 መሠረት በተለይ በአግዚአብሔርና በቃሉ ላይ ባለን አቋም ቅንነት ("Integrity") መጠበቅ ወይም እስከመጨረሻ ጸንቶ መቆም ምን ያህል ከባድ ሊሆን እንደሚችል ተነጋገሩ? ኢዮብ ሁኔታው ቢለወጥም ለምን በአቋሙ መጽናት ቻለ? ለምን ሚስቱ አልቻለችም?

4. ምሳ 10:9 "ያለ ነውር የሚሄድ ተማምኖ ይሄዳል፤ መንገዱን የሚያጣምም ግን ይታወቃል።" "ያለ ነውር የሚሄድ" ወይንም በቅንነት ("Integrity") የሚሄድ ምን ይሆንለታል? ለምን? በተቃራኒው በቅንነት የማይሄድ ምን ይሆናል? (ፍንጭ፡- "ይታወቃል"_"ይጋለጣል")፡፡ ስለዚህ ቅንነት ("Integrity") ማለት በአንድ ዓርፍተ ነገር በዚህ ጥቅስ መሰረት ምን ማለት ነው?

5. በማቴዎስ 23:3 መሰረት የምንናገረውና የምናደርገው አንድ ሳይሆን ሰዎች ምን ይላሉ? ጌታ በዚህ ክፍል ለራሱ ደቀ መዛሙርት ምንድነው የመከራቸው?

6. በቆላ 3:22 መሠረት ስል ቅንነት ምን እንማራለን?

7. ካለፉት ሁለት ጥናቶች ስለ ቅንነት/ፍፁምነት (“Integrity”)- የተረዳችሁት ምንድ ነው?

8. ጌታ በራሱ እና በሌሎች ፊት የማንለዋወጥ አንድ ወጥ ህይወት እና አገልግሎት ያለን ልጆቹ ያድርገን? የዛሬውን ጥናት በዚህ ጸሎት እንጨርሳለን።

***መደምደሚያ***

ቅንነት በእግዚአብሔር እና በሰዎች ፊት የማይለዋወጥ ህይወት መኖር ነው። ስለዚህ በቅንነት (“Integrity”) መኖር ማለት ከሙሉ ልብ እግዚአብሔርን በመውደድ፣ በታማኝነት፣ ግብዝነት በሌለው ሕይወትና ባመኑበት አቋም ፀንቶ እንደ እግዚአብሔር ቃል መኖር ነው፡፡

## ጥናት 8
## ንዑስ ጥናት፦ ቅንነት (“Integrity”)
የዮሴፍ፣ የዳንኤል እና የጓደኞቹ ህይወት

***ዓላማ***

የእግዚአበሔር ሰዎች በቅንነት (“Integrity”) እንዴት ለመኖር እንደቻሉ ከህይወታቸው በማጥናት በጌታ ጸጋ በሕይወታችን ቅን ሰዎች ሆነን እንድንገኝ ለመማር።

***መግቢያ***

ዮሴፍ ብዙ ካለፈበት የሕይወት ጎዳና የተነሳ ብዙ ነገሩ ሊለዋወጥ ሲችል ቅንነቱን (በፍጹምነቱ) ጸንቶ በመኖር በእግዚአብሔርና በሰው ፊት አስመስክሯል፡፡ እንደዚሁም ዳንኤል እና ጓደኞች መልኩ ይለያይ እንጂ በእኛም ሕይወት የሚያልፉና ሊያልፉ የሚችሉ ብዙ ነገሮችን በመጽናት አሳልፈዋል፡፡ እኛንም እግዚአብሔር እንደ ዮሴፍ፣ ዳንኤልና ጓደኞቹ በታማኝነትና በቅንነት ጸንተን መኖር የምንችልበትን መርህ ማወቅ እንድንችል እንወያያለን።

## የመወያያ ጥያቄዎች

1. ያለፈውን ጥናት በመከለስ ወይንም በማስታወስ ቅንነት (“Integrity”) ምን ማለት እንደሆነ ተነጋገሩ፡፡
2. ዘፍጥረት 37:18-20 እና 45:4-5 በማስተያየት ዮሴፍ ከብዙ ዓመታት በኋላ ወንድሞቹን ሲያገኛቸው በንግግሩ ቅንነትን እንዴት ሊያሳይ እንደቻለ በመወያየት እኛም ጎዱን የምንላቸውን የቅርብ ወይም የሩቅ ሰዎች ላይ ልባችንን በቅንነት ለመጠበቅ እንዴት እንደምንችል ተነጋገሩ::
3. ዘፍ 39:7-12 በማንበብ ዮሴፍ ወጥ የሆነውን ህይወቱን እንዴት እንደጠበቀ እና ምን ዋጋ እንዳስከፈለው በማየት ተወያዩበት፡፡
4. በዳንኤል 1:8-16 እንደሚያሳየው ዳንኤል ምን ዓይነት አቋም ወይም የህይወት ወጥነት አሳየ? ይህንን ሊያደርግ የቻለው በምን ላይ ተመስርቶ እንደሆነም ተወያዩ?
5. ቅንነት/ፍፁምነት (“Integrity”) ከሚያሳጡ ዋና ነገሮች አንዱ ማመቻመች ነው:፡ ዳንኤልና ዮሴፍ እንዲሁም የዳንኤል ጎደኞች (ዳንኤል 3:16) ማድረግ ቢፈልጉ ማመቻመች ስለሚችሉባቸው ሁኔታውች ተወያዩ:፡
6. ዮሴፍ እና ዳንኤል በእምነታቸው ሲጸኑ እግዚአብሔር ምን አደረገ? የቅንነትስ ወጤቱ ምንድ ነው?
7. ከላይ ባየናቸው ምሳሌዎች መሰረት ዛሬም ቅንነታችን/ፍፁምነታችን (“Integrity”) በምን በምን ጉዳዮች ላይ ሊፈተን እንደሚችል ተወያዩበት:፡
8. እስካሁን ባጠናነው መሰረት ቅንነት/ፍፁምነት (“Integrity”) መጠበቅ ለምን አስፈለገ? ለወንጌል እንዴት መጠቀም እንችላለን?

## ማጠቃለያ

ምሳሌ የሆኑን የእግዚአብሔር ሰዎች ቅንነት/ፍፁምነት (“Integrity”) ጠብቆ ለመኖር እግዚአብሔርን በቃሉ ማመን፡ የእምነት እርምጃን መውሰድና ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ መሆንን እንደሚጠየቅ ያስተምሩናል፡፡ ማመቻመች (compromising) ለእግዚአብሔር ክብር አንዳንኖርና የእርሱም ክብር ለኛም ይሁን ለሌሎችም እንዳይገለፅ እንቅፋት ይሆናል:፡፡ አግዚአብሔር ቅንነት/ፍፁምነት (“Integrity”) ባለው ሕይወት ይባርከን! አሜን!

## ክፍል 3

## እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት

## ጥናት 9

## የእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ምንነት

**ዓላማ**

ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መሰረትና ምሳሌ የሆነንን ጌታን ማየት፣ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ዋጋ የሚያስከፍል መሆኑን ማስገንዘብና ለጸሎት ማነሳሳት ነው ።

**መግቢያ**

በአዲሱ መደበኛ ትርጉም ላይ "እውነተኛ መንፋሳዊነት ሕይወት" የተባለው ፤ በድሮው ትርጉም ላይ "እግዚአብሔርን መምሰል" ( ኪንግ ጄምስ godliness) ተብሏል ። “እውነተኛ መንፈሳዊነት” ሕይወት ወይም እግዚአብሔርን መምሰል፤ "ዩሴባያ" ለሚለው የግሪክ ቃል የተሰጠ ፍቺ ነው ። ግሪኮች ፤ ለአማልክቶቻቸው የነበራቸውን ፍርሃትና አክብሮት የተሞላ አምልኮዊ ልምምድ "ዩሴባያ" ብለው ይጠሩታል ። የአዲስ ኪዳን መልዕክት ጸሐፊዎችም ፤ አማኝ ለአምላኩ ያለውን መሰጠት (DEVOTION IN ACTION) ፤ የሚያሳይበትን የሕይወት ዓይነት ለማሳየት ፤ በመልዕክቶቻቸው ይህንኑ ቃል ተጠቅመዋል። እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ማለት፤ ልክ ለሄኖክ እንደ ተመሰከረለት ፤ ባልተቆረጠ ልባዊ ትኩረት በእግዚአብሔር ፊት መኖር ፤ መመላለስ ፤ ማለት ነው ። እግዚአብሔርን ከልብ የመፍራት ፣ የመውደድና የመጠማት ሕይወት ነው ። እንዲህ አይነቱ መሰጠት ፤ በግል በሚደረግ የጸሎት ልምምድና የቃል ጥናት ሕይወት ፤ የሚንጻባረቅ፤ ልበናዊ ዝንባሌ ነው ።

በዚህ ጥናት "እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት" የሚለውን ሐረግ የያዙ ጥቅሶችን ከመጸሐፍ ቅዱስ ለቅመን በመመልከት፣ ተያይዞ የቀረቡትን ሃሳቦች በማዛመድና በመወያየት ፤ ጌታ መንፈስ ቅዱስ የሚያስተምረንን እውነት እንቀስማለን ። የምናጠናበት ዋና ዓላማ፤ መጸሐፍ ቅዱስ የሚለውን በመመልከት ራሳችንን ለእውነተኛ መንፋሳዊ ሕይወት ልምምድ ለማነሳሳና ለማሳሰብ ነው።

በቅድሚያ ፤ ስለ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ምንነት ያየነውን ትርጉም ከግምት ውስጥ በማስገባት ፤ ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 3:16 ፣ በምዕራፍ 2፡ 1-2/ 2ኛ ጴጥሮስ 3:11 እና በ2ኛ ጢሞቴዎስ 3:12 የሚያነሳቸውን ሃሳቦች እመለከታለን ።

- 1ጢሞ 3፡16 ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መሰረትና ምሳሌ የሆነንን ጌታችን ያሳየናል ። ወደ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ለመደረስ ፤ በቅድሚያ ፤ እውነተኛ መንፈስዊ ሕይወትን በሙላት ኖሮ ምሳሌነቱን በተወልን በጌታ ላይ መመስረት ይኖርብናል ። ያለ እርሱ ፤ እግዚአብሔርን የሚፈራ ፣ የሚወድና የሚጠማ ሰው መሆን አንችልም ።

- በ2ኛ ጢሞቴዎስ 3:12 ክርስቶስን መሰረት ያደረገ ፤ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ለመኖር የሚፈልጉ በዓለም የሚደርስባቸው ስደት እንዳለ ያሳያል ። ዓለም እግዚአብሔርን የማይፈራ ፣ የማይወድና የማይጠማ ነው ።

- 1ጢሞ 2:1-2 ውጫዊ ተጽዕኖ ፤ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ለመኖር የምናደርገውን ልምምድ እንዳያስተጓጉልብን ፤ ለሌሎችና ለነገስታትን መጸለይ እንዳለብን ያሳየናል ።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በመግቢያው መሰረት እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ምን ዓይነት ሕይወት ነው ?
2. በ1ኛ ጢሞቴዎስ 3:16 ላይ “ምስጢር” እና “ያለ ጥርጥር ታላቅ” የተባለው ምንድን ነው ?
3. በ1ኛ ጢሞቴዎስ 3:16 ላይ "እርሱ" ካለ በኋላ የሚዘረዝራቸው ነጥቦች የሚያሳዩት ማንን ነው ? በዚህ ጥቅስ ውስጥ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት የሚለው ሀሳብ በምን መለኩ ተገላጿል ?
4. 2ኛ ጢሞቴዎስ 3:10-12 ሐዋርያው ጳውሎስ ያለፈበትንና የሚያልፍበትን መከራ የሚያስረዳ ሀሳብ ምንድን ነው?

5. በ1ኛ ጢሞቴዎስ 2:1-2 ላይ ለሰዎች ሁሉ ለነገስታትና ለባለ ሥልጣናት ሁሉ ጸሎትና ምልጃ ይደረግ ካለ በኋላ በጸሎትና በምልጃ በሚሆነው ሰላም ውስጥ የሚሆነውን እንደ ምክንያት ያቀርባል ። ይህ ምክንያት ምንድን ነው ?

6. 2ኛ ጴጥሮስ 3:11 ላይ ያለውን ሃሳብን ከ1ኛ ጢሞቴዎስ 2:1-2 ጋር በማዛመድ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ለአማኝ ሁሉ የተሰጠ ዋና ሕይወት መሆኑን አስረዳ/አስረጂ

7. የእውነተኛ መንፈሳዊ ህይወት ታቃራኒው ህይወት ምን ዓይነት ህይወት ነው? የዚህ ህይወት መጥፎነቱ ምንድ ነው? ተወያዩ።

ይህ ጥናት ይቀጥላል …

**መደምደሚያ**

እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ጠቅለል ባለ መልኩ ብናጤነው ለክርስቶስ የተሰጠ ፊጹም ሕይወት ማለት ነው። ይህም አማኝ የስጋ አምሮቱን በመንፈስ እየገደል በአንጻሩ ደግሞ ለመንፈስ እየተገዛ ፍሬ አፍርቶ የሚኖረው የሕይወት ዓይነት ነው (ሉቃስ 9:23)።

# ክፍል 3

ጥናት 10

ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት አስፈላጊ ነጥቦች

**ዓላማ**

ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት የሚያስፈልገንን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሰጠን ማስገንዘብ፣ የተሰጠንን በጸጋው ትምህርት አማካኝነት በማወቅ፣ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትን እየተለማመድን፤ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ላይ የሚጨመሩትን ማሳሰብ ነው።

**መግቢያ፡-**

**ምንጩ እግዚአብሔር መሆኑን ማወቅ፡-** 2ኛ ጴጥሮስ 1:3 ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት የሚያስፈልገንን ሁሉ ፤ እግዚአብሔር እንደ ሰጠን ያሳየናል ። እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ለመኖር ብቃት የሚሰጠን እራሱ እግዚአብሔር ነው።

**መጨመር፡-** 2ኛ ጴጥሮስ 1: 6-7 የእግዚአብሔር ኃይል ያስቻለንን/ የሰጠንን ያህል፤ ዕውቀትን ፣ ራስን መግዛትንና መጽናትን መሰረት አድርገን እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት እንድንጨምር ያዘናል ። እግዚአብሔርን የሚፈራ ፣ የሚወድና የሚጠማ ማንነት (እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት) ፤ ለወንድማዊ ፍቅርና መተሳሰብ መሰረት ነው ሲል፤ "ጨምሩ" ይለናል ።

**የእግዚአብሔር ጸጋ፡-** ቲቶ 2:12 እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት የጸጋው ትምህርት ውጤት መሆኑን ያሳየናል ። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ጥሪው በሚናገርበት ምዕራፍ 1:1 ላይ ፤ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት የእውነተኛ መንፈሳዊ እውቀት ውጤት መሆኑን ያሳየናል ። የእምነት ትምህርት ዓላማ ፤ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትን ማጎልበት እንደ ሆነ ያስታውቀናል ።

## *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ዘፍጥረት 5፡ 24 ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አድርጐ እንደ ነበረ ይነግረናል። አካሄዱን የሚል ቃል ምንን የሚገልጽ ቃል ነው ? "አካሄድን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግስ" ማለት ምን ማለት ነው?
2. እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ፤ አካሄድን ከእግዚአብሔር ጋር ለማድረግ ምን ዓይነት አስተዋጽኦ አለው? ይጠቅማል ?
3. 2ኛ ጴጥሮስ 1:3 ያለው ሃሳብ ስትመለከት/ስትመለከቺ ስለ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ምን ትረዳለህ/ትረጃለሽ ?
4. በ2ኛ ጴጥሮስ 1:6-7 ላይ የተጠቀሱትን በቅደም ተከተል በማስቀመጥ፤ አንዱ ከሌላው ጋር ያለውን ግንኙነት አስረዳ። እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት በክፍሉ ውስጥ እንዴት እንደ ተቀመጠ የተረዳህውን/ሽውን አካፍል/ይ።
5. በቲቶ 1:1 እና በምዕራፍ 2:12 መካከል ያለው ሀሳብ የሚገናኘው እንዴት ነው? ክፍሎቹ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ሰለ ሚገኝበት መንገድ ምን ያሳዩናል?
6. በ1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡ 7 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ያዘዘው ምን እንዲያደርግ ነበር? ከዚህ አንተ/አንቺ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መለማመድ ምን እንደሚጠይቅ ምን ተገነዘባለህ/ልሽ ?
7. ይህ ህይወት ከሉቃስ 9:23 ጋር ምን ግንኙነት አለው?

## *መደምደሚያ*

የእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ምንጩ ጌታ ሲሆን አማኝ ደግሞ ክርስቶስን ለመምሰል በመጨመር ሕይወት ሊተጋ እንደሚገባው እንገነዘባለን።

# ክፍል 3
# ጥናት 11
# እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትን መለማመድ

**ዓላማ**

እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትን መለማመድ ታላቅ ዋጋ እንዳለው በማስገንዘብ፤ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት "ኑሮዬ ይበቃኛል" የሚል ልቦና እንደሚጠይቅ ማሳሰብና እራሳችንን ለዚህ ታላቅ ልምምድ ማነሳሳት ነው ።

**መግቢያ**

**ራስን ማስለመድ፡-** 1ኛ ጢሞቴዎስ 4:7 እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትን ራስችንን ማስለመድ እንደ ሚገባን ያሳስበናል ። እግዚአብሔርን ከማይፈሩ ፣ ከማይወዱና ከማይጠሙ ተግባራቶችና ሁኔታዎች ማራቅ ለልምምዳችን ቁልፍ የሆነ ውሳኔ መሆኑን ያስገነዝበናል።

እግዚአብሔር በሰጠን ኃይል ፣ በትምህርቱ ጉልበት የምንለማመደውን ፤ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት እያሰብን 1ኛ ጢሞቴዎስ 4:8 እና ምዕራፍ 6:6 እንመለከታለን ።

- ምዕራፍ 4፡ 8 የእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ልምምድ ለአሁኑ ለሚመጣውም ዘመን የሚጠቅም ልምምድ መሆኑን ፤ አካልን ለማጎልበት ከሚደረግ አካላዊ እንቅስቃሴ ጋር እያመሳከረ ያሳየናል ። እግዚአብሔርን መፍራት ፣ መውደድና መጠማት ያለውን የዘላለም ተሰፋ ያስገነዝበናል ።
- ምዕራፍ 6:6 ኑሮዬ የበቃኛል ላለ ፤ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይውት ትርፍ (ዋጋው የከበረ) መሆኑን ይነግረናል ። ምድራዊ ሃብት ለመሰብሰብ ከሚደረግ ጥረትና ምኞት በላይ ፤ እግዚአብሔርን መፍራት ፣ መውደድና መጠማት መለማመድ ትርፋማ ሕይወት ነው ይለናል ።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. 1ኛ ጢሞቴዎስ 4:8 የአካል ብቃት ልምምድን ፣ ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ልምምድ መገለጫ ሆኖ ቀርቧል ። የአካል ብቃት ልምምድ የሚጠይቀንን መሰጠትና ያለውን ጥቅም በመዘርዘር ፤ ከእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ልምምድ ጋር ያለውን አንድነት እና ልዩነት ተወያዩ።
2. 1ኛ ጢሞቴዎስ 6:6 "ትርፍ ነው" የተባለው ምንድን ነው ? (መደበኛው አዲስ ትርጉም)
3. በኑሮ መርካት ማለት ምን ማለት ነው ? ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ልምምድ የሚጠቅመው እንዴት ነው ?
4. 1ኛ ጢሞቴዎስ 6:9-10 ያለው ሃሳብ ፤ በኑሮ መርካት ከሚለው ሃሳብ በመጻርረ ተጠቅሷል ። ይህ በተቃርኖ የተገለጸው ኑሮ ፤ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትን እንዳንለማመድ እንቅፋት የሚሆነው እንዴት ነው?
5. እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት እግዚአብሄርን የመፍራት ፣ የመውድድ እና የመጠማት ሕይወት ነው ። እንዲህ ዓይነቱ ሕይወት በግላችን በምናደረጋቸው የጥሞና ጊዜያችን ይንጸባረቃሉ ። በኑሮ መርካት ለጥሞና ጊዜ ለመስጠት የሚረዳን እንዴት ነው? በተጨማሪ ይህ ሃሳብ በማቴዎስ 6:33 እይታ እንመዝነው ።
6. የእወነተኛ መንፈሳዊ ህይወት ተግዳሮቶች ምንድ ናቸው? እንዴትስ ልናሸንፈው እንችላለን?
7. አጠቃላይ ስለ እውነተኛ መንፈሳዊ ህይወት ምን ተረዳችሁ? አካፍሉ? ለለውጥ እንጸልያለን።

***መደምደሚያ***

እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትን እንደ ስፖርተኛ ዘወትር መለማመድ ያሻል።

# ክፍል 4
# ጥናት 12
# አንደበት

**ዓላማ**

የአንደበት ቃል ያስተሳሰብ መገለጫ መሆኑን በማሳየት፤ በአንደበታችን በአግባቡ ለመጠቀም አስተሳሰባችን ላይ መስራት እንደሚገባ ማሳየት።

**መግቢያ**

የአስተሳሰብ ዓለም ግልጽ ሆኖ የሚታየው በአንደበት ቃል ነው ። ዝም ያለ ሰው ፤ እንደ ተከደነ ድፍን ሳጥን ውስጡ አይታወቅም ። የሚያስበው ፣ የሚያውቀውና የማያውቀው አይለይም ። ምሳሌ 17:28 እንደሚከተለው ይላል "አላዋቂ እንኳ ዝም ቢል ጠቢብ ፣ አንደበቱንም ቢገዛ አስተዋይ ይመስላል "። ስንፍናም ጥበብም በአንደበት ቃል ይገለጻል ። የመክብብ መጻሐፍ በምዕራፍ 3:7 ላይ "ለዝምታ ጊዜ አለው ፤ ለመናገርም ጊዜ አለው " እንደሚል ጊዜን ጠብቆ ዝም ማለትም ጊዜን ጠብቆ መናገርም ብልህነት ነው ። ዝም ማለት ብቻ ሳይሆን መናገርም ወርቅ ነው ። አንደበት እንደ ሚያጠፋ ፤ አንደበት ያለማል ። አንደበት እንደ ሚያፈርስ ፤ አንደበት ይገነባል ። አንደበት እንደ ሚረግም ፤ አንደበት ይባርካል ። አንደበት እንደ ሚያዋርድ ፤ አንደበት ያስከብራል ። የአንደበት ኃይል ተረድቶ ፤ በአግባብ ሊጠቀምበት እንዲችል የሚገዛው ፤ "ከተማን ከሚገዛ" ይበልጣል ። አንደበት የህይወት ወይም የሞት ምንጭ ሊሆን እንደሚችል ቃሉ ያስተምረና (ያዕቆብ 3፡ 11)::

በዚህ የመጻሐፍ ቅዱስ ጥናት ዝግጅት ውስጥ በቅድሚያ፤ አንደበት የውስጥ መስኮት መሆኑና ውስጥን ማቅናት አንደበትን ለማቅናት ነው የሚል ሃሳብ እንመለከታለን። ቀጥሎም አንደበትን በመልካምና በክፉ ፍሬው እንዳኘዋለን። በመጨሻም፤ ስለ አንደበት የተሰጡትን ምክሮችና ምሳሌዎች እንዘረዝራለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በማቴዎስ 12 ፡ 33-37 ባለው የንባብ ክፍል ውስጥ የዛፍና የፍሬው ምሳሌነት የቀረበው ምንን ለማሳየት ነው?

2. መልካም መናገር አትችሉም የሚላቸው ወይም አለመቻላቸው ከምን የተነሳ ነው?

3. ከአፍ የሚወጣ አስቀድሞ በየት የነበረው ነው? ይህ ደግሞ ስለ አንደበትና ስለ ማንነት ምን ያስተምረናል?

4. በማቴዎስ 12 ፡ 33 -37 መሰረት ፤ ለንግግራችን ትኩረት መስጠት ያለብን ለምድን ነው?

5. በማቴዎስ 15 ፡ 18-19 ያለው ሃሳብ ፤ በማቴዎስ 12 ፡ 33 -37 ካለው ጋር እንዴት ይነጻጸራል?

6. በሁለቱም የንባብ ክፍሎች ፤ የአንደበት ቃል ፤ የልብ ጉዳይ መሆኑን ስናይ መጠንቀቅና መስራት ስለሚገባን ጉዳይ ምን እንማራለን?

7. ስለ አንደበት ምሳሌ መጽሐፍ ብዙ ይናገራል። ሁለት ወይም ሶስት ጥቅሶችን በመጥቀስ ተወያዩ።

8. አንደበት ጥቅም አለው? ካለው መቼ ነው ጥቅም የሚኖረው? ያዕቆብ 3:11ን በማንበብ ተወያዩ።

***መደምደሚያ***

አንደበትን በመግራት ከአደገኛነቱ ይልቅ በጨው የተቀመመና ለሚሰሙት ጸጋን የሚሰጥ ንግግር እንዲፈልቅበት ማስገንዘብ ለአማኝ አስፈላጊ ነው።

# ክፍል 5

# ጥናት 13

# የመንፈስ ፍሬ

ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም (ገላትያ 5፡22)

**ዓላማ**

ቅዱሳን የመንፈስ ፍሬን በማፍራት ክርስቶስን የመምሰል ህይወት እየተለማመዱ እንዲያድጉ ለማሳሰብ።

**መግቢያ**

ይህ ጥናት የተመሰረተው በገላትያ 5፡22 ክፍል ላይ ነው። ሐዋርያው ይህን መልዕክት ለገላትያ ሰዎች ለመጻፍ ያስገደደው ዋነኛው ነገር መዳን በክርስቶስ ማመን ብቻ ሳይሆን የተለያየ የብሉይ ኪዳን ሥርዓቶችን መጠበቅም አስፈላጊ እንደሆነ የሚያምኑ አይሁድ ክርስትያኖች ስለነበሩ እነዚህን ሀሰተኛ መምህራንን መስመር ለማስያዝ ነው፡፡ ሐዋርያው በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ሶስት የሚያነሳቸው አበይት ጉዳዮች አሉ። አንደኛ ህግን በተመለከተ ነው፡ ሁለተኛው የስጋ ስራን በተመለከተ ሲሆን፡ ሶስተኛው ጉዳይ ደግሞ በዚህ ጥናታችን የምናተኩርበትን የመንፋስ ፍሬን በተመለከተ ነው።

ራሳችንን ለክርስቶስ ባስገዛን መጠን መንፈስ ቅዱስ በህይወታችን የመንፈስ ፍሬን እንድናፈራ ይረዳናል፡ የመንፈስ ፍሬ ደግሞ በእኛ ውስጥ የሚገለጥ የክርስቶስ ባህርይ ከመሆኑም ባሻገር የክርስቶስን ማንነት ለዓለም እንድናሳይ ትልቅ ጉልበት ይሆነናል። በአጠቃላይ የመንፈስ ፍሬ ኢየሱስ ማን እንደሆነ የሚገልጥ ክርስቶስን የመምሰል ባሕርይ ነው።

**ማብራሪያ**

ፍሬ ማፍራት ክርስቶስን በህይወት የመግለጥ ትልቁ ሂደት ነው። ማንኛውም ፍሬ የተገኘበት ተክል የዚያ ተክል ማንነት መገለጫ እንደመሆኑ መጠን እንዲሁ እኛ ደግሞ የክርቶስ አካል ብልቶች ስለሆን የክርስቶስ እውነተኛ ባህሪ ውበት በእኛ ህይወት ውስጥ ፍሬን በማፍራት መታየት አለበት።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው በህይወታችን የክርስቶስን ማንነት የሚገልጠውን ፍሬ ስናፈራ በ እኛ ውስጥም ይህን ፍሬ ሰዎች ሲመለከቱ እግዚአብሔርን ማክበር ይጀምራሉ።፡ በማቴ 5፡16፣ መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን

እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።" ይላል።

የመንፈስ ፍሬን በተመለከተ በመጀመርያው ጥናታችን ላይ የምናጠናው ጥናት በገላትያ 5፡22"የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ እና ሰላም ...የሚባሉትን ሶስቱን የመንፈስ ፍሬዎችን ይሆናል፡

**ፍቅር**

ፍቅርን ስናስብ ማስተዋል ያለብን አንድ ትልቅ ቁም ነገር አለ። የፍቅር ዋናው ጽንስ ሀሳብ በእግዚአብሔር ዘንድ ነው፤ ምክንያቱም ፍቅር ከእግዚአብሔር የመነጨ ባህርዩ ስለሆነ ነው። 1ዮሐ 4፡8 ይህን ያረጋግጣል "እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።" እንግዲህ ይህን አጋፔ የሆነውን ትልቅ ፍቅር እግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ኃጢአተኛ ለሆነው ለሰው ልጅ ያለ ልክ ገለጠው (ዮሐ 3:16)። ሮሜ 5፡8" ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።"

አጋፔ ፍቅር፡- "አጋፔ" የሚለው ቃል የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም በራስ መውደድ ላይ ያልተመሰረተ ጥልቅና የማይለወጥ ፍቅር በማለት ያብራራዋል። ይህም ፍቅር እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያሳየው መለኮታዊ ፍቅር እንደሆነ በዮሐ 3፡16 ላይ እንዲህ በማለት በግልጥ ተቀምጧል፡ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።"

እንግዲህ አማኝ ከግዚአብሔር በልጁ በኢየሱስ በኩል የፈሰሰውን ወይም ልክ የለለውን ፍቅር ምላሽ የሚሰጥበት እንዲሁም በውስጡ ያለውን ፍቅሩን ለእግዚአብሔር የሚገልጥበት ትልቁ መንገድ ፍቅር የተባለውን የመንፈስ ፍሬ በህይወቱ እያፈራ ሲሄድ ነው። አማኝ ይህን ፍሬ በህይወቱ እያፈራ ሲሄድ እግዚአብሔርን ይወዳል፤አጠገቡ ያለውን ባልንጀራውን ይወዳል እንዲሁም የምስራቹን ወንጌል በማብሰር በድኅነት ስራ ላይ ባለው ተጋድሎ ዋጋን በመክፈል ቁርጠኝነትን ያሳያል።

**ደስታ**

በመሰረቱ ደስታን መፈለግ ስህተት አይደለም። ነገር ግን በዚህ ደስታን የመፈለግ ሂደት ውስጥ የሚፈጸሙት ተግባራት ግን የባሰ ደስታን ሲያጨልሙ ይስተዋላሉ። በዚህ በገሀዱ አለም ደስታን ፍለጋ ብዙ ገንዘብ ይፈሳል። ነገር ግን አለማችንን ስንመለከት በጭንቅና በስቃይ እየባሰባት ሄዷል። ከዚህም ጋር በተያያዘ አንዳንድ ሰዎችም ለዚህ ስቃይ እረፍት ማግኛ

መንገድ መስሏቸው ራስን ወደ ማጥፋት የደረሱ ቀላል ቁጥር አይደለም። 1ጢሞ 6፡10 “ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፥ አንዳንዶች ይህን ሲመኙ፥ ከሃይማኖት( ከእምነታቸው) ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ ይላል።”

እውነተኛ ደስታ ሊመጣ የሚችለው ግን በጌታ ኢየሱስ በሆነው የድኅነትሥራ ላይ ሲመሰረት ብቻ ነው። ፊሊ 4፡4 “ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ፤ ደግሜ እላለሁ፥ ደስ ይበላችሁ” ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ህይወታችን ሲገባ እውነተኛ እና የሚገለጥ ደስታ ይዞ ይገባል። ይህም ደስታ የሚለካው እግዚአብሔር በላከው በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ ላይ የተመሰረተ በማመን ውጤት ላይ የመንፈስ ቅዱስ ክንዋኔ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር በሮሜ 15፡13 እንዲህ ይላል፡ “የተስፋ አምላክም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተስፋ እንድትበዙ በማመናችሁ ደስታንና ሰላምን ሁሉ ይሙላባችሁ።” የዚህ የደስታ መሰረታዊ ምንጭ ደግሞ እግዚአብሔር ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳችን በአጽንኦት ይነግረናል (ፊል 4፡4፣ መዝ 16፡11፣ ዮሐ 20፡20)። የዚህ ደስታ ምንጭ አንቀሳቃሽ ሞተሩ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ይህን ደስታ የተባለውን የመንፈስ ፍሬ በህይወታችን እንድናፈራ ይረዳናል። ይህም ፍሬ በህይወታችን እየበዛ ሲሄድ ደግሞ ከፊታችን ያለውን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ የተዘጋጀልንን ተስፋ እያየን እንድንጓዝ ግሩም የሆነ ብርታትን እየጨመረልን ይሄዳል (ሮሜ 14፡17፣ 1ተሰ 1፤6)።

**ሰላም**

በሁሉም አቅጣጫ በግልም ይሁን በቡድን በቤተሰብም ይሁ በሀገር ደረጃ ብዙዎች ሰላምን እንደሚፈልጉ እናስተውላለን።ነገር ግን ይህ ሰላም ፍጹም አለመሆኑን በዚህ በምንኖርበት አለም ውስጥ ከሚሆኑት ሁኔታዎች በመነሳት ነፍስን የሚያረካ ሰላም እንደሌለ በግልጥ እንረዳለን። መጽሐፍ ቅዱስም ስለዚህ የአለማችን ሰላም እጦት ከነምክንያቱ በምድር ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ በተመላለሰበት ወቅት ከዳግም መምጣቱ ጋር በማያያዝ በማቴ 24 በግልጥ ተናግሯል። እንግዲህ እውነተኛው ነፍስን የሚያረካ ሰላም የሚገኘው በአንድ መንገድ ብቻ ነው እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው ሰላም ብቻ እንደሆነ ያብራራል ፡፡ ምክንያቱም ኤፌ 2፡14 “እርሱ ሰላማችን ነውና”፣ ዮሐ. ወንጌል 14፤27 “ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም። ልባችሁ አይታወክ አይፍራም” ይላል።

እንግዲህ ይህ በእርሱ የተገኛው ሰላም በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በአማኞች ህይወት ውስጥ ፍሬ ማፍራት ይኖርበታል። ይህ ፍሬ በህይወታችን ሲገኝ ሁለት አበይት ክንውኖችን ለማድረግ መንፈስ ቅዱስ አቅም ይሰጠናል።

1. በእግዚአብሔር ሰላም እንወረሳለን ፊሊጵ 4፡7 "አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።
2. ምንም ምድራዊ ነገር ላይ ያልተመሠረት እርካታ በተሞላ ህይወት መኖር እንችላለኝ።
3. ለሌሎች ምስክር እንሆናለን ማለትም ሌሎች ወደ ጌታ እንዲመጡ አንዱ መንገድ ይሆናል።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ይህን ጥናት ማጥናት ለምን አስፈለገ?
2. በጥናቱ መግቢያ ላይ እንደተመለከተው ሐዋርያው ጳውሎስ በገላትያ ምዕራፍ 5 ላይ ያነሳቸው ሶስት አበይት ጉዳዮች ምን ምን ናቸው?
3. በ1ዮሐ 4፡8 በተመለከተ የፍቅር ዋና ጽንሰ ሀሳብ ማን ነው? ይህንን ፍቅር አንተ እንዴት ትገልጠዋልህ ?
4. የገሀዱን ዓለም ደስታ እና የመንፈሳዊውን አለም ደስታ በማነጻጸር ለጥናት ቡድንህ አብራራ።
5. ይህን ደስታ የሚባለውን የመንፈስ ፍሬ እንድናፈራ የሚረዳን ማን ነው? ምን ስናደርግ?
6. በዮሐ 14፡27 መሰረት አለም ሰላምን ትሰጣለች ብለህ ታስባለህ? አዎን ከሆነ መልስህ እንዴት? ይህ አለም የሚሰጠውን ስላም እና እውነተኛ በክርስቶስ የሚጋኘውን ሰላም በማነጻጸር ተወያዩ።
7. በማብራሪያው መሰረትአማኝ ይህን ፍሬ ማፍራት ሲጀምር በህይወቱ የሚከናወኑ ነገሮች ምን ምን ናቸው ብለህ ታስባልህ?
8. የሶስቱንም መንፈሳዊ ፍሬዎች አንድነት እና ልዩነት አብራሩ።

9. ዛሬ ለእውነተኛ ፍቅር ደስታ እና ሰላም እንጸልያለን። እንዲሁም በዚህ ሳምንት አንድ በጌታ ላልሆነ ሰው ማካፈል እንችላለን?

**መደምደምያ**

አንድ ሰው ድነትን በክርስቶስ ኢየሱስ ካገኘ በኋላ የመንፈስ ፍሬን ማፍራት ተከታዩ በህይወቱ ውስጥ እየታየ መሄድ ያለበት ትልቁ ጉዳይ ነው። አማኝ ይህን ፍሬ በህይውቱ እያፈራ ሲሄድ ክርስቶስን የመምሰል ህይወት ከመኖሩም ባሻገር ከቅዱሳን ጋር ጤናማ ግንኙነት ይኖረዋል፤ አገልግሎቱ ጤናማ ይሆናል እንዲሁም ከቤተክርስትያን ጋር ጤነኛ ግንኙነት ይኖረዋል። እንግዲህ ይህን ፍቅር ፤ደስታ እና ሰላም የሚባሉት መልካም የመንፋስ ፍሬ ማፍራት ያንድ ወቅት ጉዳይ ሳይሆን አማኝ በህይውቱ ሙሉ እየተለማመደው የሚሄደው ሂደት መሆኑን አማኝ መዘንጋት የሌለብት ጉዳይ ነው።

# ክፍል 5

# ጥናት 14

## የመንፈስ ፍሬ

## ትግስት፣ ቸርንት ፣በጎነት (ገላትያ 5፡22)

### ዓላማ

ቅዱሳን በህይወታቸው ተግዳሮቶች ሲገጥማቸው እና ፍጹም ደስታን ለማግኘት ትዕግስትን ከማሳየት ባለፈ የቸርነትን እና የበጎነነት የመንፈስ ፍሬዎችን በየቀኑ እያፈሩ እንዲሄዱ ለማበረታታት።

### መግቢያ

የመጀመሪያዎቹ የመንፈስ ፍሬዎች ማለትም ፍቅር ፤ደስታ እና ሰላም የመንፈሳዊ የውስጥ ክፍሎቻችን ሲያሳዩ ትዕግስት፤ ቸርነት እና በጎነት ደግሞ ከሰዎች ጋር ባለን ግንኙነት ውጫዊ መገለጫዎቻችን ናቸው።

### ትዕግስት

ይህ የመንፈስ ፍሬ አማኝ ፈተና በህይወቱ በሚጋጥመው ጊዜ ራሱን እንዲገዛ የሚረዳው ትልቅ መሳርያ ነው። ትዕግስትን በምናስብበት ጊዜ ትዕግስትን የሚያሳጣ እንዲሁም በመታገስ ውስጥ ያለንን ጥንካሬ የሚሸረሽር ነገር በገሀዱም እና በመንፈሳዊውም አለም እንዳለ ግልጥ ነው። ከፊት የሚታይ ተስፋ ከሌለ መጠበቅ ያዝላል፤ ያሰለቻል፤ ያደክማል። በአጠቃላይ ተስፋችን ያጨልማል። የምንጠብቀው ተስፋ ሲኖረን ግን ምንም መከራ ቢበዛም ትዕግስት ተስፋ ወዳደረግነው አቅጣጫ የሚወስደን ጽናት እና አቅም ከመሆኑም በላይ ለመንገዳችን ደግሞ ስንቅ ነው። ሮሜ 5፡3-4 እንዲህ ይላል “ነገር ግን መከራ ትዕግሥትን እንዲያደርግ፥ ትዕግሥትም ፈተናን ፈተናም ተስፋን እንዲያደርግ እያወቅን፥ በመከራችን ደግሞ እንመካለን”

ዛሬ እኛ አማኞች በጉጉት የምንጠብቀው ተስፋ አለን ይህም ተስፋ በመጽሐፍ ቅዱስ የተነገረለት የክብር ንጉስ የኢየሱስ ክርስቶስ በክብር መመለስ ነው። በዚህ ንጉሳችንን በመጠበቅ ሂደት ውስጥ ብዙ መከራ ስደት እና ስቃይ ከዚህ በፊት በእምንታቸው ምክንያት እንደደረሰባቸው አባቶቻችን ዛሬም ከፊታችን አለ። ነገር ግን ይህንን ተጋድሎ በድል ለመወጣት ትዕግስት የተባለውን የመንፈስ ፍሬ በህይወታችን ማፍራት ከሁሉም አማኝ

የሚጠበቅ ትጋት ነው ። ዕብ 6፡11-12 “በእምነትና በትዕግሥትም የተስፋውን ቃል የሚወርሱትን እንድትመስሉ እንጂ ዳተኞች እንዳትሆኑ፥ ተስፋ እስኪሞላ ድረስ እያንዳንዳችሁ ያን ትጋት እስከ መጨረሻ እንድታሳዩ እንመኛለን” ብሎ ይመክረናል።

## ቸርነት

ቸርነት የምንለው የመንፈስ ፍሬ ከበጎነት የመንፈስ ፍሬ ጋር በጣም ከመዛመዱ የተነሳ ብዙ ጊዜ ለመለየት በጣም ይከብዳል። ይህን የመንፈስ ፍሬ ስንመለከት የሰውን የባህሪ ልስላሴ፤ ርህሩህነቱን እና መልካምነትን የሚያመለክት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በኤፌ 4፤32 “እርስ በርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፥ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ” ብሎ ያዘናል። ቸርነትን ስናስብ እኛ ራሳችን በራሳንች ወደ ህይወታችን ጎትተን የምናምጣው ሳይሆን ቲቶ 3፤4፣ ኤፌ 2፡6- እንደሚናገረው የእውነተኛ ቸርነት ምንጩ እግዚአብሔር ነው። ቸርነት ፍቅር ባለው ሰው ህይውት ውስጥ ይገለጣል። ስለዚህ ቸርነት የፍቅር መለለጫ እንደሆነ እንረዳለን።ይህንኑ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ በማለት ይገልጠዋል፡” ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል “ (1ቆሮ 13፤4)። በመዝሙር መጽሐፍ ብዙ የተደጋገመው ቃል የጌታ ቸርነት ነው።

## በጎነት

በመሰረቱ በጎነትን ከቸርነት ነጥሎ ማየት አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም አንዱ ያንዱ መገለጫ ስለሆነ ነው። እንግዲህ በጎነትን ስናስብ ቸርነትን በተግባር ይገልጠዋል። ይሄን የመንፈስ ፍሬ ስንመለከት በ2ቆሮ 8፡1-5 ያለውን የመቄዶንያን ቤተክርስትያንን ያስታውሰናል። የመቄዶንያን ቤተክርስትያን ቅዱሳንን ስናስብ ቸሮች ስለ ነበሩ የድህነታቸው ጥልቀት ገንዘብን በመስጠት ያደረጉትን በጎ ተግባር አልገታቸውም፡ ይልቁንም እንደ ዓቅማቸው መጠን ከዓቅማቸውም የሚያልፍ እንኳ ወደው እንደ ሰጡ ሐውርያው መስክሮላቸዋል። ይህ የመንፈስ ፍሬ ቅዱሳኑን ወርሶ እንደነበር ሐዋርያው እራሱ ካሳየው መንፈሳዊ ፍሬ በደንብ ተገንዝቧል።

እግዚአብሔር በባህሪይው ቸር ስለሆነ በጎ የሆነው ተግባሩ አንድያ ልጁን ክርስቶስን በመስጠት ገለጠው። ስለዚህ በጎ የማድረግ ጅማሬው እግዚአብሔር እራሱ ነው (ያዕ 1፡17፣ 2ጴጥ 1፤2-3)።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን በጎነት ቸር የሆነ ሰው ተግባር መገለጫ ባህሪይው ሲሆን

ውጤት እንዳለውም ይነግረናል “ነገር ግን በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋናና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል፥” (ሮሜ 2፡10)።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በጥናታችን መግቢያ ላይ ትዕግስትን እንደ መሳርያ ተብሎ ተጠቅሷል። የዚህ የመንፈስ ፍሬ መሳሪያነትን ለጥናት ቡድንህ አብራራ።
2. ሮሜ 5፡3-4 በማንበብ ትዕግስትን ከመከራ ጋር በማያያዝ እንዴት ትገልጠዋለህ? ምን ይጠቅማል?
3. ዕብ 6፡11-12 መሰረት በማድረግ ትዕግስት ከተስፋ መውረስ ጋር ያለውን መጣመር ለጥናት ቡድናችሁ አስረዱ።
4. ቲቶ 3፡4 እና ኤፌ 2፡6 በማንበብ የቸርነት ምንጭ ማን እንደሆነ ተወያዩ።
5. 1ቆሮ 13፡4 መሰረት በማድረግ የፍቅርና የቸርነትን ግንኙነት በመግለጥ ለጥናት ቡድናችሁ አስረዱ።
6. በ2ቆሮ 8፡1-5 ሐዋርያው ስለመቆዶንያ ቤተክርስትያን መልካም ነገር ይናገራል በዚህ የሐዋርያው ንግግር ውስጥ ቸርነት እና በጎነት እንዴት እንደተገለጡ ያለህን መረዳት አብራሩ።
7. ያዕ 1፡17 እና 2ጴጥ 1፡2-3 መሰረት ስለ በጎነት ተወያዩ
8. ሮሜ 2፡7-10 በማንንበብ በጎ የሚያደርጉ እና ክፉ የሚያደርጉ ሰዎች በህይወታቸው የሚያመጣውን ውጤት ለጥናት ቡድናችሁ አስረዱ።
9. እነዚህን ሶስቱን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች እንዴት ለወንጌል ስርጭት መጠቀም እንችላለን? ለዚህም ዛሬ እንጸልያለን።

***መደምደምያ***

ትዕግስት፤በጎነት እና ቸርነት በውጭ የሚታዩ የውስጥ የመንፈስ ፍሬ ነጸብራቅ ናቸው። እነዚህ የመንፈስ ፍሬዎች በቅዱሳን ህይወት ውስጥ መፍራት ያለባቸው ለመሁኑ አጠያያቂ አይደለም ምክንያቱም ለአንድ አማኝ በግል ህይወቱ፤ እርስ በርስ ባለ የቅዱሳን ግንኙነቱ እና በአገልግሎቱ ፋይዳቸው የላቀ ስለሆነ ነው። ስለዚህ ቅዱሳን እነዚህን የመንፈስ ፍሬዎች በህይወታቸው በማፍራት በእግዚአሔር የመንግስት ሰራ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ትልቅ አስተዋጽኦ ስላላቸው አማኝ በየግል ህይወቱ ማፍራት የሚጠቀምበት እውነትኛ የመንፈስ ፍሬዎች ናቸው።

# ክፍል 5
# ጥናት 15
# የመንፈስ ፍሬ
# እምነት፣ የውሃት፤ ራስን መግዛት

(ገላትያ 5፡22)

## ዓላማ

አማኞች እምነትን፣የዋሃትን እና ራስን መግዛት የተሰኙትን ፍሬዎች በህይወታቸው በማፍራት ክርስቶስን የሚመሰል ህይውት እየተለማመዱ እንዲያድጉ ለማስገንዘብ።

## መግቢያ

እምነት የዋሃት፤ እና ራስን መግዛት እነዚህ ሶስቱ የመንፈስ ፍሬዎች በገላትያ 5፤22 ላይ ከተጠቀሱት ዘጠኝ የመንፈስ ፍሬዎች መህል የመጨረሻዎቹ ናቸው። እነዚህ የመንፈስ ፍሬዎች በአማኙ ህይወት እየተገለጡ ሲሄዱ ለአማኙ መንፈሳዊ እድገትና ጥንካሬ ከፍተኛ አስተዋጽዎ አላቸው።

## እምነት

የተለያዩ የእምነት ዓይነት ዓይነቶች ቢኖሩም በዚህ ክፍል ትኩረት የምንሰጠው ስለ መንፈስ ፍሬ እምነት ነው። የእምነትን ጉዳይ በማስተዋል ካሰብን እግዚአብሔርን ከእምነት ነጥለን ማየት አንችልም። ከክርስቶስ ጋር ያለው መሰረታዊ ግንኙነታችን የተመሰረተው በእምነት ላይ ነው። ስለዚህ እምነት በልጁ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ላለን ግንኙነት መሰረት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ አስረግጦ ያስረዳናል። መጽሐፍ ቅዱስ እምነትን በሚያስደንቅ የቃል አፈታት እንዲህ በማለት ይገልጠዋል። እምነት የዳንበት እና በየቀኑ የምንኖርበት የክርስትና ኑሮ ነው። ዕብ 11፡1 “እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው። ዕብ 11፡6 “ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያስፈልገዋልና”።

ከዚህ በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስ እምነትን በተመለከተ በቀድሞ የእምነት አባቶቻችን ህይወት ውስጥ የነበረውን አስደናቂ የህይውት ጉዞ በሚገርም ሁኔታ በዕብ 11 ሙሉ ምዕራፍ ላይ ይተርካል። እንግዲህ እምነትን ስንመለከት ከታማኝነት ጋር ሳይነጣጠል ተጣምሮ የሚሄድ መሆኑን ላፍታም መዘንጋት የለበትም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ዕብ 11፡1 “እምነትም ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው።”

ስለዚህ አማኝ ለዚህ ለታመነው ጌታ ታማኝነት ትልቅ ስፍራ አለው። ታማኝነት ከስነ ምግባር ጋር ይያያዛል። ታማኝነት በአንድ አማኝ ህይወት ውስጥ በቃል እና በተግባር ሀላፊነት እንዲሰማው ያደርጋል። ስለዚህ አማኝ ጌታን በመምሰል ህይወት ውስጥ በመከራ ታማኝ፤ በፍቅር ታማኝ፤ቃልን በመጠበቅ ታማኝ፤በመታዘዝ ታማኝ እና አደራን በመጠበቅ ታማኝ በመሆን መኖር ይኖርበታል። ለዚህ ጉዳይ ዮሴፍ ዘፍ 37-48 እንዲሁም ሙሴ ዕብ 3፡5 ከብዙዎች መሀል ተጠቃሽ ናቸው።

**የውሃት**

ይህን የመንፈስ ፍሬ ስንመለከ የጭካኔ ተቃራኒ ሲሆን የደካማነት፤የበታቸኝነት እና የዝቅተኝነትም መገለጫ  አይደለም። የውሃት የሰላማዊ፤ የፍቅር እና የልከኝነት መገለጫ ህይወት መሆኑን ልብ ልንል ይጋባናል። የውሃት የመንፈስ ፍሬን ስንመለከት፤ ነግሮችን ሁሉ ለጌታ መተውንም ያሳያል። እንዲሁም፡-የሚከተሉትን ነገሮች ያመለክታል።

- ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛትን   ማቴ 11፡29
- የመማር ፈቃደኝነትን ያዕ 1፡21
- ርህራሄን ገላ 6፡1
- ከተንኮልም የራቀ ህይወት ሲሆን ነገሮች አለማጠምምንም ያሳያል።

**ራስን መግዛት**

በጌታ በየሱስ ያመኑ ቅዱሳን ከዳኑ በኋላ ራሳቸውን በመግዛት ህይወታቸውን እንዲመሩ የጌታ ሀሳብ ነው። ቲቶ 2፤11-13 “ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤ ይህም ጸጋ፥ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊ ምኞትን ክደን፥ የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፥ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል

**በምን መልኩ ነው ራሳችንን የምንገዛው?**

- ራስን መግዛት በብዙ መልኩ ልንመለከተው እንችላለን። ለምሳሌ አንደበትን በመግራት፤ የስጋ ስራን በመግደል፤ግዜን በአግባቡ በመጠቀም እና ክፉ ምኞትና ሀሳብን ባለማስተናገድ የመሳሰሉት ናችቸው። ከነዚህ ውስጥ ግን አንደበትን መግራት እና የሥጋን ስራ መግደል

እንደሚከተለው ለመግለጥ ተሞክሯል።

- **አንደበትን መግራት**:- *ያዕቆብ 3 ሙሉ ምዕራፍ ስንመለከት የአንደበትን አደገኛነት ግልጽ አርጎ ያሳየናል። እንግዲህ ቅዱሳን ከያቆብ መልዕክት እንደምንረዳው አማኝ አንደበቱን መግራት እንዳለበት በግልፐ ያስረናል። ምሳሌ 12፡19 የእውነት ከንፈር ለዘላለም ትቆማለች፤ ውሸተኛ ምላስ ግን ለቅጽበት ነው።*

- የስጋ ስራን መግዳል፤ በመሰረቱ በጌታ የዳነ አማኝ በዋጋ ስለተገዛ ከጌታ ሀሳብ ውጭ በስጋ ሀሳብ እየተመራ እንደወደደ የፈለገውን ማድረግ እንደማይችል መጽሐፍ ቅዱስ ይነገረናል።

**1ቆሮ 6፡19-20** *"ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።"*

ገላ 5፡17 *"ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን*

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. እምነት ስለተባለው የመንፈስ ፍሬ ያለችሁን ግንዛቤ ለጥናት ቡድናችሁ አካፍሉ።
2. እግዚአብሔርን ከእምነት ነጥለን ማየት እንችላለን? አዎ/ አይ ለምን?
3. ዕብ 11፡1 መሰረት በማድረግ የእምነትን ትርጉም ለጥናት ቡድንህ አስረዳ?
4. ዕብ 11 ላይ ከተጠቀሱት የእምነት አርበኞች በስማቸው በመጥቀስ በጌታ ላይ ስለነበራቸው አስደናቂ እምነት ተናገር።
5. መጽሐፍ ቅዱስን መሰረት በማድረግ በራስህ አባባል የውሃነትን እንዴት ትገልጠዋለህ?
6. በገላ 6፡1 ላይ የተጠቀሰውን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ስለየዋሃት የተረዳኸውን ለጥናት ቡድንህ አብራራ።
7. በቲቶ 2፤11-13 ላይ በመመርኮዝ ራስን መግዛት ከክርስቶስ መገለጥ ጋር በማገናዘብ ያላችሁን መረዳት ተነጋገሩ።

8. ራስን ስለመግዛት በጥናት መጽሐፉ ላይ ባሉት ሀሳቦች በተጨማሪ እናንተም የሚታውቁትን በማከል ከጥናት ቡድናችሁ ጋር ተወያዩ።

9. እነዚህን ሶስቱን የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች እንዴት ለወንጌል ስርጭት መጠቀም እንችላለን? ለዚህም ዛሬ እንጸልያለን።

***መደምደምያ***

አንድ ሰው የደህንነትን ወንጌል ክሰማ በኋላ በመቀጠል በሰማነው እውነት ላይ ያለው እምነትና ላመነው ደግሞ ምላሽ በመስጠት ሂደት ላይ እምነት ከፍተኛ ድርሻ አለው። በክርስቶስም ከዳንን በኋል እንኳን በዚህ ምድር ላይ የምንኖረው ኑሮ በክርስቶስ ላይ ባለው እምነት የምንኖረው ኑሮ ነው። የጌታ ቃል በገላ. 2፡20 እንዲህ ይላል “ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።”

እንግዲህ ይህ የመንፈስ ፍሬ ከየውሀትና ራስን ከመግዛት የመንፈስ ፍሬ ጋር በመቀናጀት ፍሬው በአማኝ ህይወት ውስጥ እየበዛ መሄድ እንዳለበት ቅዱሳን ለአፍታም መዘንጋት የለባቸው።

**ክፍል 6**

**ጥናት 16**

አብሮ ሰራተኛነት (የቡድን ሥራ Co-working)

## ዓላማ (አጠቃላይ)

እግዚአብሔር አባታችን **<u>በመለኮታዊ ድንጋጌው</u>** ሁሉን ነገር ያደረገው አብሮ በመሥራት ነው። ይህንን አብሮ የመሥራት መርሆ ደግሞ ከሰዎች ጋርም እንዲሆን አስተላልፏል። ከሰዎች ጋር በጋራ በመሥራት የተሳካልን እና ውጤታማ መሆን ያስፈልገናል። ለውጤታማ አብሮ ሰራተኝነት ልንጫወተው የሚገባንን ሚና ከእግዝአብሔር ቃል በመመልከት በአብሮ ሰራተኝነት ሂደት ውስጥ ልንወጣቸው የሚገቡንን ኃላፊነቶችን እንመለከታለን፤

## አጠቃላይ መግቢያ

ለብዙዎቻችን የቡድን ሥራ ወይም የአብሮ ሰራተኛነት የሚለው ሃሳብ እንግዳ የሆነ ሃሳብ ሳይሆን የዕለት ተዕለት የህይወታችን ክፍል ነው፤ በቤተሰብ ዙሪያ፣ በቤተ ክርስቲያን፤ ወይንም በሥራችን ገበታችንም ፤ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የየቀኑ ህይወታችን እና ኑሮችን ከሌሎች ሰዎች ጋር የተያያዘ መሆኑ ግልጽ ነው:: ልብ ብለን ካስተዋልነው ብቻችንን የምናደርገው ነገር በጣም ጥቂት ሲሆን፤ ዓይነቱና ደረጃው ይለያይ እንጂ አብሮ ሰራተኝነት (የቡድን ሥራ) ሁላችንንም የሚመለከት ጉዳይ ነው::

ከፍጥረት መጀመሪያ አንስቶ ስንመለከት እግዚአብሔር ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም ስለዚህም ረዳትን እንፍጥርለት ብሎ ፤ ወንድ እና ሴት አድርጓ እንደፈጠራቸው እናያለን (ዘፍ 2:18)። በተጨማሪም እግዚአብሔር የድነት ቃል ኪዳኑን ያደረገው ከሰዎች ጋር ነው። ለምሳሌ ከአዳም ጋር (ዘፍ 3:15)፣ከኖህ ጋር (ዘፍ 9:6)፣ ከአብርሃም ጋር (ዘፍ 12:1-4) ከዳዊት ጋር (2ሳሙ 7:10-16) እና ሌሎችም ናቸው። በድነት ቃል ኪዳኑም ፍጻሜ አብ፣ወልድ እና መንፈስ ቅዱስ በጠበቀ መልኩ በአንድነት ሠርተዋል (ኤፌ 1:1-23)::

ስናጠቃልለው አብዛኛውን የህይወታችንን ክፍል ከሌሎች ሰዎች ጋር እንድንጋራው ታስቦ የተፈጠርነው መሆኑን ከአካላችን ምሳሌ ማወቅ ይቻላል (ሮሜ 12፡1-8)። አንድ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል ብሎ ስለ ህብረት ያጠናክራል "...አንድ ብቻ ከመሆን ሁለት መሆን ይሻላል" (መክ 4:8)። እናም የሚያምርብን እና ውጤታማ የምንሆነው በተፈጠርንበት በዚህ ዓላማ መኖር ስንችል ነው፤

አብሮ የመሥራት ጥበብ ህይወታችን በሁሉም አቅጣጫዎች ስኬታም ሊያደርጉት ከሚችሉት ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው ነው። በቡድ ሥራ ወይንም በአብሮ ሰራተኛነት እኛም የምንጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። ስለዚህ ስለ አብሮ ሰራተኛነት ወይንም ስለ ቡድን ሥራ ሊኖረን የሚገባው እውቀት እና አስተሳሰብም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት ሊኖረው ስለሚያስፈልግ፤ይህንን ሃሳብ በእግዚአብሔር ቃል ልንመለከተው ያስፈልገናል።

የመወያያ ጥያቄዎች

1. በመግቢያ ሃሳብ መሰረት የዚህን ጥናት ዓላማ ተነጋገሩ
2. ዘፍ 1:26-27 በማንበብ እግዚአብሔር በመለኮቱ አብሮ ሠራተኛ ስለ መሆኑ ምን ይናገራል።
3. የሰው ልጅ በኃጢአት ከወደቀ በኋላ መልሶ ለማዳን ቃል ኪዳኑን ከማን ጋር አደረገ? ለምሳሌ ጥቀሱ ...
4. ኤፌ 1:1-23 በማንበብ በድነት ቃል ኪዳን ፍጻሜ የሥላሴን ድርሻ ተነጋግሩ።
5. 1 ቆሮ 3፡1-10 በማንበብ አብሮ ስለመሥራት ተነጋገሩ
6. ሮሜ 12:1-8 በማንበብ አብሮ ስለ መሥራት ከአካል ምሳሌ ምን እንማራለን? አንድ ላይ አብሮ መሥራት ምን ጥቅም አለው?
7. ከዛሬ ጥናት ምን ተማርን? ለቡድናችን እናካፍላለን።

መደምደሚያ

ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ እግዚአብሄር አብሮ ሠራተኛ እንደሆነ ከፍጥረትም ሆነ ከድነት ቃል ኪዳን ሂደት እንማራለን። አብሮ መሥራት ከፍተኛ ውጤት አለው። እኛም አብረን የምንሰራው ሥራ ሁሉ ለራሱ ክብር እና ለሰዎች ድነት ይሁን። አሜን::

## ጥናት 17

# አብሮ ሰራተኝነት በነህምያ አገልግሎት

## የንባብ ክፍል ነህ 2:11-20

### ዓላማ

በቡድን ሥራ ወይንም አብሮ በመስራት ልናገኝ የምንችለውን ውጤት ከፍ ያለ መሆኑን በማሳየት፤ የቡድን ሥራን ወይንም አብሮ ሰራተኛነትን ለማበረታታን ታስቦ የተዘጋጀ።

### መግቢያ

የቡድን ሥራን ወይንም አብሮ መሥራትን በምናስብበት ጊዜ በግላችን የምናደርገው እንቅስቃሴና ወይንም የምናከናውነው ሥራ ይተካዋል ማለት አይደለም። ይልቁንም የግል ችሎታችንን እና እውቀታችንን ከሌሎች ሰዎች ችሎታና እውቀት ጋር በማቀናጀት የማከናወን ወይንም የመስራት አቅማችንን ከፍ ማድረግ ማለት ነው። ስለዚህ በግላችን በምናደርገው እንቅስቃሴም ሆነ በምናከናውነው ሥራ ልናገኘው የማንችለውን በጋራ ወይንም በቡድን በመሥራት የምናገኘው ውጤት እጅግ የላቀ መሆኑ ብዙዎቻችን የምናምነው እውነት ነው።

ለምሳሌነት የአገራችንን የእግር ኳስ ተጫዋቾችን ከአገራችን ሮጮች ጋር በማነጻጸር ስንመለከት አገራችን በየዘመኑ የተደነቀ ችሎታ ያላቸውን የእግር ኳስ ተጫዎቾችን አፍርታላች። ይሁን እንጂ የአገራችን ብሔራዊ ቡድን ውጤት አልባ ከሆነ በርካታ ዓመታትን ተቆጥረዋል። በአንጻሩ ግን የአገራችን የአትሌቲክስ ቡድን በተለያዩ የዓለማት መድረኮች ላይ ለበርካታ ዓመታት አኩሪ ውጤቶችን በታሪክ መዝገብ ላይ እያስመዘገመ መጓዙን ቀጥሏል።

ለአገራችን የእግር ኳስ ቡድን ውጤት አልባነት የተጫዋቹ ችሎታ ወይንም ብቃት ማነስ ተደርጓ ብቻ ሊወሰድ አይችልም። ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ተጫዋቾቹ በየደረጃው ባሳዩት ችሎታ እና ብቃት ተመርጠው ነው የብሔራዊ ቡድን ተጨዋች የሚሆኑት። ይሁን እንጂ የግል ችሎታቸውና ብቃታቸው ሳያንስ ***እንደ <u>በቡድን የመጫወት ብቃት ማነስ</u>*** ለቡድናቸው ውጤት አልባነት ዋነኛ ምክንያት እንደሆነ የዚህ ጥናት አዘጋጅ ያምናል። በአንጻሩ የአገራችንን አትሌቶቻች

ያሸበረቀ ስኬት ሚስጢር የግል ችሎታና ብቃት ብቻ በመሆኑ በተወዳደሩበት መድረክ ሁሉ አንበሶቹ ሮጮች የሚል ቅጥያ ስም በተሰለፉባቸው መድረኮች አስጥቷቸዋል። ስለዚህ አትሌቶቻችን ***በግል ችሎታና ብቃት ላይ ብቻ የተመሰረተ ስኬትን*** መጨበጥ የቻሉ ሲሆን፤ በሌላው ወገን የእግር ኳስ ተጫዋቾቻችን የግል ችሎታን እና ብቃትን ሜዳ ውስጥ ይዘው ይግቡ እንጂ ያላቸው ችሎታ ከቡድኑ አባላት ችሎታ ጋር አቀናጅቶ ለውጤት መብቃት አልቻሉም። በዚህ ክፍል አብሮ ሠራተኛ መሆን ምን ያህል ጠቃሚ መሆኑን ከነህምያ መጽሐፍ ጥቂት ክፍሎችን በመወያያ ጥያቄዎች መልክ እናያለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች (መሪያችን እንደፈቀደ የሁለት ሳምንት መወያያ ጥያቄዎች ማድረግ እንችላለን)***

1. ነህም 2፡1-10 ስናነብ ቅጥሩን ለመስራት ራዕይ ያገኘው እንዴት ነበር? ይህስ ምን ያስተምረናል?
2. በነህ 2፡11 ነህምያ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለመሥራት ኢየሩሳሌም እንደደረሰ በቅድሚያ ያደረገው ነገር ምንድን ነበር? ለምን?
3. በነህ 2፡12-16 መሰረት አያሌ ሰዎች በዙሪያው እያሉ ነህምያ ለብቻው ያከናወናቸው ነገሮችን ምን ምንድን ናቸው?
4. በዚህ ክፍል ነህምያ ሊያከናውነው ያሰበውን ጉዳይ ሚስጢር አድርጓ ያቆየው እስከ መቼ ነበር ለምን?

ከዚህ በታች ያለውን በሚቀጥለው ሳምንት የምትመለከቱት ቢሆን መልካም ነው

5. እስከ አሁን በተመለከትነው ነህምያ ብቻውን የመስራት ብቃት እንዳለው የሚያመለክተው ምንድን ነው? ይሁን እንጂ ሁሉንም ነገር ብቻውን መስራት ይችላል ማለት ነው?
6. በነህ 2፡17-20 መሰረት ለካክናቱ ፤ ለሹማምንቱ እና ለሌሎችም ሰዎች የነገራቸው እና ያቀረበላቸው ጥያቄ ምንድን ነበር?
7. ነህምያ ሊያከናውነው ላለው የቅጥር ስራ ስኬት እና ውጤታማነት የወሰደው እርምጃ ምንድ ነው?
8. የሰዎች ምላሻቸው አወንታዊ የሆነበት ምክንያት ወይንም ሚስጢር ምንድን ነው?

9. ነህ 6፡15 ቅጥሩ በሃምሳ ሁለት ቀናት ውስጥ እንደ ተጨረሰ ያበስረናል። ለተገኘው አስገራሚ ውጤት ሚስጢር ምን እንደ ሆነ ነህም 3፡1-32 በማየት አስረዱ?(ሙሉ ምዕ. ማንበት የላባችሁም)
10. ራእይ የተቀበለው አንድ ሰው ቢሆንም በሥራው ሂደት ላይ ግን ሌሎች ሰዎች መሳተፋቸው ምን ያስተምረናል?
11. ከዛሬ ጥናት ስለ አብሮ ሰራተኛነት ወይንም ስለ ቡድን ስራ የተረዳችሁትን አንድ ነገር እንድትናገሩ እናበረታታለን።

## መደምደሚያ

ሁላችንም በግላችን የምናከናውነው ሥራ ወይንም የምናገኘው ራዕይ መኖሩ ምንም ጥርጥር የለውም። ቢሆንም ግን እግዚአብሔርም በቡድን ስራ ውጤታማዎች እንድንሆን እንደፈጠረን ቃሉ ይነግረናል። ስለዚህ ችሎታችንን እና እውቀታችንን ከሌሎች ሰዎች ችሎታና እውቀት ጋር በማቀናጀት መስራት ብንችል ግን ልናገኘው የምንችለው ስኬት ቀላል ግምት የሚሰጠው አይሆንም፡፡ በቡድን ሥራ ውስጥ ምናልባት የሥራው ወይም የአገልግሎቱን ራዕይ ያገኘው አንድ ሰው ብቻ ሊሆን ይችላል። ብቻውን ግን ሊሰራ አይችልም፡፡ በአብሮ ሰራተኝነት ልብ ጌታ እንዲባርከን ጥቂት ጊዜ በመውሰድ እንጸልያለን።

## ክፍል 7
## የአገልግሎት ጸጋ ስጦታን በመለየት ማገልገል
## ጥናት 18
## በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መካከል ያሉ የተለያዩ አማኞች ሁኔታ

የንባብ ክፍሎች (ማቴ.25:16-30፣ ሮሜ.12:3-8፣ 1ኛቆሮ. 12:4-30)

### ዓላማ

ከአገልግሎት አንጻር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ የተለያዩ አማኞችን ሁኔታ በመረዳት የትኛው ላይ እንዳለን ራሳችንን በመፈተሽ ለለውጥ መነሳሳት እንድንችል ነው።

### መግቢያ

በአብዛኛው በኢትዮጵያዊያንና ኤርትራዊያን ወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት መካከል እንደሚታየው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚገኙ ምዕመናን መካከል ያለአገልግሎት የተቀመጡት ቁጥር እንደሚበልጥ መገመት ይቻላል:: ይህንም አሳብ ለማንሳት የተፈለገው አማኞች ከጌታ የተቀበሉትን መንፈሳዊ ስጦታ፣ ችሎታና በትምህርት ያገኙትን እውቀት፣ ሙያና ልምምድ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ሌሎችን ለመጥቀምና ለመጠቀም (ለማገልገልና ለመገልገል) ዓላማ ሊያውሉት ስለሚገባ ነው። ይህንን ማድረግና ሌሎችም እንዲያደርጉ ማበረታታም ክርስቲያናዊ ግዴታችን እንደሆነ ለማስገንዘብ ነው:: ከዚህ በታች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የጸጋ ስጦታን በመረዳት እያገለገሉና እየተገለገሉ ያሉና ሊኖሩ የሚችሉ ልዩ ልዩ አማኞች የሚገኙባቸውን ቡድኖችና ሁኔታዎች ባጭሩ እንቃኛለን:፡

### ከአገልግሎት አንጻር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ የተለያዩ አማኞች ሁኔታ

**1. ስለጸጋ ስጦዎች ፈጽመው ማወቅ የማይፈልጉ**

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ወገኖች ካላቸው መንፈሳዊ እውቀትና መረዳት የተነሳም ሆነ፣ በጸጋ ስጦታዎች አጠቃቀምና አያያዝ ላይ ከሚታይ ግድፈትና ችግር እንዲሁም የግል ችግሮች ምክንያት ስለጸጋ ስጦታዎች ምንነት፣ ልዩነት፣ አንድነት፣ ዓላማና አጠቃቀም ማወቅ የማይፈልጉ፣ አእምሮቸውን ዝግ ያደረጉ፣ ግድ የማይሰጣቸውና ፍላጎት የሌላቸው አማኞች አሉ:: እንደዚህ ዓይነት አማኞችን የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ አገልጋዮችና ምዕመናን በእነርሱ ባለው የጸጋ ስጦታ የመገልገል እድል እንዲያገኙ እነርሱም በሌሎች አገልግሎት በእውቀት፣ በእምነትና በበጎ ህሊና እንዲገለገሉ ማብቃት ጠቃሚ መሆኑን

በመገንዘብ መንቀሳቀስ ያስፈልጋል።

2. **ያላቸውን የጸጋ ስጦታ ፈጽመው የማያውቁ**

እንደነዚህ ዓይነት አማኞች ስለጸጋ ስጦታዎች ምንነትና አጠቃቀም ሊያውቁ እንዲሁም በሌሎች አገልጋዮች ጸጋ የሚጠቀሙና በሌሎች ጸጋ ለመጠቀምም ፈቃደኛነት ሊኖራቸውና ጥረት ሊያደርጉ ይችላሉ:: ነገር ግን በሌሎች መገልገል እንጂ የራሳቸውን የጸጋ ስጦታ በማወቅና በመረዳት ለማገልገል ተነሳሽነት የሌላቸው ናቸው:: እንደዚህ ዓይነት አሉታዊ ተጽዕኖ ሊፈጠርባቸው ከሚችሉ የተለያዩ ምክንያቶች መካከል ስለራሳቸው ያላቸው ዝቅተኛ ስሜትና የተዛባ የማንነት ግንዛቤ ነው። ራሳቸውን የመቀበል ችግር አለባቸው። ለሌሎች ሊቀበሏቸው እንደማይችሉ ያስባሉ።

ባለባቸው የስነ ልቦና ችግርም ምክንያት እኔ እንደ ሌሎች አይሆንልኝም፣ አልችልም፣ ብቃትና ችሎታ የለኝም… የሚል የአስተሳሰብ ተግዳሮት ትግል ውስጥ ይገባሉ:: እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በሚከሰትበት ወቅት በተለይ በአገልግሎት ቆየት ያልንና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመሪነት፣ በመጋቢነት … እያገለግልን ያለን አገልጋዮች የጸጋ ስጦታቸውን መለየትና በጸጋቸው ማገልገል ያልቻሉትን ወገኖች ምክንያታቸው ምን እንደሆነ እንደሚገባ በመረዳት እንደ ችግሮቻቸው ዓይነት በእግዚአብሔር ቃል የመምከር፣ የማስተማር፣ የመጸለይና እንዲያገለግሉ የመርዳት ኃላፊነት አለብን::

3. **የጸጋ ስጦታቸውን አውቀው በተለያዩ ምክንያቶች እንዲሁ የተቀመጡ**

እንደነዚህ ዓይነቶቹ ደግሞ መንፈሳዊ ስጦታቸው ምን እንደሆነ የሚያውቁ ነገር ግን ከማገልገል ይልቅ እንዲሁ የተቀመጡ ናቸው። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ በተለያዩ ምክንያቶች ሊፈጠር ይችላል። አንዳንዶቹ ቀድሞ የነበራቸው መንፈሳዊ ግለትና ለአገልግሎት የነበራቸው መነሳሳት በመጥፋቱ ሁኔታው ሊከሰት ይችላል:: ምናልባትም ቀድሞ ይሰጡት የነበረው ትኩረት በሌላ ሲለወጥ ቀስ በቀስ ቀድሞ የነበራቸው መንፈሳዊ መነቃቃት እየጠፋ ሊመጣ ይችላል (2ኛዜና 29: 11)።

በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን እንደነበረው ባሉበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግጭት፣ አለመግባባትና መከፋፈል ሲፈጠር ከአገልግሎት ራሳቸውን ማግለላቸው አንዳንድ ወገኖች የጸጋ ስጦታወችን እንዳይጠቀሙ ያደርጋቸዋል። ሌሎች ደግሞ በመንፈሳዊ ሕጻንነት ውስጥ በመገኘታቸው ምክንያት የጸጋ ስጦታዎችን በአግባብ ያለመጠቀምና ያለመያዝ ችግር ይታይባቸዋል። በቤተ ክርስቲያን ኅብረት ለማገልገልና ለመገልገል ምቹ

ሁኔታ ሲጠፋና ምሳሌነቱ ላቅ ያለ የመሪነት ብቃት ያለው መሪ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲታጣም ብዙ ክርስቲያኖችን እንዳያገለግሉ የሚያደርጓቸው ሁኔታዎች ይፈጠራሉ። አንዳንድ ወገኖች ደግሞ ከሌላ ቦታና አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተዘዋውረው በመጡበት ወቅትም ሆነ በቆይታም የመያዝ መንፈስ ሲያጡና የእንግድነት ስሜት ሲፈጠርባቸውም እንዲሁ ሊቀመጡ ይችላሉ። ቤተ ክርስቲያን ምዕመኖቿን በየጊዜው በማስተማር፣ ወደ አገልግሎት ዘርፎች በመጋበዝ፣ በማበረታታት፣ እንግዶችን እንደሚገባ በመቀበልና፣ ቤተሰባዊነት እንዲሰማቸው የሚያደርጉ መንገዶችንም በመፍጠር በተሰጣቸው የጸጋ ስጦታ እንዲያገለግሉ ዕድል በመስጠት የጸጋ ስጦታቸውን እንዲጠቀሙበት መርዳት ይኖርበታል::

### 4. ያለ ስፍራቸው በመሆን የሚያገለግሉ

ሌላው የዘመኗ ቤተ ክርስቲያን ችግር የትክክለኛ ሰው በትክክለኛ ስፍራ አለመሆን ነው:: በተለይ የመድረክ አገልግሎትን የሚፈልጉና ጥሪያቸው ሳይሆን ስልጣንና ሌሎችን ጥቅማ ጥቅሞችን በማየት ብቻ ያለጸጋ ስጦታቸው የሚሰማሩና ወደ አገልግሎት የሚገቡ ጥቂት አይደሉም። አንዳንድ ጊዜ በወቅቱ በቤተ ክርስቲያ ውስጥ በቂ የሆኑ አገልጋዮች አለመኖርና አገልግሎቶችን እንዲሸፈኑ ሲፈለግና ጥረት ሲደረግ አገልጋዮች ያለስፍራቸው የሚሰማሩበት አጋጣሚም ከፍተኛ ሊሆን ይችላል : :

አንዳንዴ የአንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምዕመናን ግፊት፣ የማበረታቻ ቃልና የአገልግሎት ዕድልን ለሚፈልጓቸው ወገኖች መስጠት ራሳችንን ሁነን፣ የራሳችንን ተሰጥዖ በመረዳትና በትክክለኛ ስፍራችን እንዳናገለግል ትልቅ እንቅፋት ሊሆን ይችላል:: ሌላው ተጠቃሽ አሉታዊ የሆነው ምክንያት አንዳንድ አገልጋዮች በተለያየ ምክንያት ትክክለኛ አገልጋዮችን በልዩ ልዩ መንገዶችና ስልቶች ከአጠገባቸው እንዳይጠጉ ማግለል፣ ማራቅ፣ ማጥፋትና ወደ ሌላ አገልግሎት ዘወር ማድረግ ያለሥፍራቸው ሁነው የማገልገል ችግር ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋቸዋል።

### 5. በሥፍራቸው ሆነው ነገር ግን ያለስፍራቸው መሆን የሚፈልጉና የሚጥሩ

ያለ ሥፍራ ለመሆን መፈለግና ጥረት ማድረግ የአሁኗ ቤተ ክርስቲያን ችግር መሆኑን በተለያየ መልኩ አገልጋዮች ከሚያደርጓቸው ወከባዎች መረዳት ይቻላል:: ትክክለኛ ሥፍራ ላይ በመሆን እያገለገሉ የነበሩ ያለሥፍራቸው ሁኖ ለማገልገል እንዲፈልጉ ሊያደርጓቸው የሚችሉ የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ:: አንዳንዶቹ ስለአገልግሎት ምንነትና ስለራሳቸው የጸጋ ስጦታ እንደሚገባ መረዳቱና እውቀቱ ስለሌላቸው እንዲሁም በቅንነትና

በየዋህነት ከአንዱ አገልግሎት ወደ ሌላ አገልግሎት ሲዘልሉና ያለስፍራቸው ሲገኙ ይታያሉ::

ሌሎች ደግሞ በወቅቱ ባለቸው የአገልግሎት ቆይታ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የኃላፊነት ናፍቆት እና ለስልጣንና ለገንዘብ ባላቸው ፍቅር ሲታወሩ ሥፍራን የመልቀቅ ችግር ውስጥ ይወድቃሉ:: ስኬት፣ በሌሎች መፈለግ፣ የአገልግሎት ፍሬና የፕሮግራሞች መብዛት በእውቀትና በትህትና ካልታየዘ ለፈተና ሊያጋልጥ ይችላል:: ንጉስ ዖዝያን ንጉስ ሁኖ እያለ በልቡ በመታበይ የንጉሥነቱን ኃላፊነት በመተው የካህናትን ሥራ ለመሥራት ወደ መቅደስ እንደገባ ከክፍሉ መማር እንችላለን። (2ኛዜና 26: 16-18 እና ራዕ 2 ፡ 1-2)

### 6. በስፍራቸው በመሆን የሚያገለግሉ

ከጌታ የተቀበሉትን አደራ ለመወጣት ትክክለኛ የአገልግሎት ኃላፊነታቸውን የተረዱ አማኞችና አገልጋዮች መኖራቸው ነው። ከጌታ የተቀበሉትን የጸጋ ስጦታ በመረዳት ለማገልገልና ለመገልገል የተዘጋጀ ልብ፣ ለማወቅና የጌታን ፊት የሚፈልጉ፣ ቃሉን በትክክለኛ መንገድ ለመረዳት የመማር ልብ ያላቸው፣ በእውነትና በትህትና ከሌሎች ለመማርና በቅንነት ለማገልገል የሚናፍቁ፤ በየጊዜው ከስህተታቸው እየተማሩ ለመለወጥ ፍቃደኛ የሆኑ፣ ትክክለኛ አባታዊ ልብ ያላቸው አገልጋዮችና መሪዎች ያጋጠሟቸውና በሌሎች አገልጋዮች( ጸጋ) ለመገልገል ፈቃደኛ የሆኑ ባህርይ መኖሩ የሚሰጠው አስተዋጾ ከፍተኛው ነው።

### *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. ከእግዚአብሔር አምላክ በመንፈስ ቅዱስ በኩል የተሰጠንን የጸጋ ስጦታ ተረድቶ ከማገልገል አንጻር በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊኖሩ የሚችሉ የተለያዩ የአማኞች ዓይነት ይግለጹ? ይህ ጥናት ምን ያስተምራል?

2. አንዳንድ አማኞች ስለጸጋ ስጦታ ምንነት፣ አጠቃቀምና የራሳቸውን ጸጋ ስጦታ በመለየት ለማገልገል የማይፈለጉበት ምክንያት ምንድን ነው ይላሉ? የእርስዎስ ምክንያት ካለ ቢገልጹ ?

3. የጸጋ ስጦታቸውን ለይተው ነገር ግን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጃቸውን አጣጥፈው ሊቀመጡ የሚችሉበት ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል? እርስዎም እንዲህ ዓይነቱን ችግር እንደ እግዚአብሔር ቃልስ ምን ይመክራሉ ?

4. አገልግሎት ሥፍራቸውን በመለየት ከማገልገል ይልቅ ያለጸጋ ስጦታቸው እንዲመኙና እንዲፈልጉ ብሎም ማገልግገል የሚጀምሩበት ምክንያት በመግለጽ ተወያዩበት? ተገቢ ነው? እንዴት ከፈተናው መዳን እንችላለን?

5. አንዳንዶች ደግሞ በሥፍራቸው ሆነው በትጋት እንዲያገለግሉ የሚያስችላቸው ምክንያት ምንድን ነው ይላል? ለእንደዚህ ዓይነት ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላቸዋል? ምንስ ሊያደርጉ ይገባል?

6. ከዛሬው ጥናት እርስዎ ከየትኛው ወገን ነዎት? የተሰጠዎትን የጸጋ ስጦታ በውል ያውቁታል ወይ፣ አውቀውስ በትጋት እያገለገሉ ይገኛሉ? ካልሆነ ለምን ፣ ከዛሬው ጥናት መሠረት አድርገው ምንስ ማድረግ አለብኝ ይላሉ?

7. ጸጋችንን በትክክል ቦታችንን አውቀን መገልገል ከቻልን ለዳኑና ላልድኑ ምን እንጠቅማለን?

**መደምደሚያ**

እንግዲህ ጌታን የግል መድሃኒታችን አድረገን ስንቀበል በመንፈስ ቅዱስ በመጠመቅ አንድ የሰውነት አካል በመሆን ተጠምቀናል። እያንዳንዳችን ጌታ በሰጠን የጸጋ ስጦታ እርሱንና ቤተ ክርስቲያኑን እንድናገለግል ይፈልጋል። እናንተ ያላችሁበት ሁኔታ ምን ይመስላል? ከየትኛው ወገን ራሳችሁን ትመድባላችሁ? እንግዲያውስ ለጌታ ክብርና ለቤተ ክርስቲያን መታነጽ ምክንያት ለመሆን ጸጋችን በመለየት፣ በሥፍራ ሆኖ በትጋትና በጋራ በትብብር እንድንናገለግል ያስፈልጋል። ዛሬ በቤተ ክርስቲያም ውስጥ በአንድም የአገልግሎት ዘርፍ በመሳተፍ የማታገለግሉ ከሆነ ከራስና ከጌታ ጋር በመማከር እንዲሁም ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና አገልጋዮች ጋር በመቀናጀት ለማገልግለ ልትነሳሱ ይገባል።

## ጥናት 17

## የተሰጠን የጸጋ ስጦታ/ ተሰጥኦ/ በመለየት ማገልገል

የንባብ ክፍሎች (1ኛጴጥ.4፡10-11፣ሮሜ.12:4-8)

**ዓላማ**

ከአምላክ የተሰጠንን የጸጋ ስጦታ መለየት የምንችልበትን መንፈሳዊ እውቀት እንደ እግዚአብሔር ቃል በመረዳት መለማመድ እንድንችል ነው።

**መግቢያ**

የተለየ የአገልግሎት ጥሪ ያለን አገልጋዮች ከሆንን እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያኑ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ስጦታ አድርጎ ከሰጣቸው የአገልግሎት ስጦታዎች የትኛው የእኛ ጥሪ እንደ ሆነ መለየት አስፈላጊ ነው። ጥሪያችን ለምን እንደ ሆነ እንደሚገባ መረዳት በዚያው አገልግሎት እግዚአብሔርን በማክበር፣ ቤተ ክርስቲያንን በማነፅና ቅዱሳንን ለአገልግሎት በማዘጋጀት ድርሻችንን መወጣት እንድንችል ዝግጁ ያደርገናል።

ሐዋርያው ጳውሎስ በመልዕክቶቹ መጀመሪያ ላይ "ሐዋሪያ ሊሆን የተጠራ" የሚሉ ሐዋሪያነቱን ጥሪ የሚመሰክሩ ቃላትን በመጠቀም ይታወቃል። ጢሞቴዎስን ደግሞ “የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ” እና “አገልግሎትህንም ፈፅም” (2ኛጢሞ 4÷ 5) በማለት የወንጌል ሰባኪነትና የመጋቢነትን አገልግሎት አጥብቆ እንዲይዝ ይመክረዋል (1ኛ ጢሞ 1÷ 4)። በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን ነብያትና መምህራን እንደ ነበሩ (ሐዋ 13÷ 1-3) እና ፊሊጶስ ደግሞ ወንጌላዊ እንደ ነበረ (ሐዋ 21÷ 8) በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈውን በማንበብ እንረዳለን። ይህ የቅዱሳት መጻሕፍት እውነት እግዚአብሔር ያኔ በዚያ ዘመን ሰዎችን ለተለያየ አገልግሎት እንደ ፈለጋቸውና እንደ ተጠቀመባቸው ሁሉ እንዲሁ ዛሬም እኛን ለምን አገልግሎት እንደ ፈለገን ለመለየት ጥረት እንድናደርግ ያሳስበናል። በዚህ ጉዳይ ላይ ግልጽ አቋም እንዳይኖረንና ግራ እንድንጋባ የሚያደርጉን የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ።

**አገልግሎታችንን እንዳናውቅ ከሚያደርጉን እንቅፋቶች**

አገልግሎታችንን እንዳናውቅ ከሚያደርጉን እንቅፋቶች ጥቂቶቹን እንደሚከተለው እንዳስሳለን፡-

**የመጀመሪያው** አማኞች ከጌታ የተቀበሉትን አገልግሎት በመረዳትና በመለየት እንዳናገለግል እንቅፋት ከሚሆኑብን ምክንያቶች መካከል **የአገልግሎትን ምንነት እንደሚገባ አለመረዳት** ቀዳሚው ተጠቃሽ ምክንያት ነው:: ሀ) **አገልግሎት አምልኮ** እንጂ ፕሮግራምና የተለያየ እንቅስቃሴ አይደለም (ዘጸ 8፡ 1፣ 10፡ 3፣ ያዕ 2፡ 18-20):: ሌላው አገልግሎት ለ) **የፍቅር**

***መግለጫ ነው*** ባለመገንዘብ (ዮሐ 21፡ 15-17) እና ሐ) አገልግሎት ***ራስን ዝቅ በማድረግ ባሪያ መሆን*** እንጂ በሌሎች ላይ ለመሰልጠን የምንጠቀምበት መሳሪያ አይደለም።

**ሁለተኛው** አገልግሎትን የመለየት እንቅፋት ሊፈጥር የሚችል ምክንያት አገልግሎት **የተሰጠበትን ዓላማ መሳት** ነው:: እግዚአብሔር መንፈሳዊ ስጦታን ለአማኞች የሚሰጥበት ምክንያት ለራሱ ለእግዚአብሔር ክብር (1ኛጴጥ 4፡ 10) ለቅዱሳን መታነጽ (1ኛቆሮ 14፡ 26-33)፣ የመንግሥቱ ወንጌል ይሰፋ ዘንድ (የሐዋሪያት ሥራ መጽሐፍ) እና ቅዱሳን ለመንግሥቱ ሥራ ይዘጋጁ ዘንድ ነው (ኤፌ 4፡ 11-16)። ይህ ሲዘነጋና ሲጠፋ አገልጋዮች ትክክለኛ ሥፍራቸውን እንዳያውቁና ያለሥፍራ ለመሆን ፈተና ተጋላጭ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል::

***ሦስተኛው*** እንቅፋት ለጌታ ***ደቀ መዝሙር ለመሆን የተዘጋጀ ማንነት ያለው አገልጋይ መጥፋቱ ነው::*** የደቀ መዝሙር ሕይወት በየጊዜው ተማሪ (ፊል 3፡ 10-16)፣ ያለማቋረጥ ጌታን የሚከተል (ሉቃ 9፡ 23)፣ በገዛ ፈቃዱ የራሱን ሰውነት፣ ቃል፣ መብት (2ኛቆሮ. 4፡5) ጌታ እንዲጠቀምበት የሰጠ በመሆኑ ይገለጣል። ከዚህ ተቃራኒ የተገላቢጦሽ የሆነ ሕይወት ሲኖረን አደራ ለመቀበልና በተሰጠን የጸጋ ስጦታ ለማገልገል ትልቅ እንቅፋት ያጋጥመናል::

***አራተኛው*** እንቅፋት ***አደራ መቀበልንና ተጠያቂነትን መፍራት ነው።*** ፍርሃት የተሰጠንን የጸጋ ስጦታ በመለየትና በመረዳት እንዳናገለግል የሚሞግተን ፈተና ሊሆንብን ይችላል (2ኛጢሞ 2፡ 1-2፣ 1፡ 7):: አገልጋዮች ለዚህ ችግር ተጋላጭ እንዲሆኑ ሊያደርግ የሚችለው ሌላው ምክንያት ምናልባት የአደራው ታላቅነት ሊሆን ይችላል:: አደራው በጣም ገዝፎ ከታየን አደራውን ለመቀበል የብቃት አለመሰማት ማለትም የማንነት አለመብቃት ፍርሃት ውስጥ እንገባለን (1ኛጢሞ 4፡12)። ከአደራው ትልቅነት ባሻገር የምናገለግላቸውን ሰዎችና በአገልግሎቱ ውስጥ የሚያጋጥመንን የጠላት ተግዳሮት መፍራት አደራን የመቀበል እንቅፋት ሊሆን ይችላል:: ተተኪ አገልጋይ ለመሆን የተዘጋጀ ማንነት ከሌለንና የሚተካና የሚያሳድግ መንፈሳዊ አባት አለመኖሩን ካወቅን አደራን ለመቀበል ድፍረት እንዳይኖረን የሚያደርግ ችግር ያጋጥመናል (1ኛጢሞ 4፡ 12-16)::

**አምስተኛው** የአገልግሎትን ጸጋ በመለየት ማገልገል እንዳይቻል ሊያደርግ የሚችል ተጠቃሽ እንቅፋት ***በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ምቹ ሁኔታዎች አለመኖራቸው ነው*** (1ኛጢሞ 4፡ 11-12):: በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምቹ ሁኔታ አለመኖር የሚፈጠረው ግጭትና መለያየት ሲበዛ፣ አገልግሎት በተወሰኑ አማኞች ብቻ ሲያዝና አገልግሎት ሰባዊ በመሆን መንገድ

ብቻ ሲከፈትና ሲዘጋ ነው። ይህ ሁኔታ በሰፊው ካለ አገልጋዮች የተሰጠንን የጸጋ ስጦታ እንደሚገባ እንዳናውቅና እንዳናገለግል ከፍተኛ ተግዳሮት መሆኑ አይቀሬ ነው::

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ከላይ የተጠቀሱትን አሳቦች መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት በማድረግ አገልግሎት ማለት ምንድነ ነው ?
2. የአገልግሎት ምንነትን እንደሚገባ አለመረዳት የጸጋ ስጦታችን ለይተን እንዳናውቅ እንቅፋት ሊሆን የሚችለው እንዴት እንደሆነ በስፋት ተወያዩበት?
3. እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት አገልግሎት የተሰጠበት ዓላማ ምንድን ነው? ደግሞስ ዓላማውን በመፈጸም አገልግሎት እየሰጠን ነው ብለው ያስባሉ? ባይሆን ለምን?
4. አገልግሎት የተሰጠበትን ዓላማ **እንደሚገባ አለመረዳት** የተሰጠንን የጸጋ ስጦታ እንደሚገባ እንዳንለይ እንቅፋት ሊሆን ይችላል ብለው ያምናሉ? ከሆነስ እንዴት?
5. የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት ባደረገ መልኩ እውነተኛ የጌታ ደቀ መዝሙር መሆን ማለት ምንድን ነው?
6. እውነተኛ የጌታ ደቀ መዝሙር መሆን አለመቻል አገልግሎታችንን ለይቶ ከማገልገል ጋር ምን ያገናኘዋል?
7. አገልግሎትንና ተጠያቂነትን መፍራት ሊመጣ የሚችለው በምን ምክንያት ነው?
8. ከእግዚአብሔር ቃል በትክክለኛ ቦታ ያገለገሉ ሰዎች እነ ማን ናቸው? ውጤቱ ምን ነበር?
9. ፩ጴጥ 2:9 እና ማቴ 28:19 መሠረት ለሁሉም አማኝ የተሰጠ ስጦታ እና ኃላፍነት ምንድ ነው? ምን ሀሳብ አለን?

***መደምደሚያ***

አገልግሎታችን እንደሚገባ እንዳንለይ ሊያደርጉ የሚችሉትን ሁኔታዎች በውል ለይቶ በመረዳት ልናስወግዳቸው ይገባል። የአገልግሎት ምንነት፣ የተሰጠበት ዓላማ፣ ከሕይወት በፊት አገልግሎት ላይ ብቻ በማተኮርና አገልግሎትን በተለያዩ ምክንያቶች በመፍራት ራስን ማውጣትና ማግለል ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምምድ መሆኑን ከጢሞቲዎስ ሕይወትና አገልግሎት ልንማር ይገባል። ራስን መቀበልና ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነትም በመቀባበልና በመተባበር እንዲሁም አንዱ ለሌላው ተጠያቂነት በመፍጠር ማገልገል ተገቢ ነው።

## ጥናት 18

## አገልግሎትን መለየት የምንችልበት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምምድ

የንባብ ክፍሎች (ሐዋ 13፡1፣ 1ጴጥ 4፡10-11)

*መሪያችን እንደሚለን ሰዓቱ ካልበቃን የሁለት ቀን ጥናት ማድረግ ይቻላል*

### ዓላማ

የተሰጠንን መንፈሳዊ ስጦታ ለይተን ጌታን በማክበር፣ ቤተ ክርስቲያን በማነጽና ራሳችንም በመባረክ ፍሬያማ የሆነ አገልግሎት መስጠት የምንችልበትን ግንዛቤ ማሳደግ ነው።

### መግቢያ

በሰዎችና በሁኔታዎች ግፊት ሳይሆን እውነተኛ የእግዚአብሔር ጥሪ ምን እንደሆነ፣ ለምን አገልግሎት እንደ ተጠራንና የት ቦታ እግዚአብሔር እንደፈለገን መረዳት በግምት እንዳናገለግልና በአገልግሎት ውስጥ በሚገጥሙን ተግዳሮቶች ተገፍተን መንገድ ላይ እንዳንቀር አቅም ይሆነናል። ትክክለኛ ሰው በትክክለኛው ሥፍራ በመሆን አገልግሎት መስጠት ለአገልጋዩም ፍሬያማነት ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ከእርሱ ጋር አብረው ለሚያገለግሉ ሰላም፣ እረፍትና በረከት መሆኑ አጠራጣሪ አይደለም።

### የአገልግሎት ጥሪያችንን ለመለየት የሚያስችሉ እርምጃዎች

አገልግሎታችን ለይተን ለማገልገል የሚረዱ ጥቂት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆችን እንመልከት።

1. **በጸሎት (ሐዋ 13:1-3፣ ዕብ 4:16)**

አገልግሎታችንን ለመለየት የምንጸልየው የጸሎት ርዕስ ትኩረትም ጌታ አገልግሎትንና የጸጋ ስጦታን እንዲሰጠን ሳይሆን የተሰጠን ጸጋ ምን እንደ ሆነ መለየትና ማገልገል እንድንችል ሊሆን ይገባዋል። እንደ ምህረቱ ብዛት ከጨለማ ወደ ሚደነቅ ብርሃን ጠርቶን በመንፈስ ቅዱስ በማጥመቅ ወደ አካሉ እንድንገባና በአካሉ ውስጥ ጠቃሚዎችና አገልግሎት ያለን አማኞች እንድንሆን አስችሎናል (የሐ. 13:1-3) እንግዲያውስ በእግዚአብሔር ቤት ሥራ ፈት የሆነ አማኝ የለምና የጸሎት ርዕሶቻችንን አስተካክለን በመጸለይ ምን ማድረግ እንዳለብንና በምን እንድናገለግለው መንፈስ ቅዱስ እንደፈለገ ጥሪውን ተረድተን በተሰጠን በዚያው ጸጋ እግዚአብሔርንና ቅዱሳንን ልናገለግል ይገባል።

**2. በእግዚአብሔር ቃል**

በኤፌ. 4÷ 11 ላይ የተጠቀሱትን አምስት የአገልግሎት ስጦታዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረታቸውን፣ አንዱ ከሌላው የሚለዩበትን፣ የሚመሳሰሉበትን፣ የአገልግሎት ትኩረታቸው የት ላይ እንደ ሆነና አገልግሎቶቹ የሚጠይቋቸውን የሕይወት ጥራቶች የመሳሰሉ አሳቦችን በተመለከተ ከእግዚአብሔር ቃል ምላሽ ማግኘት መልካም ነው። ምናልባት ጠለቅ ያለ እውቀት እንዲኖረን መጽሐፍ ቅዱሳችን ባግባቡ ማጥናት፣ በእነዚህ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትምህርት እንዲሰጥ ማድረግ፣ የተፃፉ ጽሑፎችንና መጻሕፍትን ማንበብና መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤቶች በመግባት ቃሉን ለመረዳት ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው።በተለይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች፣ ስልጠናዎች፣ የተልዕኮ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤቶች እየበዙ፣ ብዙ መጻሕፍትና መጣጥፎች እየተጻፉ፣ ባለበት በዚህ ዘመን ብዙ መረጃዎችን በማግኘት የአገልግሎት ስጦታዎችን ምንነት፣ የአገልግሎት ትኩረት፣ አንድነትና ልዩነት መረዳት የምንችልባቸውን አጋጣሚዎች በመጠቀም አገልግሎታችን ለማወቅ ጥረት ማድረግ እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው።

**3. የውስጣችንን ሸክም ደጋግመን መጠየቅ**

የእግዚአብሔርን ጥሪ መለየት የምንችልበት አንዱ መንገድ ከስሜታዊነት ያለፈና በየዕለቱ የማያቋርጥ የአገልግሎት ሸክም ያለን መሆኑ ነው። ሐዋያው ጳውሎስ “... ዕለት ዕለት የሚከብደኝ የአብያተ ክርስቲያት ሁሉ አሳብ ነው” (2ኛ ቆሮ 11÷ 28፣ 1ኛቆሮ 9÷ 16) በማለት የገለጠውና ለገዛ ዘመዶቹ የማያቋርጥ ጭንቀትና የልብ ሀዘን እንዳለበት ያሳወቀው (ሮሜ 9፡ 1-4) እውነተኛ የአገልግሎት ሸክምን በሕይወቱ ይዞ የሚኖር እውነተኛ ጥሪ ያለው አገልጋይ ስለነበረ ነው። ነህምያ በምቾት ቦታ እየኖረ እያለ ስለኢየሩሳሌም ሁኔታ በየጊዜው መጠየቁ፣ በጾምና በጸሎት በእግዚአብሔር ፊት መቅረቡና በውስጡ ያለው የአገሩ ሸክም በንጉሱ ፊት እስኪታወቅ መድረሱ የኢየሩሳሌም መፍረስ ግድ ይለው ስለነበረ ነው። ይህ ሸክም ከቤተ-መንግሥት ትቶ እንዲወጣ አድርጎታል። እውነተኛ የልብ ሸክም አውቀነውም ሆነ እንዲሁ ሳናውቀው በየጊዜውና በቋሚነት በንግግራችን፣ በፀሎታችን፣ በውይይታችን እና በእንቅስቃሴያችን ... ሁሉ ይገለጥብናል።

በእርግጥም ከእግዚአብሔር የሆነው የአገልግሎት ሸክም በየጊዜው እየከበደ፣ በውስጣችን ስፍራ እየያዘና እየጨመረ በሌሎች ሁሉ ይታወቃል (ይታያል)። ያለንበት ምቾትም ሆነ መከራ አያስቆመንም ይልቁንም ይበልጥ ደፋር እንድንሆንና ጌታን በመተማመንና በመታዘዝ

እንድንጓዝ አቅም ይሆነናል።

### 4. ቀደምትነት ያላቸውን አገልጋዮችን ማማከር (ዕብ 10፡ 24-25)

የእግዚአብሔር የሆነና ተጠርቻለሁ የሚል ሰው ምክር ፈላጊ፣ ምክር ጠያቂ እንዲሁም ከሌሎች ለመማር የሚፈልግ ትሁት መሆን ይኖርበታል። የተጠራንበት አገልግሎት የበለጠ ግልፅ ይሆንለት ዘንድ ሊመከርና ተረድተው ሊረዱት የሚችሉ በእምነት የሚቀድሙት አገልጋዮችን ምክር መጠየቅ አዋቂነት ምልክትና የበለጠ የምናውቅበትን ጊዜ ማሳጠሪያ መንገድ ነው ::

ሐዋሪያው ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ለአህዛብ ሐዋሪያ ይሆን ዘንድ በጌታ የተጠራ ሰው ነበር። ነገር ግን ሁለት ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ለአገልጋዮችና አዕማድ መስለው ለሚታዩ "… ምናልባትም በከንቱ እንዳልሮጥ ወይም በከንቱ ሮጬ እንዳይሆን በአህዛብ መካከል የምሰብከውን ወንጌል አስታወቅኋቸው ዋኖች ግን መስለው ለሚታዩ ለብቻቸው አስታወቅኋቸው" (ገላ 2÷ 1-2) በማለት ለቀደሙት አገልጋዮች የነበረውን ስፍራና ከእነርሱ ለመማር የነበረውን ፈቃደኝነት አሳይቶናል ።

### 5. የአገልግሎታችንን መልካም ተፅዕኖ /ፍሬ/ መቃኘት

በእግዚአብሔር የተጠራ ሰው በተጠራበት የአገልግሎት አቅጣጫ የሚያመጣው መልካም ተፅዕኖ ይኖረዋል። ነገር ግን መልካም ተጽእኖ ማምጣት በአንድ ጀንበር ወይም በአጭር ጊዜ አይታይም። በመሆኑም መጠበቅና መታገስን የሚጠይቁ ሁኔታዎች መኖራቸው አይቀሬ ነው። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል "በለሱን የጠበቀ ፍሬዋን ይበላል፤ ጌታውን የሚጠብቅ ይከብራል" (ምሳ 18፡ 13) እንደሚል ፍሬ የሚሰጠውን ጌታ በመጠየቅ "...ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬያችሁ ሊኖር ሾምኋችሁ..." (ዮሐ15. 16) በማለት የተናገረውን መርህ በሕይወታችን ለማየት በትዕግስትና በትጋት መጽናት ይጠበቅብናል። የምናገለግለው አገልግሎት ሰዎችን ወደ ክርስቶስ በማቅረብ ቅዱሳንን በማነጽና ለአገልግሎት በማዘጋጀት በፍሬ መገለጡን መቃኘት አስፈላጊ ነው።

### 6. ስለአገልግሎታችን የሌሎች ቅዱሳን ምስክርነት

በጠራን ጌታና በእኛ ብቻ ይታወቅ የነበረው የአገልግሎት ጥሪ እየገፋና ሌሎችም ሰዎች እስኪገነዘቡትና እስኪመሰክሩ ድረስ እየተገለጠ መምጣቱ አይቀሬ ነው!! የሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌዎች ይህንን እውነታ የሚያጠናክሩ ምስክሮች ናቸው፡-

1. **ስለኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት፡-** መጥምቁ ዮሐንስ “ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ” በማለት ሲመሰክር (ዮሐ 1፡ 39)፤ ኒቆዲሞስ ደግሞ “ …መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ እናውቃለን ” (ዮሐ 3፡ 2) ብሏል። ጴጥሮስም “ …አንተ ክርስቶስ የህያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ ..” (በማቴ 16፡ 16) በማለት መስክሮለታል።

2. **ስለ ጳውሎስ ለአገልግሎት መጠራት፡-** ሐናኒያ በአሕዛብም፣ በነገስታትም፣ በእስራኤል ልጆችም ሁሉ ፊት የጌታን ስም የሚሸከምና የተመረጠ ዕቃ እንደሆነ ከእግዚአብሔር ዘንድ በመስማት መሰከረለት (ሐዋ 9፡ 10-19)፤

3. **የአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን** ደግሞ ለተጠሩበት ሥራ በርናባስንና ሳውልን ለዩልኝ የሚለውን የመንፈስ ቅዱስን ድምጽ በመስማት ምስክር ሆነው እጅ ጭነው ከጸለዩላቸው በኋላ አሰናበቱአቸው (ሐዋ 13፡ 1-3)።

4. **ስለ ጢሞቴዎስና ስለ ቲቶ የአገልግሎት ጥሪ፡**- ጳውሎስ “ስለ ቲቶ የሚጠይቅ ቢኖር ስለ እናንተ አብሮኝ የሚሠራ ባልንጀራዬ ነው፤ ስለ ወንድሞቻችን የሚጠይቅ ቢኖርም የአብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞችና የክርስቶስ ክብር ናቸው።” (2ኛቆሮ 8፡ 16-23) ፣ ስለጢሞቴዎስ “በትንቢት ከሽማግሌዎች እጅ መጫን ጋር የተሰጠህን፥ በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል።” (1ኛጢሞ 4፡ 12-14 2ኛጢሞ 1፡ 6-8) በማለት መሰከረ።

## *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. አገልግሎትን ለመለየት በእግዚአብሔር ፊት መሆንና ቅዱስ ቃሉን ማጥናት የሚሰጠውን ጠቃሜታ ቃሉን መሠረት በማድረግ ተወያዩበት?
2. በጸጋ ስጦታ መለየትና ማገለገል ሂደት ራሳችንን ደጋግመን መጠየቅና ሌሎች እኛን የቀደሙ አማኞች ማማከር ያለውን አስተዋጾ በመግለጽ ተወያዩበት
3. በተሰጠን የጸጋ ስጦታ የአገልግሎት ፍሬ መቃኘትና የሌሎች የተገልጋዮችና የመሪዎችን ምስክርነት መስማት ያለውን አዎንታዊ ጠቀሜታ በመግለጽ በስፋት ተወያዩበት?
4. እርስዎ የተሰጥዎን የጸጋ ስጦታ እንዳይለዩ እንቅፋት የሆነብዎት ችግር የሚሉትን ቢገልጹ?      ችግሩን ለማስወገድ ሊወስዱት የሚገባ እርምጃ ምንድን ነው ይላል?

5. የጸጋ ስጦታን ለይቶ በመረዳት፣ በሥፍራ ሆኖ ከሌሎች ጋር ለማገልገል ምን ማድረግ አለብኝ ይላሉ? ልምምድዎን በነጻነት ያካፍሉ?
6. በ1ኛ ጴጥ. 4:10 መሠረት አንድ አማኝ ጌታ በሰጠው  አገልግሎት ሲያገለግል እንዴት ማገልገል ይኖርበታል ይላሉ?  እርስዎስ እንዴት እያገለገሉ ነው?
7. በዛሬውም ጥናት የተማሩት አንድ አዲስ ነገር ካለ ያካፍሉ?

**መደምደሚያ**

ክርስቶስን አምኖ ደህንነት እንዳገኘ አማኝ ቢያንስ አንድ የጸጋ ስጦታ ይኖረናል። የተሰጠን ጸጋ ስጦታ ለይቶ መረዳትና በተሰጠን ስጦታ ማገልገል ደግሞ  ሌላ የአማኞች ፍላጎት፣ ትጋትና ተባብሮ ማገልገልን  ይጠይቃል። ከጌታ የተቀበልነውን የጸጋ ስጦታ ለመለየት ተግዳሮት በመለየት ማስወገድ ተገቢ ነው። የተሰጠን የጸጋ ስጦታ ለመለየትና ራሳችንን ለማሳደግ በእግዚአብሔር ፊት ማቅረብ፣ ቃሉን መሠረት አድርጎ ማገልገል፣ ለእግዚአብሔር ክብር በመስጠትና ለቅዱሳን መተናጽ ምክንያት በመሆን እናገልግል። ጌታንና ቅዱሳን ማገልገል ከአምላክ የተሰጠን ዕድል መሆኑን በመገንዘብ እንደ መከረኛ ሳይሆን እንደ ዕድለኛ ከሌሎች ጋር በመተባበር እጅ ለእጅ ተያይዘን በትጋት ልናገለግል ይገባል።

## ክፍል 8
## የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ
## ጥናት 19
## ፈቃዱን ለማወቅ እግዚአብሔርን ማወቅ

**የንባብ ክፍል** ነው"ቆላስይስ 1:9-12

"ከዚህ የተነሣ እኛ ደግሞ ይህን ከሰማንበት ቀን ጀምሮ እግዚአብሔር የፈቃዱን ዕውቀት በመንፈሳዊ ጥበብና መረዳት ሁሉ ይሞላችሁ ዘንድ ስለ እናንተ መጸለይና መለመን አላቋረጥንም፤ የምንጸልየውም ለጌታ እንደሚገባ እንድትኖሩና በሁሉም ደስ እንድታሰኙት ነው፤ ይኸውም በመልካም ሥራ ሁሉ ፍሬ እያፈራችሁ <u>እግዚአብሔርን በማወቅ</u> እያደጋችሁ፣11ታላቅ ጽናትና ትዕግሥት ይኖራችሁ ዘንድ፣ እንደ ክቡር ጉልበቱ መጠን በኀይል ሁሉ እየበረታታችሁ፣ ደስ እየተሰኛችሁ፣ 12በቅዱሳን ርስት በብርሃን ተካፋዮች ለመሆን ያበቃንን አብን እንድታመሰግኑ

"ደግሞም ልባቸው እንዲጽናናና በፍቅር እንዲተሳሰሩ፣ ፍጹም የሆነውን የመረዳት ብልጥግና አግኝተው የእግዚአብሔር ምስጢር የሆነውን ክርስቶስን እንዲያውቁ እተጋለሁ፤" ቆላስይስ 2:2

**ዓላማ**

አሁን ካለንበት የእምነት እውቀት ደረጃ በላቀ መልኩ በቃሉ መሰረት እግዚአብሔርን አውቀንና በእርሱም ታውቀን አላማ መር ሕይወት እና በኑሮአችንና በአገልግሎታችን ፈቃዱን አውቀን መኖር እንድንችል ለማስገንዘብ

**መግቢያ**

<u>**የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከማወቅ በፊት እግዚአብሔርን ራሱን ማወቅ ይቀድማል።**</u> በዘፍጥረት 5 ላይ ከአዳም ጀምሮ እስከ ኖህ ድረስ አስር የቤተሰብ አባላት ተጠቅሰው ሲገኙ ከሄኖክ በስተቀር ዘጠኙ የትውልድ መሪዎች ኖረውና ወልደው ሲሞቱ ሄኖክ ግን አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር በማድረጉ እንዳልተገኘና እግዚአብሔር እንደወሰደው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። የዕብራውያን ጸሃፊ ይህንኑ ሲያብራራ ወደ ሰማይ ከመወሰዱ በፊት እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ገልጿል (ዕብ፡- 11:5)። ኖረ ወለደና ሞተ ከሚለው የተፈጥሮ ሂደት ይልቅ አካሄዱን <u>ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ የሚለው የከበረ ሃሳብ</u> ነው። የትንቢት መንፈስ በሆሴዕ በኩል እንዲህ ይላል እግዚአብሔርን "እንወቅ፤ እናውቀውም ዘንድ እግዚአብሔርን እንከተል፤ እንደ ወገግታም ተዘጋጅቶ እናገኘዋለን፤ እንደ ዝናብም ምድርንም እንደሚያጠጣ እንደ መጨረሻ ዝናብ ይመጣል"።

በትንቢተ ዳንኤል 11:32፦ "… ነገር ግን አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ ይበረታሉ፣ ያደርጋሉም" የሚል ቃል አለ፤ የዚህ አባባል መነሻው ታሪካዊ ነው። አንዳንድ አይሁዳውያን የግሪክ ባህልና ቋንቋ ከሌላው ብልጫ አለው ብለው በተሳሳተ መልኩ በመገንዘባቸው ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን እምነትና የተቀደሰውን ኪዳን በመተው የግሪኩ መሪ አንጥያኮስ ኤፒፋነስ 4ኛ የግሪክን ባህልና እምነት ወደ አይሁድ እንዲያስገባና እንዲቀላቅል አግባቡት። እርሱም ይህንኑ በመተግበር በኢየሩሳሌም ቤተመቅደስ እርያ ሰውቶ በተቀደሰው ስፍራ ዜውስ የተባለውን የግሪክ አምላክ ምስል አቆመ። ይህ ተግባር ሲፈጸም በአንጻሩ (በተቃራኒው) እግዚአብሔርን የሚያውቁና ለእርሱም ታማኝ የሆኑ አይሁድ ነበሩ። እነዚህም በይሁዳ መቃቢስ መሪነት የሽምቅ ውጊያ በማካሄድ አንጢያኮስን አሸንፈው ሰራዊቱ ወደ መጣበት ወደ አገሩ ወደ ግሪክ እንዲያፈገፍግ አስገደዱት። ከዚህ በኋላ ቤተመቅደሱ ተቀደሰ፣ መብራቶቹም እንደገና በሩ። ይህም ድል እስካሁን ድረስ በአይሁድ ዘንድ የሐኑካ በዓል በመባል ይከበራል። እነዚህ የአይሁድ ወገኖች አምላካቸውን የሚያውቁና ለርሱ ቀናኢ በመሆናቸው ነበር ዋጋ በመክፈል ይህንን ታላቅና የተፈራ የግሪክ ንጉስ ገጥመው ያሸነፉት። የዳንኤል 11:32 ጥቅስም የሚያመለክተው ይህንኑ ነው።

ለዳሰሳ ያህል ብንመለከት ኖህ ጻድቅና ከበደል የራቀ አካሄዱንም ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ ነበር (ዘፍ. 6:8፣ 7:1)፣ አብራሃም ለተገለጠለት ለእግዚአብሔር ሳያቅማማ እሺ ብሎ የወጣ ነበር (ዘፍ. 12:1-4)፣ ሙሴ የአባቶቹን አምላክ እግዚአብሔርን ተገንዝቦ ፊት ለፊት ለማየት የፈራና ፊቱን የሸፈነ ነበር (ዘፀ. 3:1-6)። መጽሐፍ ቅዱሱን ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ድረስ በትዕግስት ብናስሰው ቁጥራቸው ብዙ የሆኑና አምላካቸውን እግዚአብሔርን የሚያውቁ ሰዎችን እናገኛለን። የጋራ ባሕሪያቸው የሆነው ደግሞ እግዚአብሔር ራሱን ሲገልጥላቸው ከእርሱ ጋር ይበልጥ እየተቀራረቡና እየተዋወቁ ለርሱና በእርሱ መኖር ነው።

### ***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ቆላስይስ 1:9-12 እና ቆላ 2:2 መሠረት የሐዋርያው ጸሎት ምንን ያሳያል?
2. በዮሐ. 1:12 መሰረት እግዚአብሔርን ማወቅ የሚመነጨው ከምንድን ነው?እርሱንስ ማወቅ የሚችለው ማን ነው (1ዮሐ.2:29)?
3. እግዚአብሔርን እንድናውቅ ያደረገን ወይም ከእርሱ ጋር ያስተዋወቀን ማን ነው (1ዮሐ. 5:20)?
4. ሄኖክን በዘመኑ ከኖሩት ሰዎች ልዩ የሚያደርገው ምንድን ነው (ዘፍ.5:24፣ ዕብ. 11:5)?

እንደእርሱ እግዚአብሔርን ስናውቅስ እንዴት እንኖራለን?

5. ስለ እግዚአብሔር አውቆ መጨረስ አይቻልም? እንዴት? ስለዚህ ለምንድን ነው እግዚአብሔርን ማወቅ ላይ ማተኮር ያለብን (ዮሐ. 17:3)?
6. እግዚአብሔርን ማወቅ የሁለትዮሽ ትውውቅ በመሆኑ በእርሱ ዘንድ መታወቅ እንደሆነ በማቴዎስ 7:21-23 ባለው እውነታ ተመርኩዘው ያብራሩ
7. “... ነገር ግን አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ ይበረታሉ፣ ያደርጋሉም” (ዳንኤል 11:32) የሚለውን ታሪካዊ እውነት ያብራሩ
8. ሆሴዕ 6፡1-3 በማንበብ እግዚአብሔር ከህዝቡ ምን ይፈልጋል? አብራሩ።
9. እግዚአብሔርን በትክክል ማወቅ ለሌሎች እርሱን ከማሳወቅ (ከወንጌል ሥርጭት) ጋር ምን ግንኙነት አለው? በዚህ ሳምንት እርሱን ያወቅነውን ያህል እናሳውቅ።

***መደምደሚያ***

የነገሩን ፍሬ ሐሳብ ስናጠቃልለው እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት መንፈስ ቅዱስ በገለጠልን መጠን አምላክነቱንና አባትነቱን በፍጹም ማንነታችን ተገንዝበን ከእርሱም ጋር ዘለቄታዊ ቁርኝት ፈጥረን ለክብሩ መኖር ማለት ነው። ይህ ደግሞ የሐዋርያው ጳውሎስም ጸሎት ነው።

# ጥናት 20

## የእግዚአብሔርን ድምጽ መለየት

**ዓላማ**

የአምላካችንን ድምጽ ለይተን በማወቅ በአብሮነት ጥምረት የሚገኘውን ደስታ እያጣጣምን መኖር እንድንችል ለማበረታታት

**መግቢያ**

አንድ ሕጻን ተወልዶ እያደገ ሲመጣ ከወላጆቹ ጋር ካለው ጥምረትና ደጋግሞ ድምጻቸውን የመስማት ሂደት የተነሳ እያደር ድምጻቸውን መለየት እንደሚችል ሁሉ አማኝም ጌታን ተቀብሎ የልጅነት ሥልጣንን ካገኘ በኋላ እያደር የአምላኩን ድምጽ በይበልጥ ማወቅ ይጀምራል። በዮሐ. 20:16 ከሞት የተነሳው ኢየሱስ ለመግደላዊት ማሪያም ሲገለጥላት የነበረውን ትዕይንት ብንመለከት ይህንን እውነታ በደንብ ያብራራልናል። "ኢየሱስም ማሪያም አላት እርሷም ወደ እርሱ ዘወር ብላ በአራማይክ ቋንቋ ረቡኒ አለቺው።" ዖች ማን ኒ የተባለው የእግዚአብሔር ሰው የዚህን ጥቅስ ጥልቅ ሚስጢር ሲያብራራ እንደዚህ ይላል። "በመጀመሪያ ማሪያም ስሟን ታውቃለች ቀጥሎም የጠራትን የድምጽ ቃና አበክራ ታውቃለች። ለዚህም ነበር ሳትጠራጠር ረቡኒ ያለቺው።" ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐ. 10:4 ላይ ስለ መልካሙ እረኛ ማለትም ስለ ራሱና በጎቹ ስለሚላቸው እርሱን አምነው የዳኑ አማኞች ሲናገር፡- "በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል" ይላል። ያም ብቻ ሳይሆን "እንግዳ የሆነውን ግን ድምጹን ስለማያውቁ ከእርሱ ይሸሻሉ እንጂ ፈጽሞ አይከተሉትም" በማለት በመቀጠል ይናገራል። በዚህ የእግዚአብሔር ቃል ብርሃን መሰረት የእግዚአብሔርን ድምጽ የለዩ አማኝ በትምህርት ነፋስ ሁሉ የሚፍገመገም አይሆንም።

እንዴት ድምጹን መስማት እንችላለን?

1. ስለ ጌታ ሁል ጊዜ በማሰብ፣
2. ፊቱን በጸሎት በመናፈቅ
3. ቃሉን በማንበብ
4. ስለ ጌታ በመመስከር
5. ለጌታ እና ለልጆቹ ባለን ታላቅ ፍቅር

## *የመወያያ ጥያቄዎች*

1. የእግዚአብሔርን ድምጽ መለየት የምንለማመደው እንዴት ነው (ዮሐ. 15:4)?
2. አዳምና ሄዋን የእግዚአብሔርን ድምጽ ለይተው ያውቁ ነበር ማለት እንችላለን? አብራሩ?
3. በዮሐ. 10:5 መሰረት በጎቹ እንግዳ ከሆነው ድምጽ የሚሸሹት ለምንድን ነው?
4. ነቢዩ ሳሙኤል የእግዚአብሔርን ድምጽ የተለማመደው እንዴት (1ሳሙ. 3:1-10) ነው?
5. ጌዲዮን የእግዚአብሔርን ድምጽ የለየው እንዴት ነው (መሳ. 6:17-22፣ 36-40)?
6. መግደላዊት ማሪያም ጌታ ኢየሱስን በመቃብሩ ሥፍራ ያወቀችው እንዴት ነው?
7. ሳሙኤል የእግዚአብሔርን ድምጽ የለየው እንዴት ነው (1ሳሙ. 3:1-10)?
8. የጌታንም ድምጽ መስማት የምንችልባቸውን መንገዶች በመጥቀስ ተውያዩ። ምንስ ይጠቅማል?

## *መደምደሚያ*

ስናጠቃልል በትክክል ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛችን አድርገን ከተቀበልን በኋላ “በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ እኖራለሁ” (ዮሐ.15:4) ተብሎ በተጻፈው መሰረት እርሱን በጸሎትና ቃሉን በማንበብ ትጋት ይበልጥ እየተጠጋነው ስንሄድ ድምጹን በሚገባ እንለያለን።

# ጥናት 21
# መሰል ድምጾች

**የንባብ ክፍል** (ዘዳግም 13:1-5፣ት.ኤርምያስ 23:9-18፣1ኛ ቆሮንቶስ 14:29-31፣ 37-38)

**ዓላማ**

ከእግዚአብሔር የተሰጡ ድምጾችን (ትንቢቶችን፣ትምህርቶችን፣መገለጦችን፣ ስብከቶችን፣ሕልሞችን ወ.ዘ.ተ) በቃሉ ወንፊት አበጥረንና መዝነን በመለየት የቤተክርስቲያንን ጤናማ ዕድገት እንዴት መጠበቅ እንዳለብን ለመርዳት

**መግቢያ**

**እንደ እግዚአብሔር መልዕክተኛ በእግዚአብሔር መንፈስ ታዞ የእግዚአብሔርን ሐሳብ ለሕዝቡ የሚናገርና ቤተክርስቲያንን የሚያንጽ ልዩ ልዩ ጸጋ ያለው አገልጋይ እንዳለ ሁሉ አስመሳይና ለእግዚአብሔር ክብርም ሆነ ለሕዝቡ ጥቅም ሳይሆን ለራሱ ረብና ዝና ሲል እግዚአብሔር ተናገረኝ የሚል እንዳለ በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በየዘመናቱ በተከሰቱት የቤተክርስቲያን ታሪካዊ ሂደቶች የታወቀ እውነት ነው።** ጥሩ ነግሮች እንዳሉ ሁሉ የማያንጹ ነገሮችም መኖራቸውን መማር፣ማወቅ እና መኖር በጣም ጥሩ መንፈሳዊነት ነው። በብሉይ ኪዳን እውነተኛ ነቢያት እንደነበሩ ሁሉ ሀሰተኞችም ነበሩ። ለምሳሌ ያህል በ2ኛዜና 18:4-7 ያለውን ታሪክ ብንመለከት ንጉስ አክዓብ አራት መቶ እግዚአብሔር ያልተናገረውን አስመስለው የሚናገሩ የሐሰት ነቢያት እንደነበሩትና “እግዚአብሔር በንጉሡ እጅ አሳልፎ ይሰጣታልና ውጣ” ብለው ወደ ሬማት ዘገለዓድ ለጦርነት እንዲወጣ የተነበዩለት ነበሩ። ሐቁን ስንገነዘበው ግን ታሸንፋለህ የተባለው ንጉሥ አክዓብ በውጊያው ወቅት በጦር ተውግቶ መሞቱን እናያለን። በዘዳግም 13:1-5 ያለውን ብንመለከት፡- “… ነቢይ ወይም ሕልም አላሚ ቢነሳ ምልክትም ተአምራትም ቢሰጥህ… “ እያለ ከቀጠለ በኋላ ግን ከእውነተኛ አምላክ ወደ ጣዖት ዘወር የሚያደርግ ከሆነ መገደል እንዳለበት ይናገራል።

በሌላ መልኩ አንድ ባለ መሰል ድምጽ ነቢይ ነኝ ወይም ባለ ራዕይ ነኝ ባይ የሕዝብን በደልና ኃጢአት የማይኮንንና ለትምህርት እንዲሆን የማያጋልጥ ከሆነ በኤርምያስ 23:9-18 እንደተገለጸው፡- “ትንቢት የሚናገሩላችሁን የነቢያትን ቃል አትስሙ፤ ከንቱነትን ያስተምራችኋል፤ ከእግዚአብሔር አፍ ሳይሆን ከገዛ ልባቸው የወጣውን ራዕይ ይናገራሉ…” በማለት እግዚአብሔር ራሱ ያስጠነቅቃል።

ሌላው እውነት የተነገረው ትንቢት ተፈጻሚነቱ እውን ካልሆነ ትንቢት ስለሚመስል ብቻ መቀበል የለብንም። በኦሪት ዘዳግም 18:20-22፡- "ነገር ግን ይናገር ዘንድ ያላዘዝሁትን በስሜ በድፍረት የሚናገር ወይም በሌላ አማልክት ስም የሚናገር ነቢይ እርሱ ይገደል። በልብህ እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል እናውቅ ዘንድ እንዴት ይቻለናል? ብትል፣ ነቢዩ በእግዚአብሔር ስም በተናገረ ጊዜ የተናገረው ነገር ባይሆን ባይመጣም፣ ያ ነገር እግዚአብሔር ያልተናገረው ነው፣ ነቢዩ በድፍረት ተናግሮታል እርሱን አትፍራው።" ጥቂት ነጥቦችን ብንመለከት የዚህ ዓይነት አገልጋይ ነኝ ባይ፡-

1. የሚናገረው በጌታ ያልታዘዘውን ነው (ቁ. 20)

2. የሚናገረው በእግዚአብሔር ስም በድፍረት (በማያዋጣ ድፍረት) ነው (ቁ. 20)

በአዲስ ኪዳንም ደግሞ 1ኛ ቆሮንቶስ፡- 14:29-31፣ 37-38 ላይ ያለውን ብንመለከት ሐዋርያው ጳውሎስ በሚገባ አብራርቶት እናያለን። ከቁ. 29-31 ባለው መሰረት እንዴት በሥርዓት መናገር እንደሚኖርበትና የሚለዩ ሰዎችም ማለትም ከእግዚአብሔር ሆኖ እንደሆነ የሚመረምሩ መኖር እንዳለባቸው ሲገልጽ፣ **ከቁ. 37-38 ደግሞ ይህ የሐዋርያው ጳውሎስ ትንተና ከእግዚአብሔር የተሰጠው ትዕዛዝ በመሆኑ መንፈሳዊ የሆነ ሰው ሁሉ ቢቀበለው መልካም እንደሚሆንለትና ከእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነትን እንደሚያገኝ ይህንን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ባይቀበል ግን እግዚአብሔር እርሱንም እንደማይቀበለው ይናገራል።**

በ1ኛ ዮሐንስ 4:1 ደግሞ፡- 'ወዳጆቼ ሆይ ፣ መንፈስን ሁሉ አትመኑ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ ፣ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና" ይላል።

ቤተ ክርስቲያን በችኮላ የምትሰማውን ትንቢትም ሆነ መገለጥ በችኮላ ከእግዚአብሔር ነው ብላ ከመደምደሚና ከመቀበሏ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎችን በአገልጋዮቹም ሆነ በመልዕክቱ መጠየቅ ይኖርባታል።

1. ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ይስማማል ወይስ አይስማማም? (1ኛ ዮሐንስ 4:1)

2. የቅድስናን ኑሮ ያበረታታል? (1ኛ ጢሞ. 6:3)

3. መልዕክቱን ተናጋሪው ሰው በክርስቶስ ጌትነት ሥር በእውነት የሚኖር ነው? (1ኛ ቆሮ፣ 12:3)

4. ትክክለኛና እውነተኛ መልዕክት ነው? (1ኛ ተሰ. 5:20-21)

በተረፈው እውነተኛው ድምጽ ያመኑትን ያጸናል፣ከጥፋት ይመልሳል፣ላልዳኑት ምልክት ይሆናል እና ሌሎችም። በመካከላችን እንደዚህ እውነተኛ የሆኑትን ጸጋዎች ደግሞ እናበረታታለን፣እንዲሁም እንጸልይላቸዋለን።

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. በመግቢያው መሰረት መሰል ድምጽ ማለት ምን ማለት ነው?
2. በ2ኛ ዜና 18:7 መሰረት ከንጉሥ አክዓብ አባባል ምን እንማራለን ?
3. ከእግዚአብሔር አፍ ሳይሆን ከገዛ ልባቸው የወጣውን ራዕይ ይናገራሉ የሚለውን ያብራሩ(ኤር. 23:16)
4. እግዚአብሔርን በመዳፈር በስሙ የሚናገር ስንል ምን ማለታችን ነው? (ዘዳ. 18:20-22)
5. የየዋህን ሕዝብ ጥማት ተመልክተው መሰል ድምጽን የሚያመጡ አሉ ብለው ያምናሉ? 1ኛ ዮሐ. 4፤1ን ያብራሩ
6. መሰል ድምጾችን የምንለይባቸው ጥቂት ነጥቦችን ይዘርዝሩ
7. ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና (1ኛ ጴጥ. 1:21) ሲል ምን ማለቱ ነው?
8. በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔር እውነተኛ ድምጽ ጥቅሙን አብራሩ።

***መደምደሚያ***

መሰል ያልሆነና ትክክለኛ የትንቢት ድምጽም ሆነ መገለጥ የሚሰጠው ከእግዚአብሔር ሲሆን (1ቆሮ. 12:11፣ 2ኛ ጴጥ. 1:21) ዓላማውም ራሱን እግዚአብሔርን ለማክበርና ቤተክርስቲያንን ለማነጽ እንደሆነ በመገንዘብ በመሰል ድምጾች ከመታለል መጠንቀቅ ያስፈልገናል።

## ጥናት 22

## የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቆ ማገልገል

### ዓላማ

*መዝሙረኛው በምዕራፍ 25 ቁጥር 4 ላይ "እግዚአብሔር ሆይ አካሄድህን እንዳውቅ አድርገኝ፤ መንገድህንም አስተምረኝ" እንዳለው ፈቃዱን አውቀን ማገልገል እንችል ዘንድ እንድንተጋ ለማሳሰብ*

### መግቢያ

*አንድ በእግዚአብሔር ያመነ ሰው የዕድገት ሂደት ብንመለከት፡- 1) በመጀመሪያ ጌታን ተቀብሎ መዳን ፡- "እናንተ ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ ወደ እኔ ኑ" ማቴ. 11:28፣ 2) ከእግዚአብሔር ጋር መኖር፡- "በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ" ዮሐ. 15:4፣ 3) አገልጋይ መሆን፡- "ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" የሐዋ. 1:8፣ "ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ..." የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ እውነታዎች በጌታ የዳንበትንና ከእርሱ ጋር አብረን በመኖር እርሱን በይበልጥ እያወቅን የሄድንበትን ሂደት ሲያመላክቱ፤ ሶስተኛ ደግሞ እርሱን ስላወቅን እንደራሴዎቹ ሁነን ፈቃዱን የምናስፈጽም መሆናችንን የሚያስረግጥ ነው።*

*እንግዲህ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቆ እንደ ፈቃዱ ማገልገል ራሱን እግዚአብሔርንና የልቡን ሐሳብ ከማወቅ ይጀምራል። እግዚአብሔር አብን የሚያውቀውና ከእርሱ ጋር አንድ ሐሳብ ያለው እግዚአብሔር ወልድ፡- "እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤እንደሰማሁ እፈርዳለሁ፤ ፍርዴም ቅን ነው፣የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና (ዮሐ. 5:30)" ይላል። ደግሞም፡- "...የማስተምረው ትምህርት ከራሴ ሳይሆን ከላከኝ የመጣ ነው። ማንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ቢፈልግ የእኔ ትምህርት ከእግዚአብሔር ወይም ከራሴ የመጣ መሆኑን ለይቶ ያውቃል፤ ከራሱ የሚናገር ያን የሚያደርገው ለራሱ ክብርን ስለሚሻ ነው፤ ስለላከው ክብር የሚሰራ ግን እርሱ እውነተኛ ነው (ዮሐ. 7:17-18) በማለት ይጨምራል። እናም ጌታ ኢየሱስ የደህንነትን ሥራ የሰራው የአብን ትዕዛዝ በመፈጸም ነው።፡ እኛም ሰዎችን ወደ ደኅንነት ልናመጣ የምንችለው በእርሱ ፈቃድና ምሪት ስንጓዝ ብቻ ነው። ለዚህ ደግሞ ወደ እውነት ሁሉ የሚመራንና ከራሱ የማይናገር የእውነት መንፈስ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አደራረጉን ያሳየናል (ዮሐ. 16:7-12)።*

**የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ደግሞ በአ ዕምሮአችን ዕለት ዕለት መታደስ አለብን (ሮሜ 12:1-2)። እግዚአብሔርን አውቀን ስንኖር ፈቃዱን ለመፈጸም እግዚአብሔር የፈቃዱን ዕውቀት በመንፈሳዊ ጥበብና መረዳት ሁሉ ይሞላብን ዘንድ መጸለይ ይኖርብናል (ቆላስይስ፡- 1:9-10)። ደግሞም ከምናውቀውና ፈቃዱን ከተገነዘብነው ከእግዚአብሔር ዘንድ የጸጋን ሥጦታ ስንቀበል በዚያው መጠን ማገልገል እንደሚኖርብን ቃሉ ይናገራል (1ኛ ጴጥ. 4:10)።**

ምሳሌያችን የሆነው ጌታችን ኢየሱስ፡- "እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ (ዮሐ. 17:4)" በማለት መናገሩ ሥራ ሰጪ አብ ሥራን ፈጻሚ (አድራጊ) ራሱ (ወልድ) መሆኑን ያስገነዝበናል።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለማገልገል በመዳን፣ በእርሱ በመኖርና በመላክ ያለውን ግንኙነት ያብራሩ
2. ሮሜ 12:1-2 በማንበብ ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ተወያዩ።
3. በዮሐ. 7:17 "የማስተምረው ትምህርት ከራሴ ሳይሆን ከላከኝ የመጣ ነው" ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንድናውቅ ወደ እውነት ሁሉ የሚመራን ማን ነው (16:7-12)
5. ስለ እግዚአብሔር ፈቃድ ክርስቶስ በዮሐ. 17:4 "**እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ" አለ።** ከዚህ ቃል ምን እናስተውላለን?
6. በፈቃዱ እውቀት እንድንሞላ ምን ማድረግ አለብን (ቆላስይስ 1:9-10)?
7. የሳኦል የውድቀቱ መነሻ ምን ነበር (1ኛ ሳሙኤል 13:13)?
8. "ዳዊት በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ካገለገለ በኋላ... (የሐዋርያት ሥራ.13:36)" የሚለውን ያብራሩ። በዚህ ክፍል የተጠቀሰው የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድ ነው?
9. ከዛሬው ውይይት ምን ተማርን?

**መደምደሚያ**

የእግዚአብሔርን ፈቃድ አውቀን ለማገልገል ከእርሱ ጋር የጠበቀ ሕብረትና የልቡን ትርታ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት መረዳት ያስፈልጋል። እንደራሴዎቹ ስለሆንን እንደ ራሱ ሆነን በውክልና ፈቃዱን እናከናውናለን እንጂ ለምኞታችንም ሆነ ለዝና አናገለግልም።

# ክፍል 9
# ባህልና ክርስትና በመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ እይታ
# ጥናት 23
# ባህልና ክርስትና

## ዓላማ

የተወለድንበትና ያደግንበት ሀገር እና ህዝብ ይሁን አሁን ያለንበት ሀገር ባህል እንደ እግዚአብሔር ቃል ካልያዝነው ህይወታችንን እና ኑሮአችንን እጅግ ሊጎዳን ይችላል። ስለዚህ ይህ ጥናት የባህልን ምንነትና መገለጫዎች ለይቶ በመረዳት በባህል ውስጥ ሚዛኑን የጠበቀ የክርስትና ሕይወት መኖር እንድንለማመድ ለመርዳት ነው።

## መግቢያ

ሁሉም ባህል የራሱ ጠቃሚ እና ጎጂ ልማዶች መኖሩ ግልጽ ነው። ተወልደን ያደግንበት ባህል በአሁኑ አስተሳሰባችንና የአኗኗር ዘይቤያችን ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽዕኖ መፍጠሩ የታወቀ ነው። ያለፈውም ሆነ የአሁኑ ባህል በእኛ ላይ በመፈራረቅ እይታችንና የክርስትና አኗኗራችን ላይ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ። ዛሬ በምንኖርበት ዘመንና አገር ያለው ባህል ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ማዛመድና መተግበር እንዳያስቸግረን የባህሉን ታሪካዊ ዳራ መመርመር ያስፈልጋል። የቤተሰብ፣ የቤተ ክርስቲያን፣ ማኅበረሰብና አገር ውስጥ ያለውን ባህል መረዳት በጋራ ተባብረን ለመኖርና አምላክን ለማክበር ይረዳል። <u>**እንደ ክርስቲያን ባህልን ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ባልተጣረሰ መንገድ መለማመድና መኖር እንድንችል ባህል በመጽሐፍ ቅዱስ መፈተሽና መተርጎምና ብሎም መተግበር ያስፈልጋል።**</u>

## የባህል ምንነት

የአንድ ማኅበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ፣ ወግ፣ ልማድ፣ እምነትና ሌሎችን ነገሮች የሚያጠቃልል እንደሆነ ይታመናል። ሰዎች ያላቸው ባህል በተለያየ ጊዜ ሊለወጥና ሊሻሻል የሚችል ነው። ከዚህም የተነሳ አንድ ማኅበረሰብ ወይም አገር ለሌላው አገር ባህልን በተለያዩ መንገዶች በማስተዋወቅ የባሕል ልውውጥ ያደረጋሉ። በተለይ በዚህ ዘመን ዓለም አንድ መንደር በሆነችበት ወቅት የአንድን አገር ባህልና ወግ ለማወቅ፣ ለመረዳት እንዲሁም ለመልመድ ቀላል ነው። የአንድ አገር ባህል ለሌላው አገር ሰው አንዳንዶችን ሲያስደነግጥ ሌሎችን ደግሞ መቀበል እና ቶሎ የመልመድ አጋጣሚን ሊፈጥር ይችላል።

በተለይ ደግሞ በሰው አገር ለምንኖር ለእኛ ያለንበትን የዚህን ማኅበረሰብ የአኗኗር

ዘይቤ ራስን በማስለመድ ሂደት ያለው ፈተና፣ ችግር፣ ፍርሃትና ድንጋጤ፣ ውጥረትና ጫና ቀላል አይደለም። እንደ ክርስቲያን ደግሞ ከመጣንበት አካባቢ፣ አብያተ ክርስትያናት፣ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ከዚሁ በጌታ አምኖ በመዳን የቤተ ክርስቲያን አባል በመሆን ከሌሎች ጋር ሆኖ በኅብረት ማምለክና ማገልገል ወዘተ ራሱን የቻለ ባህልና ልምምድ ነው።

ሌላው ቀርቶ መጽሐፍ ቅዱስን በግልም ሆነ በጋራ ስናነብና ስናጠና፣ ስንሰማና ስንሰብክ እንዲሁም በጥልቀት ቃሉን ስናጠና የተጻፈላቸውን ሰዎች ባህል ማጥናትና መረዳት የግድ ይለናል። ከዚህ የተነሳ የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪካዊ ዳራ ለመገንዘብ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ የአንደኛ ቆሮንቶስ መልዕክት የተጻፈላቸው ሰዎች የሚኖሩበት አገር ባህል፣ የቤተ ክርስቲያን አኗኗር ዘይቤ፣ የጻፊው ሁኔታ፣ የተጻፈበት ወቅት፣ ቦታ፣ የአገሩና የቤተ ክርስቲያን መልካዓ ምድራዊ፣ ማኅበራዊ፣ መንፈሳዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ መቃኘት የግድ ይላል። ይህ ሁሉ የሚሆነው መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ አሳቡ በመረዳት መተርጎም እንዲቻል ነው። ይህ ደግሞ በዚያ ዘመን ያለውን ተረድቶ በዚህ ዘመን ለእኛ አውዳዊ ትርጉሙን ጠብቆ ከሕይወት ጋር ለማዛመድ ስለሚረዳን ነው።

ባሕል በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ የሚገኝ ልማድ ሲሆን በተለይ ደግሞ በአንድ በተወሰነ ቦታ ወይም የሰዎች መደብ ውስጥ በእጅጉ የተስፋፋ ልማድ ነው። እንደ አመጋገብ እና አነጋገር ሥርዓት ያሉ አንዳንድ ባህሎች ሰዎች በቡድን በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ጥሩ ጠባይ እንዲያሳዩና እርስ በርሳቸው መከባበር እንዲችሉ ባሕርያቸውን ለመጋራት ከማሰብ የመነጬ ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲህ ባለው ወቅት በኅብረተሰብ ውስጥ የሚኖረው መልካም ባሕርይ ከዘይት ጋር ሊመሳሰል ይችላል። ምክንያቱም በሰዎች መካከል ያለው ግንኙነት ሸካራ እንዳይሆን ይረዳል።

## የውይይት ጥያቄዎች

1. በአንድ አገር ወይም ሕዝብ ውስጥ የባህል ምንነትና አስፈላጊነት በመግለጽ በስፋት ተወያዩበት።

2. አንድ አገር የራሱ የሆነ ባህልና ወግ አለው ሲባል መገለጫዎቹ ምንድ ናቸው? ቤተ ክርስቲያንስ የራሷ የሆነ ባህል አላት? ካላትስ በምን ይገለጻል? ገላ 3፡28 ቆላ 3:11 በማንበብ ይህንን መልስ ይመልሱ!

3. መጽሐፍ ቅዱስን በምናጠናበት ጊዜ የተጻፈበትን ዘመን፣ የተጻፈላቸው ሰዎች ታሪካዊ

ዳራ ማጥናት ስንጀምር ለማወቅና ለመረዳት ጥረት የምናደርገው ለምንድን ነው? ጠቀሜታውስ ምንድን ነው?

4. ክርስቲያን ከባህል ውጭ መሆን ይችላል? ካልሆነ ከባህል ውጪ አለመሆናችን እንዴት ይገለጻል? ባህል በምን መመዘን አለበት?
5. የእኛን የምንኖርበትንና መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበት ባህል አስታርቆ ለመሄድ ምን ማድረግ አለብን ይላሉ? የበላይ መሆን ያለበት የትኛው ነው ትላላችሁ? ለምን?
6. ስለባህል ምንነትና አስፈላጊነት እንዲሁም በባህል ውስጥ ስንኖር እንዴት መመላለስ እንዳለብን የተማሩት አንድ አዲስ ነገር ያካፍሉ?
7. የአንድን አገር ኃጢአት ያልሆኑትን በባህል ውስጥ ያሉትን ልምምዶች ለወንጌል እንዴት መጠቀም እንችላለን? ምሳሌ መስጠት እንችላለን?

## *መደምደሚያ*

እንግዲህ የባህል ምንነት እንደሚገባ መረዳት የአኗኗር ዘይቤያችን በጥንቃቄ እንዲሆን ያግዛል። ሁላችንም የትናንት ያደግንበትና የኖርንበት፣ ዛሬ እየኖርንበት ያለ አገር፣ ቤተ ክርስቲያንና የመጽሐፍ ቅዱስ ባህል ውስጥ ለመኖር ጥረት የምናደርግ መሆናችን መዘንጋት የለብንም። ይህን መረዳት ደግሞ ነገሮችን እንደ እግዚአብሔር ቃልና አምላክን በሚያከብር ሁኔታ እንዲሁም ጽድቅና ሰላም ባለበት መንገድ ለመኖር ከፍተኛ እገዛ ይሰጠናል። ባህልን ሁሉ ክፉ ወይም መልካም እንዲሁም ዘላለማዊ አድርጎ መቁጠርና ራስን በግል ባህል ብቻ ማጠር፣ እኛ ወደ ሌሎች አገር ባህል ዘለልና ሌሎችም ወደ እኛ እንዳይደርሱ እንቅፋት እንዳይሆንብን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያሻዋል። ባህል የሚያድግ፣ የሚለወጥና የሚሻሻል መሆኑን በመገንዘብ በየጊዜው መልካም ከሆነው ለመማር፣ ለመለወጥና ራስን ለማስለመድ ራስን ማዘጋጀትና ማስለመድ መቻል መንፈሳዊነትና ብስለትም ነው።

## ጥናት 24

## ባህልና የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን

### የንባብ ክፍል ሐዋ ሥራ 6፡1-6፤ሐዋ.10፡1-35,44-48

**ዓላማ**

የባህል ልዩነትና አንድነት በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ላይ የፈጠረው ተጽዕኖ አጉልቶ በማሳየት እኛ ከእነርሱ በመማር ጠንካራ ኅብረት እንዲኖረን ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ነው።

**መግቢያ**

በአንድ ቤተሰብ፣ ቤተ ክርስቲያን፣ ማኅበረሰብና አገር የሚኖር የተለያዩ ሰዎች የባህል አንድነትና ልዩነት ሊከሰት ይችላል። የባህል አንድነትና ልዩነት አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ ሊፈጥር ይችላል። በተለይ ከባህል ዘለል የሆነ ክርስቲያናዊ ኅብረት ሊኖራት የሚገባት ቤተ ክርስቲያን በአማኞች መካከል በባህላቸው ዋጋ የሚሰጣቸው፣ የሚመዘኑና አገልግሎት የሚያገኙ ከሆነ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል። **ያደግንበት እና የኖርንበት ባህል በመጽሐፍ ቅዱስ ይመዘናል እንጅ ባህል መጽሐፍ ቅዱስን ሊመዝን አይችልም። በቃሉ እይታ ኃጢአት ሊሆኑ የሚችሉ የባህል ልምምዶች እንዳሉም መዘንጋት የለብንም። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የባህል ልዩነት በመረዳት ሁሉም ሰው በክርስቶስ በኩል አንድ ቤተሰብ መሆናችንን በመገንዘብ ልንኖር ይገባል።** በመካከልም የሚፈጠሩ የልምምድ ልዩነቶችንም እንደ እግዚአብሔር ቃል መሠረት መፍታትና ወደ ጋራ አምልኮ፣ አገልግሎትና ሌሎችን በወንጌል ለመድረስ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። የባህል ልዩነትና አንድነት በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን ላይ የፈጠረው ተጽዕኖ

1) በመካከላቸው በነበረው ኅብረት አድሎና መገለል ተፈጥሮ ነበር፡- ሐዋ.6፡1-6
2) ግጭትና መለያየትን መፍጠር፡- ሐዋ.6፡1-6
3) አማኞችን ለሌላ ባህል ክፍት እንዳይሆኑና ክርስትናን ለአይሁድ ባህል ብቻ አድርጓቸው ነበር፡- ሐዋ.10፡1-35,44-48
4) የባህል ተጽዕኖ አንዳንድ አገልጋዮችን በሰው ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖራቸው የአገልጋይነት ስበዕናቸውን በመተው ግብዝ እንዲሆኑ ጋብዟል፡- ገላ.2፡7-17
5) በአሕዛብና በአይሁድ የሌለ የኃጢአት ልምምድ ተፈጽሞ ዝም ብለው መቀመጣቸው፡- 1ኛቆሮ.6፡1

6) ለሰው ወይም ለሃይማኖት ሰራሽ የባህል ልምምዶች ለምሳሌ የቆሮንቶስ መል ዕከት ብዙ ያስተምራል (አመጋገብ፣አነጋገር፣የአምልኮ ሥርዓት እና ሌሎችም)

**የምንኖርበትን አገር ባህል ጠንቅቆ መረዳትና በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ መፈተሽ የሚኖረው ጠቀሜታ**

1. የራስ የሆነ የክርስትና ማንነትና ስብዕና እንዲኖረን ያግዛል
2. በጋራ ለመኖር የጋራ የሆኑ ማኅበራዊ እሴቶች ለመለየትና ለመንከባከብ ያግዛል
3. በጋራ ባለን ግንኙነት ኃላፊነታችንና ግዴታችን በመለየት ለመኖር መስመር ያበጅልናል
4. በልዩነት አንድነት እንዲኖረን፣ በመከባባርና በመረዳዳት ለመኖር መሥፈርት ይሰጠናል።
5. ባህል በሰዎች ስብእናና አኗኗር ዘይቤ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ማምጣቱን ለመገንዘብ፣ ራስን ለመጠበቅና ባህልን በእግዚአብሔር ቃል በመዋጀት የክርስትና እሴት ለማራመድ ከፍተኛ ዕድል ይሰጣል።
6. መጽሐፍ ቅዱስን በእኛ ዘመን ባለው ባህል መነጽር እንዳንተርጉምና እንዳንለማመድ ይረድናል

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1) በሐዋ.6:1-6 መሠረት በመካከላቸው የነበረው የዜግነትና የባህል ልዩነት ምን እንደፈጠረ ተወያዩበት
2) በሐዋ.6:1-6 የተደረገው አድልኦና መገለል የፈጠረው ግጭትና መለያየት ምን ተጽዕኖ እንዳመጣባቸው በስፋት ተነጋገሩበት
3) በመካከላቸው የተፈጠረውን አለመግባባትና ግጭት እንዴት እንደፈቱትና እንደተቆጣጠሩት በመግለጽ በኅብረት መካከል ለሚፈጠሩ ግጭቶች የምንማረው መርህ ምንድን ነው?
4) በሐዋ.10:1-35,44-48 የሃይማኖት ልምምድ መሠረት ክርስትናን ለማን ብቻ እንደሆነ እንዲያስቡ አድርጓቸው ነበር? ይህንስ ከቃሉና በዚህ ክፍል ጋር በማጣቀስ ገላ.2:7-17 የነበረው ችግር ምንድን ነበር?

5) በ1ኛቆሮ.8፡1- 13 መሠረት በቆሮንቶስ ከተማ የነበረው የአኗኗር ዘይቤ በቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ላይ የፈጠረው አሉታዊ ተጽዕኖ ምንድን ነበር? ጳውሎስ ችግሩን ለመፍታት የሰጠውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ ነበር? በስፋት ተወያዩበት

6) በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ላይ የታዩ ባህልን መሠረት ያደረጉ አለመግባባትና ግጭቶች በመነሳት ከእነርሱ ልምድ በመማር ልንወስደው የሚገባ መርህ ምንድን ነው ይላሉ?

7) የምንኖርበትን አገር አካባቢ ባህል ጠንቅቆ መረዳትና በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ መፈተሽ የሚኖረው ጠቀሜታ በመጥቀስ ተወያዩበት?

8) ከዛሬው የጥናት ክፍል የተማሩትንና እርምጃ ሊወስዱበት የሚገባ አንድ በመጥቀስ ለኅብረቱ ያካፍሉ?

**መደምደሚያ**

እንግዲህ በተለያዩ ጊዜያት በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መካከል የባህል አንድነትና ልዩነት የፈጠረው አለመግባባትና ግጭት በመረዳት ልንማር ይገባል። በባህል ምክንያት በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የፈጠረውን ተጽዕኖ በመቃኘት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ምላሽ በመስጠት በቃሉ መኖር ያስፈልጋል። ባህልን በመጽሐፍ ቅዱስ እይታ መፈተሽ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ይህም ደግሞ የራስ የሆነ ማንነትና ስብዕና እንዲኖረን፣ በጋራ ለመኖር የጋራ የሆኑ ማኅበራዊ እሴቶች ለመለየትና ለመንከባከብ ፣ በጋራ ባለን ግንኙነት ኃላፊነታችንና ግዴታችን በመለየት ለመኖር ፣ በልዩነት አንድነት እንዲኖረን፣ በመከባበርና በመረዳዳት ለመኖር መሥፈርት መስጠትና መጽሐፍ ቅዱስን በእኛ ዘመን ባለው ባህል መነጽር ብቻ እንዳንተርጉምና እንዳንለማመደው ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

# ጥናት 25
# የባህል እሴቶቻችን በመጽሐፍ ቅዱስ
# መሪያችን እንደሚመራን ይህንን ጥናት የሁለት ቀን ጥናት ማድረግ እንችላለን

**ዓላማ**

የእኛ አገር ባህል መገለጫ የሆኑቱን ለይቶ በመረዳት መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ እውነት የግልና የኅብረት አይታዎቻችንና እሴቶቻችን ማስተካከል እንድንችል ለማገዝ ነው።

**መግቢያ**

ሁላችንም ተወልደን ያደግንበት ሀገር እና ህዝብ ባህል ለዛሬው ማንነታችን ያደረገው አስተዋጾ ቀላል የሚባል አይደለም። ዛሬ በትዳር፣ በቤተሰብና በቤተ ክርስቲያን መካከል የእሴትና የልምምድ ልዩነት እንዲፈጠርና እንድንለይይ ሊያደርግ ከሚችሉ መካከል አንዱ ባህላችን ነው። የአለባበስ፣ የሰላምታ፣የሥራ፣የአመጋገብ፣ የሀዘን መግለጫ፣ የአሳብ ልዩነት የምናስተናግደበት መንገድ እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አብሮ በማምለክና በማገልገል ላይ ሲንጸባረቅ ለማየት አያስችግርም። በባህላችን የሚንጸባረቁ የተለያዩ መገለጫዎችን በመለየትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትን መሠረት አድርገን ከሌላ ባህል ጋር እንዴት መኖር፣ ጌታን ማምለክ እና ማገልገል እንደምንችል እውቀትና ልምድ ማግኘት እንችላለን።

**እንዲሁም ሀዘን ሲገጥመን ሀዘን ቤት ስንሄድ እና እኛም ሀዘንን ስናስተናግድ የተለያዩ ከጌታ ቃል ውጪ የሆኑ ልምምዶችን እናደርጋለን። እነዚህንም ነገሮች እንደ ጌታ ቃል ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም ለጊዜ ያለን ዋጋ ከባህል እንደወርስነው ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል እንደሚለን መሆን አለበት።**

በተለይም የመጣንበትን ህዝብ እና ሀገር በተመለከተ፡-

## 1. የአገር ቤትና አሁን የምኖርበት አገር የተለያዩ የባህል ልምዶች እና መገለጫዎች

**ሀ. የአለባበስ ሥርዓትና ወግ፡-የአለባበስ ሥርዓትና ወግ** ብለን ስንል የወንድና የሴት አለባበስ ፣ ከቤተ ክርስቲያን ውጪና ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለን የአለባበስ ባህልን የሚገልጽ ነው። በተለይ አገራዊና በውጩ ዓለም ስንኖር ከአገር ባህል በተለያዩ ጊዜያት የሚለበሱ የባህልና ዘመናዊ የሆነ አለባበስ በግልጽ ልዩነት ይታወቃል። በየጊዜው ከሁኔታው ጋርና ሁኔታዎች ለመግለጽ ከምንጠቀምባቸው መንገዶች አንዱ የልብሱ ዓይነትና የቀለም ልዩነት ተጠቃሽ ናቸው።

**ለ. የአመጋገብ ሥርዓትና ወግ፡-** ይህ የአመጋገብ ባህል እንደ አካባቢያችን፣ አቅማችንና እንደ ጤንነታችን ሁኔታ ሊወሰን ቢችልም በብዙኃኑ የተለመደና ባህል የሆነ መሆኑ የታወቀ ነው። የአመጋገብ ባህላችን የምንወደውና የምንጠላው በአካባቢያችን የተለመደና የተጠላ፣ በምንኖርበት አገር ባህል የሚዘወተር የምግብና የአመጋገብ ሥርዓት ፣ በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ግልጽ ሆኖ ተቀምጧል። እንዲሁም የሰላምታ እና የንግግር ዘይቤዎች ሌሎች ተጠቃሾች ናቸው።

**ሐ.** የሰላምታ ሥርዓት፡- ለምሳሌ በአሜርካን ሀገር ባህል እንደሀገራችን ከተቃራኒ ጾታ ጋር የምናደርጋቸውን ንግግሮች እና ሰላምታዎች ልዩነት እንዳላቸው ማወቅ ተገቢ ነው።

**መ.** የሥራ ባህል፡- ለሥራ እና ለንግድ ደንበኞች ያለው ባህል እና ልምድ በአሜርካን ሀገር ከኤርትራ እና ኢትዮጵያ ብዙ ልዩነት እንዳለ ማወቅ አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ በትጋት እንድንሰራ ያዘናል "ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ፤ በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ፤ ለጌታ ተገዙ፤" (ሮሜ 12፥11)።

**እጅግ ጠቃሚ ምክር፡-** የአንደኛ ቆሮንቶስ አና የቆላስይስ መልዕክቶች ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው (ቆላ.2:16-23, 1ቆሮ 11:2-16)። በቆሮንቶስ ቤ/ክ የነበሩ ምዕመናን ወደ ቤ/ክ ሲመጡ ብዙ የውጭ የባህል ልምዶችን ይዘው እንደነበረ ይታወቃል። ሐዋርያው ጳውሎስ አንዳንዶችን ለሌሎች መዳን ሲል እንዲጠብቁ ሲጠይቃቸው የተወሰኑትን ልምዶች ደግሞ እንዲተው ያዛቸዋል።

### 2. *ሀዘን ሲገጥመን የምናስተናግድበት መንገድ፡- ራዕይ* 21:1-6፣ 2ኛሳሙ.12:13-23

- ***የሀዘን መግለጫ***

*ክርስትያን ባልሆኑና በሆኑም ህብረተሰብ እንደ ሰው ተፈጥሮአዊ ማንነት፣ ጾታና እንደ አስተዳደጋችን እና እንደምንኖርበት አገር ባህል የሀዘን መግለጫችን ሊለያይ ይችላል። አንዳንዱ በለቅሶ በእንባ፣ በዝምታ፣ አካሉን በመጉዳት፣ ራስን በመጣልና ባለመጠበቅ፤ አለባበስን በመቀየር ሀዘኑን የሚገልጥባቸው መንገዶች ናቸው።*

*ሀዘንተኞችን ለማጽናናት ስንሄድም የተለያዩ ስህተቶችን እንሰራለን ማለትም መናገር የሌለብንን ነገሮች እንናገራለን፤ለምሳሌ ሟቹ በጌታ መሆኑንና አለመሆኑንን ሳናውቅ ጌታን ያውቅ ነበር ብሎ መጠየቅ፣ የሟቹን ቤተሰብ ብዙ ማስለቀስ፣ ስለ እግዚአብሔር ቅጣት መናገር፣በጌታ ቃል አስቦ አለማጽናናት እና ሌሎችም ናቸው።*

- *ሀዘን የሚፈጥረው ተጽዕኖ*

ሀዘን በማንኛውም ሰውና ባህል ሊገለጽ የሚችል ከሠው ሕይወትና ኑሮ ቁርኝት ያለው ልምምድ ነው። በየጊዜው ከሰው ሰው ሊቀልና ሊከብድ የሚችል የማይለመድ ክስተት ነው። ሀዘን በሰው ሕይወት ላይ የሚያመጣውና የሚፈጥረው ተጽዕኖ እንደ ሰዎቹ ዓይነት ቢለያይም አሉታዊ ተጽዕኖ መፍጠሩ አይቀሬ ነው። ሀዘን በሰዎች አካላዊ ማንነት ላይ የጤንነት እክል፣ አካላዊ ክብደት የመጨመርና የመቀነስ አጋጣሚ ሊፈጥር ይችላል።

ሌላው በሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በመፍጠር በአንዳንዶች ላይ ከአምላክና ከቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና ምዕመናን ጋር እንዲጣሉ፣ እንዲጋጩ፣ እንዲያኮርፉ በመሆን ከቃሉ፣ ከጸሎት፣ ከቅዱሳን ኅብረትና አገልግሎት ሊርቁ ይችላሉ። በሀዘንተኞች ሥነ ልቦናዊ ማንነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በመፍጠር በከፍተኛ ድብርት (depression)፣ ጭንቅትና ውጥረት፣ ፍርሃትና ድንጋጤ፣ ተስፋ መቁረጥና ጨለምተኛ ሊያደርጋቸው ይችላል። ሀዘን በሰዎች ማኅበራዊ ሕይወትና ግንኙነት ላይ ሰዎችን ይበልጥ የሚፈልጉበት ወይም ይበልጥ የሚርቁበት ብቸኛ ለመሆን ተጋላጭ ሊያደርጋቸው የሚችል ነው። ከዚህም የተነሳ በሙያቸውና በኑሮአቸው ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊፈጥርባቸው ይችላል። **ይህ በአማኝ ህይወት እንዲሆን የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። አማኝ ማዘን ያለበት እንደ ጌታ ቃል ብቻ መሆኑን ማወቅ አለበት።**

- *ሀዘንን የምናስተናግድበት ባህልና ወግ*

ሀዘን በግልና በቤተሰብ ሲፈጠር የምናስተናግድበት መንገድ፣ ልምድና ክህሎት ሊለያይ ይችላል። አንዳንዱ ሀዘን ቀለል፤ ሌላው ከበድ፣ አንዳንዶች በውስጣቸው ሌሎች በውጫዊ በአካላቸው የሚገልጹ፣ አንዳንዶች ለአጭር ጊዜ ሌሎች ለብዙ ጊዜ ሊቆይባቸው ይችላል።

- *መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት*

ከዳዊትና ልጁ ልምምድ ከሐዋርያው ጳውሎስ ህይወት ምን እንማራለን? አማኝ ሀዘንን የሚያስተናግድበት መንገድ ካላመኑ ወገኖች እጅግ ይለያል። እንዲሁም ሀዘን ሲገጥመን ሀዘን ቤት ስንሄድ እና እኛም ሀዘንን ስናስተናግድ ከጌታ ቃል ውጪ የሆኑ የተለያዩ ነገሮችን እናደርጋለን። እነዚህም ነገሮች እንደ ጌታ ቃል ማድረግ እጅግ አስፈላጊ ነው። ሀዘን ቤት ስንሄድ አላስፈላጊ ነገሮችን ከመናገር የጌታ የመጽናናት ቃል መናገር እጅግ ጠቃሚ ነው (2ቆሮ 1:1-7)።

**3. ለጊዜ ያለን ዋጋና የጊዜ አጠቃቀም ባህላችን፡- መክ.3፡11፣**

የጊዜ ምንነትና አስፈላጊነት፡- ለሁሉም ሰው እኩል የተሰጠ በረከት ቢኖር ጊዜ ነው። ጊዜን ለተፈለገው ቁም ነገር ማዋልና መጠቀም ለጊዜ ያለን ዋጋ ይወስነዋል። ይህም ጊዜ አለኝ በሚል የመዝናናትና በመጨረሻም ባለቀ ሠዓት በውጥረት መሥራትና መከወን ባህል አድርጎ መንቀሳቀስ የተለመደ ነው። ጊዜን በአግባቡ ያለመጠቀም ባህላችን በሁለንተናዊ ማንነታችንና እንቅስቃሴያችን ላይ የሚያመጣው አሉታዊ ተጽዕኖ በቀላል የሚታይ አይደለም። ጊዜን በአግባብ አለመጠቀም ትናንትን በጸጸትና በወቀሳ ፣ ዛሬን ደግሞ ከደስታና ከእርካታ ይልቅ በድብርትና በጭንቀት እንድንመላለስ ከማድረጉ ባሻገር ቀጣይ የነገ ሕይወታችንን ባለራዕይነት ይልቅ ጨለምተኛ እንድንሆን ያደርጋል። ጊዜን በአግባብ እንዳንጠቀም ከሚያደርጉን ከተለያዩ ምክንያቶች መካከል ለጊዜ ያለን እሴት፣ አጠቃቀም፣ ቅድሚያና አንገብጋቢ የሆኑትን ለይቶ ባለመረዳት ተጠቃሽ ናቸው።

**4. የአሳብ አንድነትንና ልዩነትን የምናስተናግድበት ልምምድ**

1. አስተዳደጋችን የፈጠረብን ተጽዕኖና በመካከላችን ያለው የእድሜና የጾታ ልዩነት
2. በመንፈሳዊ ሕይወት ያለን ብስለትና በዓለማዊ እውቀት ያለን መረዳት ልዩነት
3. ነገሮችን የምናይበትና የምንተረጉምበት ዘዴ
4. የአሳብ አንድነታችንና ልዩነት ለመግለጽ የምንጠቀምባቸው አቀራረብ ትልቅ ሚና ይጫወታል። ሐዋሪያው ጳውሎስ በቆሮንጦስ ቤተ ክርስቲያን ለነበረው ዘርፈ ብዙ ችግር ለማስተካከል በጻፈው ድብዳቤ በቀጥታ በትችት አለመጀመሩ ትልቅ ምሳሌ ነው። የቆሮንጦስን ምዕምናንን በእግዚአብሔር ዘንድ ያላቸውን ሥፍራና ዋጋ ፣ ያላቸውን የኅብረት ዓይነት በመግለጽና በማበረታታ ነው። 1ኛቆሮ.1፡1-3፣ ምሳሌ፣ 25፡20
5. የማደመጥና የመናገር ክህሎት፡- ያዕ.1፡19

**የመወያያ ጥያቄዎች (የሁለት ቀን ጥናት ቢሆን ይመረጣል)**

1. የአመጋገብ ሥርዓትና ወግ ከነበሩበትና ከዚህ አገር ባህል ጋር በማነጻጸር የአመጋገብን ባህል ይግለጹ? በዚህ ቃል 1ኛቆሮ.11፡5-12፣ ቆላ.2፡16-23 መሠረት ስለአመጋገብ ያለውን ሥርዓት እንዴት ይረዱታል?

2. ስለ ሰላምታ እና ሥራ ያለው የባህል ልዩነት ተነጋገሩ። መጽሐፍ ቅዱስስ ምን ይላል።

3. የሀዘን ምንነት፣ ለምን እንደሚገጥመን በመጥቀስ የሀዘን መግለጫ ከውጬ ዓለም ጋር በማነጻጸር ይነጋገሩበት

4. እንደ ማንኛውም ሰው ሀዘን ሲገጥመን እንዴት ማስተናገድ ይኖርብናል ይላሉ? የምናስተናግድበት መንገድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታው ምን ሊመስል ይገባል ይላሉ? 2ኛሳሙ.12:13-23 ራዕይ 21:1-6

5. እንደ 1ኛ ተሰ. 4:13-18 ባለው ቃል መሠረት የአዲስ ኪዳን አማኞች በጥልቅ ሀዘን ውስጥ መግባት የማያስፈልገው ለምንድን ነው ይላሉ?

6. ሀዘን ስንሄድ ማድረግ የሌለብን ነገሮች ምንድ ናቸው? ያ ቤተ ሰብ ወይም ግለሰብ ወደ ሀዘን ከመግባቱ በፊት እድሉን ካገኘን ምን እናድርግ?

7. በጊዜና በጊዜ አጠቃቀም ላይ ያለን የአገር ቤትና የዚህ አገር ባህል ያለውን ልዩነትና አንድነት በመጥቀስ ይነጋገሩበት? ምን እናድርግ?

8. በመክ. 3:1-11 መሰረት ለጊዜ ያለንን ዋጋና የጊዜ አጠቃቀም ባህላችን እንዴት መሆንና ማድረግ አለብን?

9. የአሳብ አንድነትንና ልዩነትን የምናስተናግድበት ባህልና ልምድ እንዴት ይገልጹታል? በአሳብ አንድ ዓይነት እንዳንሆንና በልዩነት ማስተናገድ እንዳንችል ሊያደርገን የሚችሉ ምክንያቶች ምን ሊሆኑ ይችላሉ ይላሉ?

10. የባህል ተጽዕኖ ለቤተ ሰብ አለመግባባት ምን ቦታ አለው? በባልና ሚስት፣ ወላጆች ከልጆች ጋር ባለው ግንኙነት መካከል አለመግባባት እንዲፈጠር ምክንያት የሚሆኑትንና እንዴትስ በመግባባት ልዩነቱን መቆጣጠር እንደሚቻል በስፋት ተወያዩበት?

11. ከዛሬ ጥናት የተማሩትና ያገኙት እንዲሁም ተግባራዊ እርምጃ ሊወስዱበት የሚገባ አንዱ ነገር ቢገልጹልን?

***መደምደሚያ***

እንግዲህ የአገር ቤትና አሁን የምኖርበት አገር የተለያዩ ባህል መገለጫዎች ተመሳሳይነትና የጎላ ልዩነት ሊኖራቸው ይችላል። በባህል ውስጥ ያሉ የአንድ አገር ባህል ሊገልጡ የሚችሉ የተለያዩ መገለጫዎች መኖራቸው በግልጽ መረዳት ተገቢ ነው። የአንድ አገር ባህል ሊገልጹ የሚችሉ የአለባበስና የአመጋገብ ሥርዓትና ወግ በመለየት እንደ ቃሉና ለሌሎች መሰናከል በማንሆንበት መንገድ ጥንቃቄ ማድረግን መለማመድ ተገቢ ነው።

ሌላው ሀዘን ሲገጥመን የምናስተናግድበት መንገድ ልንለወጥባቸው ከሚገቡን አንዱ ነው። ይህ ሲባል ማዘንን እናቁም ሳይሆን ራሳችንን ይበልጥ ለሌሎች ችግሮች ሊያጋልጠን በሚችል ያሉ እርምጃዎች ጥንቃቄ እንድንወስድ ለማሳሰብ ነው።

ሌላው በሥራ ላይና በቤተ ክርስቲያን የአምልኮና የአገልግሎት ጊዜ ያለን የተለያየ የጊዜ አጠቃቀም ባህል ነው። ይህ ልምምድ ለውጥ ከሚያሻን አንዱ ችግራችን ነው። ይህን የፈጠረብን ዋናው ተጠቃሽ ችግር ደግሞ ለጊዜ ያለን ዋጋና የጊዜ አጠቃቀም ባህላችን ነው። እጅግ በጣም ልናዳብረው የሚገባ ልምድና ባህል ቢኖር የአሳብ አንድነትንና ልዩነትን የምናጸባርቅበትና የምናስተናግድበት መንገድ ነው። የምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ የጌታ ቃል የተቃኘ መሆን እጅግ ተገቢ ነው።

## ጥናት 26
## ባህልና የመጽሐፍ ቅዱስ የበላይነት

### ዓላማ

በባህል ምክንያት የሚፈጠሩ አለመግባባትና ግጭት ወይም ልዩነት በመቀነስ በጋራ ለማምለክ፣ ለማገልገል፣ ለመኖርና አብሮ ለመስራት የምንችልበትን ልምድና ክህሎት ማሳደግ እንድንችል

### መግቢያ

ከቃሉ ጋር የማይቃረን ባህልን መለየትና ማዳበር መቻል ራሱን የቻለ ክህሎት ነው። ሁሉም ባህል ኃጢአትና ጽድቅ ነው በማለት መፈረጅ ባንችልም ጽድቅን ወይም አመጽን እንድንለማመድ ዕድል ሊሰጥ ይችላል። በእርግጥ አንዳንድ ባህሎች ከሰይጣን አምልኮና ሥርዓት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነትና ተጽዕኖ ሊኖራቸው ይችላል። የማንም ባህል ፍጹም አይደለም። ባህል በየጊዜው ሊለወጥና ሊሻሻል የሚችል ልምምድ ነው። ባህላችን ተምረን እንደተለማመድነው ሁሉ ልንረሳው ወይም በሌላ አዲስ ባህል ልንለውጠው እንችላለን። ከአሁን በፊት ስንለማመደው የነበሩ ባህሎች፣ አሁን የገጠመን አዲስ ባህል የሚፈጥረው ተጽዕኖ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በመንፈሳዊ ሕይወት፣ ከሌሎች ጋር ባለን መንፈሳዊ ኅብረት፣ አገልግሎትና ማኅበራዊ ግንኙነት እንዲሁም በዕለት ተዕለት ተግባራችን ባለው ምርጫና ውሳኔ በሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ ከጽድቅ መንገድ ሳንወጣ መኖር የምንችልበት ክህሎት ማሳደግ ይኖርብናል።

### በባህል ምክንያት የሚፈጠሩ ግጭቶችን በጋራ የመፍታት ክህሎት

1. ምንም ለባህሉ ነጻነት ቢኖረንም ልምምዳችን ሌሎችን በማያሰናክል መልኩ እንዲሆን ጥረት ማድረግ፡-1ኛቆሮ.8:1-13
2. ከመጽሐፍ ቅዱስ መርህ ጋር የማይጣረስ መሆኑን መፈተሽ፡- ሐዋ.15፡1-33
3. ችግሩንና በባህሉ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በመለየት ለመፍታት መዘጋጀት፡- ሐዋ.6:1-6
4. ከሃይማኖትና ከተለያዩ ነገሮች የተለመዱ ባህላዊነትና መንፈሳዊነት እየተወራረሱ ግራ እንዳያጋቡን መጠንቀቅ፡- ገላ.1:6-16፤ 6:12-16
5. አስቀድመን የሌሎችን ባህል ሳንነቅፍ አውዱን ጠብቀን ወደ ክርስቶስ ለማምጣትና እርሱን እንዲመስሉ መርዳት፡- ሐዋ.17:16-34

6. በመካከላችን ያለው ክርስቲያናዊ ግንኙነት ባህልን መሠረት በማድረግ ማቅረብና ማራቅ እንዳይኖር መጠንቀቅ መቻል፡- ቆላ.3:11

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. በባህል ልዩነት ምክንያት ሊፈጠሩ የሚችሉ የተለያዩ ሁኔታዎችና ገጠመኞች በመጥቀስ ተወያዩበት
2. እንደ 1ኛቆሮ.8:1-13 መሠረት አንዳንድ ባህሎችን መጽሐፍ ቅዱስ ቃል የማይጣረሱና ለእኛ ነጻነት ቢኖረን ልምምዳችን ለሌሎች ምን እንድናደርግ ይመክረናል? በዚህ ዘመን እንዲህ ዓይነት ጥንቃቄ አለ ወይ፣ ለምን?
3. እንደ ሐዋ.15:6 መሠረት በአይሁድና በአሕዛብ መካከል በተፈጠረው አለመግባባት በኢየሩሳሌም የነበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምን አደረጉ? ይህስ ልምምድ አስፈላጊ ነው ወይ ይላሉ?
4. እንደ ሐዋ.15:7-12 መሠረት በአይሁድና በአሕዛብ መካከል በተፈጠረው አለመግባባት ጴጥሮስ፣ በርናባስና ጳውሎስ በየተራ የግል ልምምዳቸውን መግለጽ መቻላቸው አስፈላጊ ነበር ወይ ? የሚሰጠውስ ፋይዳ ምንድን ነው?
5. እንደ ሐዋ.15፡-13-19 መሠረት በአይሁድና በአሕዛብ መካከል በተፈጠረው አለመግባባት በኢየሩሳሌም ተሰብስበው ለነበሩ የያዕቆብ ማስረጃ ምን ነበር? ምንስ ጥቅም አለው? ከዚህስ ምን መርህ ይማራሉ?
6. እንደ ሐዋ.6:1-6 መሠረት በቤተ ክርስቲያን መካከል በአንዳንድ ሥርዓቶችና ባህል ምክንያት የሚፈጠሩ ግጭቶችን ፈጥኖ መፍታት የሚያስፈልገብት ምክንያት ለምንድን ነው ይላሉ?
7. ገላ.1:6-16፣ 6:12-16 እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በማንበብ ባህላዊነትና መንፈሳዊነት እየተወራረሱ ግራ እንዳያጋቡን ልንወስዳቸው የሚገቡ ጥንቃቄ ይገልጹ
8. እንደ ሐዋ.17:16-34 መሠረት ከሐዋሪያ ጳውሎስ የወንጌል አገልግሎት የሌሎችን ባህል አውዱን ጠብቀን ወደ ክርስቶስ ለማምጣትና ክርስቶስን እንዲመስሉ መርዳት መቻል አለብን ይላሉ?
9. እንደ ቆላ.3:11-15 መሠረት በኅብረታችን መካከል ያለው ክርስቲያናዊ ግንኙነት ባህልን መሠረት በማድረጋችን ማቅረብና ማራቅ እንዳይኖር ምን ዓይነት ጥንቃቄ ልንወስድ

ይገባል?

10.ከዛሬው ጥናት የተማሩትና ልተገብረው የሚገባኝ ጥንቃቄ የሚሉትን አንዱን ያካፍሉ?

***መደምደሚያ***

በባህል እየኖርን ባህላዊነት ከመንፈሳዊ እውቀት፣ብስለትና ልምምድ ጋር እንዳይጋጭብን ጥንቃቄ ማድረጉ መልካም ነው። ምናልባትም በመካከል በሚፈጠሩ አለመግባባትና ግጭት በጋራ በመቀመጥ ለመነጋገር ራስን ከማዘጋጀት ይጀምራል። በውይይታችን ወቅት በመንፈሳዊ ሕይወት፣ ኅብረትና አገልግሎት ላይ እየፈጠረና ሊያመጣ ያለውን አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ መመዘን ተገቢ ነው። የግላችን ልምምድ መለዋወጥ ቢያስፈልግም ነገሮችን ከቃሉ አንጻር ማየትና ለእግዚአብሔር ክብር፣ ለቅዱሳን መታነጽ፣ ለሌሎች ወንጌል ለመመስከር እንቅፋት እንዳይሆንና የመንግሥትን መርህ የማይጣረስ መሆኑን ማረጋገጥ መቻል መንፈሳዊነት ነው። በዚህ ምክንያት በቤተ ክርስቲያን ባለው አገልግሎት እንቅፋት እንዳይፈጥር፣ ዋና የሆነውን የመንግሥቱን ሥራ ችላ እንዳይልብን፣ ኅብረታችን ለመለያየት ጠንቅ እንዳይሆንና በዚህ ምክንያት ሰዎች ከክርስቶስ እንዳይርቁና መምጣትም እንዳያግዳቸው ይብለጥ ልንጠነቀቅ ይገባል።

# ክፍል 10
# የመጨረሻው ዘመን
## ጥናት 27
## የክርስቶስ ዳግም ምጽዓቱ አጠቃላይ መግለጫ
## የንባብ ክፍል 2 ጴጥ 3:1-12
## ማሳሰቢያ፡- በዚህ ክፍል በዛ ያሉ ጥቅሶች ቢጠቀሱም መሪው የሚፈልገውን ብቻ ማስነበብ ይችላል።

### ዓላማ

የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትን በመረዳት አማኞችን ማነቃቃትና ግንዛቤ መጨመር መቻል

### መግቢያ

መጽሐፍ ቅዱስ የዘመንና የነገሮች ጅማሬ እንዳለው ሁሉ የዘመንና የነገሮች ፍፃሜም እንደሚኖር አጥብቆ ያስተምራል። ስለዚህ በዘመን ፍፃሜም ሊሆኑ ስለተቃረቡ እውነቶች በዝርዝር መረዳቱ ከመሠረታዊ የክርስትና እምነታችን አንዱና ዋናው ነገር ስለሆነ ይህንን ማወቅ የማንኛውም አማኝ ግዴታና የቤተ ክርስቲያንም ኋላፊነት ነው። የፍጻሜን ዘመን ስናስብ ሊታሰብባቸውና የሚገባቸው ወይም መልስ የሚያሻቸው ዋና ዋና ርዕሰ ጉዳዮች እንደሚከተሉት ናቸው፡-

- ስጋዊ ሞትና እስከ ትንሳኤ
- የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽዓት
- የአማኞች ንጥቀትና ታላቁ መከራ
- የሙታን ትንሳኤ
- የሺህ ዓመት መንግሥት
- የመጨረሻው ፍርድና የዘላለም

### የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ቤዛ በመሆን በመስቀል ለመሞት በተቃረበበት ወቅት ለደቀ

መዛሙርቱ እንዲህ ሲል “ እኔ ባለሁበት እናንተም ከእኔ ጋር እንድትሆኑ ልወስዳችሁ ዳግመኛ እመጣለሁ” የሐ.14:3።

1. **ምንነቱ**

ሀ) ከመጨረሻው ዘመን አንዱ የጌታ ዳግም ምጽአት መከናወን ነው።

ለ) ከትንሳኤው በኋላ ወደ ሰማይ በክብር ያረገውና በአባቱ ቀኝ የተቀመጠው ጌታ በትንሳኤው አካል ወደ ምድር መመለሱን ቃሉ ይገልጻል፡- ማር.14:62፣ ሉቃ21:27፣ ሐዋ.1:11

ሐ) ስለጌታ ዳግም መመለስ የተናገሩ

- ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሯል፡- ዮሐ.14:3
- መላዕክት ተናግረዋል፡- ማቴ.24:3፣ ሐዋ.1:11

መ) የጌታ ዳግም መምጣት ለአማኞች የተባረከ ተስፋችን ነው፡- ቲቶ 2:13

2. **የምፅዓቱን ጠቀሜታ በጥቂቱ ስንመለከት**

- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ትንቢታዊ ቃሎች የሚረጋገጡበት ነው - ማቴ 24፡ 44-46፣ ሉቃ 21፡34-36፣ ሐዋ 1፡11
- የክርስቲያኖች ተስፋ የሚጠናቀቅበት ነው ፡- ቲቶ 2፡13፣ ዮሐ 14፡1-5
- የክርስቲያኖች እንዲጽናኑ የዓለምን መከራ እንዲታገሱ የሚያደርግ ነው - 1ተሰ 4፡14

3. **የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምጻት እርግጠኝነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት**

ሀ) ስለ መጀመሪያ መምጣቱ የተነገሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች በሙሉ ተፈጽመዋል፡- ዮሐ.1:45

- ከዳዊት ዘር መወለዱ፣ በቤተ ልሔም መወለዱ፣ ከድንግል መወለዱ፣ ታምራታዊ በሆነ አገልግሎት ማገልገሉ
- በአህያ ወርንጫ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱ

- በሰላሳ ብር መሸጡ፣ ሕማማቱ፣ መሞቱ፣ መቀበሩና ትንሳኤው

ለ) የመመለሱ ተስፋ የተሰጠው በራሱ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ፡- ዮሐ.14:1-3

ሐ) ቅዱሳን መላዕክት ስለክርቶስ ዳግመኛ መመለስ መናገራቸው፡- ሐዋ.1:9-11

መ) ሐዋሪያት የክርስቶስን ዳግም ምጽአት፡-

- ሰብከዋል፡- ሐዋ.3:22
- በትምህርታቸውና በመልዕክታቸው አተኩረዋል፡-1ኛቆር.1:7፣ 2ኛተሰ.1:7-10፣ ቲቶ.2:13፣ 1ኛዮሐ.2:28፣ 2ኛጴጥ.1:16

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ስንል ምን ማለታችን ነው?
2. የመጨረሻው ዘመንና የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚያገናኛቸው ምንድን ነው?
3. ዮሐ.14:3 ፣ ማቴ.24:3 እና ሐዋ.1:11 ስለዳግም ምጻዓቱ ማረጋገጫ እነማን እንደተናገሩ በመግለጽ ተወያዩበት
4. ከታች የተጠቀሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በማንበብ የምፅዓቱ  ትምህርትና ዜና መስማት የሚሰጠው ጠቀሜታ ከመጽሐፍ ቅዱስ አንፃር በመግለጽ በስፋት ተወያዩበት ( ማቴ 24፡44-46፣ ሉቃ 21፡34-36፣ ሐዋ 1፡11 ፤ ቲቶ 2፡13፣ ዮሐ 14፡1-5 እና 1ተሰ 4፡14)
5. እንደ አማኝ የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም ምጽዓት እርግጠኛ ሆነን እንድንጠብቀው የሚያደርገን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት በመጥቀስ በስፋት ተወያዩበት ( ዮሐ.1:45፣ ዮሐ.14:1-3፣ ሐዋ.1:9-11)
6. የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ስለኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት የነበራቸውን ስብከትና ትምህርት በመጥቀስ ከአሁኑ ከእኛ ዘመን ጋር በማነጻጸር

ተወያዩበት ( ሐዋ.3:22 ፣ 1ኛቆር.1:7፣ 15:23፣ 2ኛተሰ.1:7-10፣ 2:1-8፣ 1ኛጢሞ6:14፣ 2ኛጢሞ.4:1-8፣ ቲቶ.2:13፣ ዕብ.9:28፣ ያዕ.5:5-7፣ 1ኛዮሐ.2:28፣ 1ኛጴጥ.1:2-13፣ 2ኛጴጥ.1:16 እና 2ኛጴጥ.3:4-12)።

7. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ለእኛ ለአማኞች ሕይወትና አገልግሎት ያለውን ፋይዳ በመጥቀስ ተወያዩበት ከዛሬው የጥናት ክፍል የተማራችሁትን አንድ አዲስ ነገር ያካፍሉ።

8. የክርስቶስን ዳግም ምጽዓቱ በውሉ ማወቅ ለወንጌል ሥርጭት ምን ዋጋ አለው? ምን እናድርግ?

### *መደምደሚያ*

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ከቅዱስ ቃሉ በመማርና በማጥናት እንደሚገባ መረዳት መቻል ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ትልቅ መልኅቅ ነው። በተጨማሪም የጌታን ምጽዓት እውቀት እንደሚገባ መጨመራችን ክርስትናን በደስታና በጉጉትና ሊገለጥ ያለውን ተስፋ እያሰቡ በመከራ መጽናት የሚቻልበት አቅምና መሠረት በመሆኑ ነው። ይህን የጌታን ዳግም መምጣት ናፍቆት የግል አቋምና ልምምድ እንዲሁም የየዕለት ስብከታችንና ትኩረታችን ሊሆን ይገባል። በጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የነበሩበት ዘመን የመጨረሻ ዘመን እንደሆነና የጌታን ዳግም ምጽአት በናፍቆት እንደጠበቁና እንደሰበኩ ሁሉ እኛም ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ቅርብ ምጽዓቱ መሆኑን በመገንዘብ በጽድቅና በቅድስና እንዲሁም የተሰጠንን የወንጌል ኃላፊነት በመወጣት እንመላለስ ይገባል።

## ጥናት 28

## የዳግም ምጻቱ ሁኔታዎች

### ማሳሰቢያ፡- በዚህ ክፍል በዛ ያሉ ጥቅሶች ቢጠቀሱም መሪው የሚፈልገውን ብቻ ማስነበብ ይችላል።

### ዓላማ

ኢየሱስ ክርስቶስን በምን ዓይነት ሁኔታ ዳግም ይመለሳል የሚለውን በመገንዘብ በንቃትና በትጋት መጠበቅ እንድንችል ማስገንዘብ ነው።

### መግቢያ

የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መምጣት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ነው (ማርቆስ 13፥26፣ ሉቃስ 21፥27)። የጌታን ዳግም መመለስ ለማረጋገጥ ቀደም ብሎ የመጀመሪያ ስጋ ለብሶ ስለመምጣቱ ትንቢቶች መፈጸማቸውና የመስቀሉንና የትንሳኤ ሥራ አከናውኖ ማረጉ ማረጋገጫችን እንደሆነው ሁሉ ዳግም መመለሱ አይቀሬ ነው። ዳግም ምጻቱን የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሰብከዋል፣ አስተምረዋል ደግሞም በእነርሱ ዘመን መመለሱን ናፍቀው አልፈዋል። በእኛ ዘመን ዳግም መመለሱን የሚያሳዩ ብዙ ምልክቶች በቃሉ እንደተጻፉ እየተፈጸሙ ይገኛሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ በእርግጥ ዳግም ይመለሳል ነገር ግን እንዴት ሆኖ ይመጣል የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት መረዳት በንቃት ለመጠበቅ ይረዳናል።

### ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም የሚመጣባቸው ሁኔታዎች

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም እንደሚመጣ ቃሉ ቢናገርም መቼ እንደሚመጣ በግልጽ ቀኑና ሠአቱን እንደማይታውቅ ራሱ ጌታ ኢየሱስ ይናገራል። ማቴ.24:36 የሚመጣበትን ቀንና ሠዓት ራሱ ጌታ፣ መላዕክቱና ደቀ መዛርቱ ሊያውቁት እንደማይችሉ ይናገራል።

### የሥውር አመጣጡ ምክንያትና ምላሽ

**1) አመጣጡ**

- በቶሎ/ በቅርብ/ ፡- ራዕይ 22:7, 11፣ እንደ ሌባ፡- 1ኛተሰ.5:2፣ ራዕ.16:15፣ በድንገት/ ባልታሰብ ሠዓት/፡- ማቴ.24: 44

**2) ምክንያቱ**

- አማኞችን ለመውሰድ፡- ዮሐ.14:2-3፣ ያንቀላፉ አማኞች ትንሳኤ እንዲያገኙ፡-

1ኛቆሮ.15:23፣ 1ኛተሰ.4:15-17

- በቅዱሳኑ ዘንድ ሊከብር፣ በሚያምኑት ዘንድ ሁሉ ሊገረም፡-2ኛተሰ. 1:10 ፣አማኞችን ከታላቁ መከራ ለማዳን፡- 1ኛተሰ.1:10፣ ራዕ.3:10፣ ለእያንዳንዱ አማኝ እንደ ሥራው ዋጋ ለመክፈል፡-1ኛቆሮ.4:15፣ 2ኛቆሮ.5:10፣ 2ኛተሰ.1:7

**3) የአማኞች አጠባበቅ ሁኔታ**

- ነቅተን መጠበቅ፡- ማቴ.24:42፣ ሉቃ.12:35-42፣ ተዘጋጅተን መኖር/ ዝግጁ መሆን/ ማቴ.24:44
- ተግተን መጠበቅ፡- ማር.13:37፣ በአግባቡ መመላለስ፡- ሮሜ.13:11-14፣ ራሳችን በመግዛት መኖር፡- 1ኛተስ.5:4-8

**በግልጽ አመጣጡና ምክንያቱ**

**i. አመጣጡ**

- እየታየ፡- ሐዋ፣1:11፣ ራዕይ. 1:7 ፣በደመና፡- ማቴ.24:30፣ በአባቱ ክብር፡- ማቴ.25:31፣ በእሳት ነበልባል፡- 2ኛተሰ.1:6-7
- በኃይልና በብዙ ክብር፡- ማቴ24:30፣ ከመላዕክቱ ጋር ማር.8:38፣ ከቅዱሳን ጋር 1ኛተሰ3:13፣ ይሁዳ 14-15

**ii. የመምጣቱ ምክንያት**

- የክርስቶስን ተቃዋሚ ለመሻር፡- 2ኛተሰ.2:8
- አመጻኞችን ለመበቀል/ በአህዛብ ለመፍረድ/፡- ማቴ.24:31፣ 25:32-46፣ 2ኛተሰ.1:8 እና ይሁዳ.15

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. እንደ ማቴ.24:36 መሠረት ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለራሱ ዳግም መመለስ ቀንና ሠዓት ምን ይላል? እንዲህ ሲልስ ከአምላክነቱ ባህርይ ጋር እንዴት ታስታላችሁ?
2. በእነዚህ ቃል መሠረት (ራዕይ 22:7, 11፣ 1ኛተሰ.5:2፣ ራዕ.16:15፣ ማቴ.24: 44) ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥውር አመጣጡን መጽሐፍ ቅዱስ በምንና እንዴት ይገልጸዋል ?
3. ከታች የተገለጹትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በማንበብ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥውር የሚመጣበትን ምክንያት በግልጽና በስፋት ተወያዩበት 1ኛተሰ.4:15-17፣

1ኛቆሮ.4:15፣

4. የጌታ ኢየሱስ በሥውር ዳግም ምጽአት አማኞች እንዴት መጠበቅ እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል? ማቴ.24:42-44፣1ኛተስ.5:4-8
5. የጌታ ኢየሱስ በግልጽ ዳግም መምጣቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታው ምንድን ነው?
6. ከታች የተዘረዘሩትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በመጥቀስ የጌታ ኢየሱስ በግልጽ ዳግም መምጣቱን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ ያስረዳል? ሐዋ፣1:11፣ ራዕይ. 1:7፣ ማቴ.24:30፤ ማር.8:38፤ 1ኛተሰ3:13
7. የጌታ ኢየሱስ በግልጽ ዳግም የመምጣቱን ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ይገልጸዋል? 2ኛተሰ.2:8፣ ማቴ24:21-22 ፣ራዕ.0:4-6
8. የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም በሥውርና በግልጽ መምጣቱ ለአንተ ለሕይወትና ለአገልግሎት የሚሰጥህ ፋይዳ ምንድን ነው?
9. ከዛሬው የጥናት ክፍል ምን አዲስ ነገር እንደተማራቹሁ ለቡድኑ አባላት ያካፍሉ

***መደምደሚያ***

የኢየሱስ ክርስቶስ በስውር በቶሎ/ በቅርብ/፣ እንደ ሌባና በድንገት/ ባልታሰብ ሠዓት ይመጣል። ኢየሱስ ዳግም የሚመጣውም እኛን አማኞችን ለመውሰድ፣ ያንቀላፉ አማኞች ትንሳኤ እንዲያገኙ ፣ በቅዱሳኑ ዘንድ ሊከብር፣ በሚያምኑት ዘንድ ሁሉ ሊገረም ፣ አማኞችን ከታላቁ መከራ ለማዳንና ለእያንዳንዱ አማኝ እንደ ሥራው ዋጋ ለመክፈል ነው። እኛ አማኞች በአግባቡ በመመላለስ፣ ራሳችንን በመግዛት፣ በንቃትና በትጋት ልንጠባበቀው ይገባል። በስውር ብቻ ሳይሆን ሁለተኛም በግልጥ እየታየ በደመና በአባቱ ክብር ፣ በእሳት ነበልባል ፣ በኃይልና በብዙ ክብር ፣ ከመላዕክቱ ጋርና ከቅዱሳን ጋር የክርስቶስን ተቃዋሚ ለመሻር፣ የአርማጌዶዮን ጦርነት በድል ለመፈጸም ፣ እስራኤልን ለማዳን ፣ አመጻኞችን ለመበቀል/ በአህዛብ ለመፍረድ/ እና አንድ ሺህ ዓመት በምድር ከሕዝቡ ጋር ለመንገስ ይመጣል።

## ጥናት 29

## የዳግም ምጽዓቱ ምልክቶች

### ማሳሰቢያ፡- በዚህ ክፍል በዛ ያሉ ጥቅሶች ቢጠቀሱም መሪው የሚፈልገውን ብቻ ማስነበብ ይችላል።

### ዓላማ

የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ምልክቶችን በመረዳት በጽድቅና በቅድስና እንዲሁም በንቃትና በትጋት ክርስትናን መኖር እንድንችል ለማሳሰብ ነው።

### መግቢያ

የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ነው። ይህን እውነት በቅዱስ ቃሉ በተለያየ ቦታ ተገልጾ እናገኛለን። ይህን እውነት አርሱ ጌታ በምድር በነበረው ቆይታ በተደጋጋሚ የገለጸውና ደቀ መዛሙርቱን ያጽናናበት ተስፋ ነው። ከጌታ ባሻገር የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች የሰበኩትና ያስተማሩት እንዲሁም አማኞችን ያስጠነቀቁበት መሠረታዊ የክርስቲያን ትምህርትና ተስፋ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መምጣት በፊት ሊከናወኑ የሚገባቸው የተለያዩ ምልክቶች በተለያዩ ቦታዎች መፈጠራቸው ይጠቁማል። ይህን ደግሞ አስቀድሞ በነብያት፣ በራሱ በጌታ በኢየሱስና በሐዋሪያቱ በተደጋጋሚ የተገለጹ መሆናቸው ነው። የኢየሱስ ክርስቶስን ዳግም መምጣቱ ጋር ተያይዞ ያሉ ልዩ ልዩ ምልክቶች እና ምልክቶችን አስቀድሞ የመረዳትና መለየት ያለውን ጠቀሜታና የአማኞችን ኃላፊነት በመዘርዘር የሚያስቃኝ ጥናት ነው።

### የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም የመምጣቱ ምልክቶች

1. **በቤተ ክርስቲያን የሚታዩ ምልክቶች**

   ሀ) በአመጽ ምክንያት የፍቅር መቀዝቀዝ ፡- ማቴ.24:12

   ለ) የሐሰተኛ ክርስቶሶች/ነብያት/ መነሳትና ታላቅ ምልክቶች /ድንቆች ማድረግ/፡- ማቴ.24:24 እና 1ኛጢሞ.4:1-3

   ሐ) የሚያስጨንቅ ዘመን መምጣትና ስለዚያ ዘመን የተሰጡ ምልክቶች፡- 2ኛጢሞ.3:1-8

**2. ከቤተ ክርስቲያን ውጭ የሚታዩ ምልክቶች**

ሀ) ጦርነትና የጦር ወሬ መሰማት፡- ማቴ.24:6

ለ) የሕዝብ በሕዝብ፣ መንግሥት በመንግሥት ላይ መነሳት፡- ማቴ.24:7

ሐ) የኖህና የሎጥ ዘመን ምልክቶች መታየት፡- ሉቃ.17:26-30

መ) የምርምርና የእውቀት መብዛት፡- ዳን.12:4

**3. በእስራኤል ላይ የሚሆኑ ምልክቶች**

ሀ) የእስራኤል ሕዝብ ከተበተኑበት ወደ ምድራቸው መሰብሰባቸው፡- ሕዝ.36:24፣ 37:21 እና ኤር.31:10

ለ) የእስራኤል መንግሥት መመሥረትና የአህዛብ ዘመን ፍጻሜ መቅረብ፡- ሉቃ.21:24

ሐ) ባድማ የነበረው የእስራኤል ምድር መለምለም፡- ሕዝ.36:8-15

**4. በተፈጥሮ ውስጥ የሚታዩ ምልክቶች**

ሀ) ረሃብ፣ ቸነፈርና የምድር መናወጥ በልዩ ልዩ ሥፍራ መሆንና እየጨመረ መሄድ፡- ማቴ.24:7

ለ) በሰማይ ላይ የሚሆኑ የሚያስፈሩ ነገሮችና ምልክቶች መታየት፡- ሉቃ.21:11

**ምልክቶችን ማወቅ የሚሰጠው ጠቀሜታ**

- እስራኤልና አህዛብ እግዚአብሔርን ያውቁ ዘንድ፡- ሕዝ.36:11, 23, 36, 38፣ ሕዝ.37:13, 14, 28
- አማኞች የጌታ ዳግም መምጣት እንደ ደረሰ እንዲያውቁ፡- ማቴ.24:32-33
- አማኞች በጌታ ሥራ በመጠመድ እንዲኖሩ፡- ማቴ.24:45-51
- አማኞች በጸሎት በመትጋት እንዲኖሩ፡- ሉቃ.21:36

- አማኞች ሊሆኑ ካሉት መጥፎ ነገሮች ራሳቸውን በመጠበቅ እንዲኖሩ፡-
2ኛጢሞ.3:10-11, 14

**በዳግም ምጽአት የአማኞች ኋላፊነት፣ ድርሻና አጠባበቅ**

- ወንጌልን መስበክ ሥራ በማድረግ
- በንቃት በጽድቅና በቅድስና በመጠበቅ

**የመወያያ ጥያቄዎች (የሁለት ቀን ጥናት ማድረግ ትችላላችሁ)**

1. የሚከተሉትን ጥቅሶች በማንበብ የጌታን ዳግም ምጽዓትን በተመለከተ በቤተ ክርስቲያን መካከል የሚታዩ ምልክቶችን በመጥቀስ በስፋት ተወያዩበት
    - ማቴ.24:12፣ 24፣
    - 2ኛጢሞ.3:1-8
2. የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት በማድረግ ስለ ዳግም ምጽዓት ከቤተ ክርስቲያን ውጭ የሚታዩ ምልክቶች ምንድን ናቸው? ተፈጻሚነታቸውስ እንዴት ታዩታላችሁ?
    - ማቴ.24:6-7
    - ሉቃ.17:26-30
3. ስለ ዳግም ምጽዓት በተፈጥሮ ውስጥ የሚታዩ ምልክቶችን በመጥቀስ ተፈጻሚነታቸውን እያረጋገጣቹህ ተወያዩበት
    - ማቴ.24:7
    - ሉቃ.21:11
4. ከታች የተጠቀሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በመሠረት በማድረግ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መምጣት ምልክቶች ማወቅ የሚሰጡን ጠቀሜታ በመዘርዘር ተወያዩበት
    - ማቴ.24:32-33
    - 2ኛጢሞ.3:10-11, 14

5. ለኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ምልክቶችን በመረዳት መኖርና መመላለስ ሂደት የእኛ የአማኞች ኃላፊነት፣ ድርሻና አጠባበቅ ምን ሊሆን ይገባል ትላላችህ? በተለይም የወንጌል አገልግሎትን በተመለከተ ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?

6. በእርስዎ መረዳት የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መምጣት ጊዜ በቅርብ ወይስ በሩቅ ነው ይላሉ ? ከሆነስ ለምን?

7. ከዛሬው የጥናት ክፍለ ጊዜ የተማሩት አንድ አዲስ መረዳትና ተግባራዊ ርምጃ በመጥቀስ ለቡድኗ ያካፍሉ?

***መደምደሚያ***

የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መምጣቱ በመቼ ጊዜ፣ ሠዓትና ደቂቃ እንደሆነ ባናውቅም የመጣቱ ተስፋ ግን በብዙ ምልክቶችና ማረጋገጫዎች የተረጋገጠ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታ ነው። በተለያዩ ጊዜያትና ቦታዎች እየተፈጸሙ ያሉ የተለያዩ ምልክቶች እኛን ይበልጥ ሊያዘጋጁን፣ ሊያነቁንና ሊያተጉን ይገባል። ሌላው በዚህ የመጨረሻ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየታየ ያለው የመንፈሳዊ ሕይወት መቀዝቀዝና መነቃቃት መጥፋት፣ ከእውነተኛ ሕይወትና አገልግሎት በላይ የቅድስና መለኪያ በወረደበትና ደቀ መዝሙርነት በጠፋበት እንዲሁም የእውነት አገልጋዮች ቁጥር እየመነመነ በመጣበት ወቅት ከእውነት ጋር መወገን፣ ዋጋ መክፈልና ማስቀጠል የእያንዳንዳችን መርህ ሊሆን ይገባል። በእኛ በአማኞች መካከል የጠፋው በቅድስና ሕይወት መመላለስና ለወንጌል የሚከፈለውን ዋጋ በመክፈል ለሌሎች ማዳረስ እንዲሁም አሳድጎ ተተኪ በማፍራት ረገድ ከፍተኛ የሆነ ጥረትና ትጋት ሊጨምርብን ይገባል።

## ጥናት 30

## የመጨረሻው ፍርድ

## ማሳሰቢያ፡- ሁሉንም ጥቅሶች ማንበብ አይጠበቅባቸውም።

### ዓላማ

በመጨረሻው የመጨረሻ ፍርድ መኖሩን በመገንዘብ ከወዲሁ የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መምጣት እርግጠኝነቱን በማመን ራስን በጽድቅና በቅድስና መመላለስ የሕይወት መርህ እንድናደርግ ለማነሳሳት

### መግቢያ

ሰው ሁሉ ለሠራው ሥራ መጠየቁና በአምላክ ፊት ለፍርድ መቆሙ አይቀሬ ነው (2ቆሮ.5:10) ። ፍርድ መኖሩ ደግሞ ሰው እንዲኖርበት ከአምላክ የተሰጠ ሕግ፣ መሥፈርትና መለኪያ መኖሩን ያሳያል። ይህ የመጨረሻው ፍርድ እስከ አሁን ያልነበረና ያልተከናወነ ወደፊት የሚፈጸም ፍርድ ነው (ኢሳ 9:7)። የመጨረሻ ፍርድ ጻድቅ ፈራጅ በሆነው በአምላክ በመሆኑ የሰው ልጅ በንግግር፣ በማስመሰልና በተዛባ መስፈርት ሊሰውረው የሚችለው ነገር አይኖርም። ይህ የመጨረሻው ፍርድ የሚሰጠው ሰው የዘራውን የሚያጭድበትና የአምላክ ጻድቅ ፈራጅነትም የሚታይበት ወቅት ነው ( ሮሜ 14:10)።

### የመጨረሻው ፍርድ ምንነት

1. የመጨረሻ ፍርድ እስከ አሁን ድረስ ያልሆነና የእግዚአብሔር ቃል ወደፊት ከሚሆኑት ትንቢቶች አንዱ መሆኑን የሚነግረን ነው
2. በብሉይ ኪዳን ሆነ በአዲስ ኪዳን ( በቤተ ክርስቲያን) ዘመን ያልሆነ
3. የአህዛብን ፍርድና የታላቁ የነጩ ዙፋን ፍርድ የሚያመለክት ስለሆነ ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በኋላ እንደሆነ ያመለክታል (1ዮሐ 4፥17 )።

### የመጨረሻው ፍርድ አስፈላጊነት

1. የድነት ቃል ኪዳን አንዱ ክፍል ስለሆነ ራዕይ 21:1-6
2. ሰው የዘራውን ያኑን ማጨድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ስለሆነ፡- ገላ.6:7-8
3. እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ መሆኑን ስለሚያሳይ፡- 1ኛጴጥ.1:17፣ ሮሜ.2:11፣ ቆላ.3:25

### በእነ ማን ላይ ይፈርዳል?

1. በመላዕክት ይፈረድባቸዋል፡- በእግዚአብሔር ላይ በአመጹ መላዕክት በእግዚአብሔር የፍርድ ቀን ባደርጉት ኃጢአት ይፈረድባቸዋል፡- ይሁዳ.6፣ 2ኛጴጥ.2:4፣ ማቴ.12:24-27፣ ማቴ.25:41
    - ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመለስ ሰይጣን ተይዞ ለሺህ ዓመት ይታሠራል፡- ራዕይ 20:1—10
    - በመጨረሻም ወደ ዲን እሳት ባህር ይጣላል፡- ራዕ.12:7-12፣ ማቴ.25:41፣
2. ባላመኑት ላይ ይፈረዳል፡- በክርስቶስ ያላመኑት ሰዎች የቅጣታቸው መጠን የተለያየ ሲሆን በመጨረሻም ፍርድ ይጠብቃቸዋል፡- ሮሜ.2:5-7፣ ማቴ.11:24፣ ሉቃ.20:47፣ ራዕ.20:12-13

**የፍርድ ዓይነቶች**

1. **የታላቁ መከራ ፍርድ**
    - ታላቁ መከራ እስከዛሬ ሆኖ የማይታወቅ መከራ የሚሆንበት ጊዜ
    - ሰይጣን አስከፊ መከራውን በቅዱሳንና በእስራኤላዊያን ላይ የሚያመጣበት ጊዜ ነው
    - በተጨማሪ ሰዎች የኃጢአተኝነታቸው ባህርይ ከፍተኛ ደረጃ ስለሚደርስ ኃጢያታቸው የእግዚአብሔርን ፍርድ ይልክባቸዋል።
    - በምድር ያሉት በተለያዩ መቅሰፍቶች የሚሰቃዩበት ነው፡- ራዕ.4:19፣ ራዕ. 16:12-17
2. **የአህዛብ ፍርድ**
    - ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር ሲመለስ አህዛብ ሁሉ በፊቱ ተሰብስበው ለወንድሞቹ( ለእስራኤል ልጆች) መልካምና በጎ ነገር ያደረጉት ወደ ሺህ ዓመት የሚያልፉበት ሌሎች ደግሞ የሚፈርድባቸው ማቴ.25:31-45
3. **የታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ**
    - የታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ በራዕይ 20፡11-15 ላይ ተገልጿል፣
    - እሱም የፍጻሜው ፍርድ ሥርዓት ነው፣ የጠፉት ወደ እሳት ባሕር የሚጣሉበት፡- ከራዕይ 20፡7-15
    - ይህ ፍርድ የሚከናወነው ከሺ ዓመት መንግስት በኋላ ነው፣
    - እንዲሁም ሰይጣን፣ አውሬው፣ እና ሐሰተኛው ነቢይ ወደ እሳት ባሕር ከተጣሉ በኋላ (ራዕይ 20፡7-10)።

- የተከፈቱት መጽሕፍት (ራዕይ 20፡12) የእያንዳንዱን ሰው ሥራ ይዘዋል፣ መልካም ቢሆን ወይም ክፉ፣ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ከማወቁ የተነሣ፣ የተባለውን፣ የተደረገውን፣ ወይም የታሰበ እንኳ ቢሆን፣ እሱም ያስሸልማል ወይም ያስቀጣል (ሮሜ 2:6፤ ራዕይ 2:23፤ 18:6፤ 22:12)።
- በማያምኑ ላይ ዘላለማዊ ቅጣት የሚያመጣ የመጨረሻ ፍርድ ነው፡-በራዕይ 20፡ 11-15 አማኞችም ደግሞ በክርስቶስ ይፈረድባቸዋል፣ ነገር ግን የክርስቶስ ጽድቅ ወደ እኛ በመተላለፉ ምክንያት እና ስማችን በሕይወት መጽሐፍ በመጻፉ፣ እንሸለማለን እንጂ አንቀጣም፣ እንደ ሥራችን ሁኔታ። ሮሜ 14፡10-12 እንደሚለው፣ ሁላችንም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለን፣ እናም እያንዳንዳችን ለእግዚአብሔር ምላሽ እንሰጣለን።

**የመወያያ ጥያቄዎች**

1. የመጨረሻው ፍርድ ስንል ምን ማለት ነው? መቼ ነውስ የሚከናወነው?
2. እንደ ገላ.6:7-8፣1ኛጴጥ.1:17፣ ሮሜ.2:11፣ ቆላ.3:25 የመጨረሻው ፍርድ መኖር አስፈላጊ ነው ወይ? ከሆነስ ለምን ያስፈልጋል?
3. የእግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅነት ከምድራዊ ፈራጆች ጋር በማነጻጸር ተነጋገሩበት?
4. በመጨረሻው ፍርድ እግዚአብሔር በእነማን ላይ ይፈርዳል?
5. በመጨረሻው ፍርድ እግዚአብሔር በመላዕክት ይፈረድባቸዋል ሲል በየትኛውቹ መላዕክት ማለቱ ነው? ለምን? የፍርዱስ መጨረሻ ምንድን ነው?
   - ራዕ.12:3-4፣
   - ይሁዳ.6፣
   - 2ኛጴጥ.2:4፣
   - ማቴ.12:24-27፣
6. በመጨረሻው ፍርድ በክርስቶስ ባላመኑት ላይ ይፈርዳል ሲል ምን ማለቱ ነው? የሚፈርዳባቸውስ እንዴት ነው?
   - ሮሜ.2:5-7፣
   - ሉቃ.20:47፣
   - ራዕ.20:12-13፣
7. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ የተለያዩ የፍርድ ዓይነቶች በመጥቀስ ተነጋገሩ ?

ምንነታቸውን፣ የፍርዳቸው መጠን በመጥቀስ በስፋት ተወያዩበት

- የታላቁ መከራ ፍርድ፡- ራዕ. 16:12-17፣ 19:11
- የአህዛብ ፍርድ፡- ማቴ.25:31-45

●የታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ ፡- በራዕይ 20፡11-15

- የመጨረሻው ፍርድ ስታስቡ ምን እርምጃ እንድትወስዱ ያነሳሳችኋላ? ምንስ ትማራላቹህ?
- በዚህ የጥናት ክፍለ ጊዜ አዲስ የተማራቹትና እርምጃ ለመውሰድ የተነሳሳቹበት አንድ ነገር ያካሉ?

***መደምደሚያ***

የተባረከ ሕያው የሆነ የጌታችን ዳግም ምጽአት ብቻ ሳይሆን የመጨረሻው ፍርድ እንዳለና አማላክችን ጻድቅ ፈራጅ መሆኑን መገንዘብ የሕይወት ሚዛን በመጠበቅ እንድኖር ያግዘናል። እግዚአብሔር የመጨረሻ ፍርድ እንዳለውና በመላዕክት፣ በማያምኑና በአማኞችም እንደሚፈርድ በመገንዘብ የክርስትናን ሕይወት እስከ መጨረሻው ከጌታ ጋር ሆነን እንድንዘልቅ ያስጠነቅቀናል። በተለያዩ አካላት መፍረድ ብቻም ሳይሆን የተለያዩ የፍርድ ዓይነቶችም እንዳሉ በመረዳት የፍርድ ዓይነትና መጠን በግልጽ በመለየት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ይዘን እንድንቆም ያግዘናል።

## ጥናት 31

## ዘላለም

**ማሳሰቢያ፡-**

1. *መሪያችን የሚለውን በበመስማት የሁለት ቀን ጥናት ማደረግ እንችላለን*
2. **በክፍሉ የተጠቀሱትን ሁሉንም ጥቅሶች ማንበብ አይጠበቅባቸውም።**

**ዓላማ**

ከጊዜያዊ ደስታና እርካታ ይልቅ ለዘላለም በአዲሷ ሰማይና ምድር ለዘላለም መኖራችን እያሰብን በጽናት መጠበቅ እንድንችል ለማስገንዘብ ነው።

**መግቢያ**

የነገሮች መጀመሪያ እንዳላቸው ሁሉ መጨረሻም አላቸው። የሰው ሕይወት በመወለድ ጀምሮ በሥጋ ሞት ምድራዊ ቆይታው ይጠናቀቃል። ምንም የምድር ሕይወት ቆይታ በእድሜ የተገደበ ቢሆንም ነፍስ ከአምላክ እስትንፋስ የተገኘች በመሆኗ ሥጋ ወደ አፈር ሲመለስና በትንሳኤ ጊዜ የማይበሰበስ አካል በመልበስ ለዘላለም ከአምላክ ጋር እንኖራለን። ይህን ደግሞ ለእኛ ለአማኞች በዚህ ምድር በሚገጥመን የተለያዩ የሕይወት ውጣ ውረዶችና ተገዳሮቶችን በመታገስ እንድንጸና አቅም የሚሰጠን የክርስትና እውነት ነው። ከጊዜያዊ ይልቅ ዘላለማዊ፣ ከምድራዊ ይልቅ ሰማያዊ፣ ከአርጌው ሰማይና ምድር ይልቅ አዲስቷን ኢየሩሳሌም በናፍቆት፣ በጽድቅና በትጋት እንድንጠብቅ ያነሳሳናል።

**ዘላለም**

1. **ምንነት**

የመጨረሻው ፍርድ በነጩ ዙፋን ላይ በተቀመጠው በክርስቶስ ኢየሱስ ፈራጅነት ተከናውኖ ሰይጣንና ርኩሳት መናፍስት ደግሞም ሙታን ( የሁለተኛው ሞት ተካፋዮች) ወደ እሳት ባህር ከተጣሉ በኋላ ዘላለማዊ ኹነት( ኑሮ) ይጀመራል።

2. **የጻድቃንና የኀጢአን የመጨረሻ ሁኔታ**

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጻት የብሉይና የአዲስ ኪዳን ቅዱሳን ከሙታን ተነስተው በሕይወት የነበሩትም ተለውጠው፣ የታላቁ መከራ ቅዱሳንና የእስራኤል ልጆች (ክርስቶስን የተቀበሉ) ትንሳኤ አግኝተው ሺህ ዓመት ከክርስቶስ ጋር እንደሚነግሱ ተመልከተናል።

**3. አዲስ ሰማይና ምድር**

ሀ) አዲስ ሰማይና ምድር ከመሆኑ በፊት የመጀመሪያው ሰማይና የመጀመሪያቱ ምድር ያልፋሉ

ለ) አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ከመፈጠሩ በፊት የመጀመሪዎቹ ሰማይና ምድር በእሳት ሊጥፉ ተጠብቀዋል

ሐ) አዲስ ሰማይና ምድር ክፉ ነገሮች የማይኖሩባት ሥፍራ ናት ፡- ራዕ.21:8, 27

መ) የእግዚአብሔር መገኛ ሥፍራ ናት፡-

- እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ይሆናል፡- ራዕ.21:3
- የእግዚአብሔር ታላቅ ክብር የሚያንጸባርቅባት ሥፍራ ናት
- በእግዚአብሔር ክብር ደምቃ ታበራለች። በጉ ራሱ መብራቷ ስለሆነ፡- ራዕ.21:11, 23
- አሥራ ሁለት በሮች ያሏትና እያንዳንዱ በር በእስራኤል ነገዶች ስም ተሰይመዋል። እያንዳንዱ በር በአንድ አንድ መላዕክት ይጠብቃል፡- ራዕ.21:12-31፣ ዕብ.1:14፣ዮሐ.4:22
- የከተማይቱ መሠረት ከውድና ከከበሩ ድንጋዮች የተሠሩ ሲሆኑ በአሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋሪያት ተሰይመዋል፡- ራዕ.21:18-14፣ 19:20፣ ኤር.2:2
- መንገዶቿ በንጽሕ ወርቅ ተሠርተዋል፡- ራዕ.21:18-21
- በከተማይቱ ውስጥ ጌታ አምላክ (በጉ) መቅደስ ስለሆነ ሌላ መቅደስ የለባትም፡- ራዕ.21:22-23፣ 22:4

ሠ) የቅዱሳን የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ፡-በአዲስ ሰማይና ምድር መኖር

- ቅዱስን እግዚአብሔር እያመለኩ በበጉ ክብር ተሞልተው ለዘላለም ይኖሩባታል፡- ራዕ.21

- በፍጹም ጤንነት፣ ሕመምና ደዌ፣ ሞትና መበስበስ በማይሆንበት የትንሳኤ አካል ለዘላለም ይኖራሉ፡- ራዕ.21:4
- በዘላለማዊና በማያቋርጥ ደስታ ይኖራሉ፡- ራዕ.21:4፣ ሮሜ.8:18-25
- ሁሉ የእነርሱ ይሆናል፡- ራዕ. 21:7
- ሰው የተፈጠረበትን ትልቁና ዋና ዓላማ የሆነውን የአምልኮ አገልግሎት እየሰጡ ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም ይኖራሉ። ራዕ.22:3፣ ዕብ.12፡ 22-22-24

ር) የኃጢአን የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ

- በሁለተኛው ትንሳኤ ከሙታን ይነሳሉ
- በታልቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ ላይ የተቀመጠው ክርስቶስ ይፈረድባቸዋል
- ወደ እሳት ባህር ( ሁለተኛው ሞት) ይጣላሉ። ይህም ዲያብሎስን፤ ርኩሳንን ይጨምራል
- የኃጢአን የመጨረሻ ኑሮ
- ኃጢአን ከክርስቶስ ውጭ ወደሆነው ወደ ዘላለም እሳት ይሄዳሉ፡- ማቴ.25:41
- ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወደሆነበት ወደ ጨለማ ይጣላሉ፡- ማቴ.8:12
- ከእግዚአብሔር ቁጣ በታች መውደቅ፡- ሮሜ.2:5
- ለዘላለም ጥፋት መቀጣት፡- 2ኛተሰ.1:9
- በእሳት በዲን መሰቃየት ወይም መጣል፡- ራዕ.14:10-11፣ 21:8

***የመወያያ ጥያቄዎች***

1. ዘላለም ስንል ምን ማለታችን ነው? መቼ ይጀምራል?
2. በዚህ የዘላለም ኑሮ የሚካተቱ ጻድቃን እነማን ናቸው? ከየት ጀምሮ ያሉትንስ ያጠቃልላል?

3. እንደ ራዕ.21:8, 27 መሠረት አዲስ ሰማይና ምድር ምንድን ነው? አዲስ ሰማይና ምድር ከመምጣቱ በፊት አሮጌው ሰማይና ምድር ምን ይሆናል?

4. እንደ ራዕ.21:3፣ 11-31 መሠረት አዲስ ሰማይና ምድርን እንዴት እንደሚገልጣት በማብራራት ተወያዩበት

5. በዚሁ ክፍል መሠረት የቅዱሳን የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ ምንድን ነው? ምንስ ይሆንላቸዋል?

6. በሚቀጥሉት ጥቅሶች መሰረት የኃጢአን የመጨረሻ ዕጣ ፈንታስ ምንድን ነው?

- ማቴ.25:41
- ማቴ.8:12
- 2ኛተሰ.1:9
- ራዕ.14:10-11፣ 21:8

7. አማኞች በአዲሷ ሰማይና ምድር ለዘላለም መኖርን ትምህርት መስማት፣ መማርና ማጥናት የሚሰጠው ፋይዳ ምንድ ነው?

8. በዛሬው የጥናት ክፍለ ጊዜ በሕይወታችሁ አንድ ነገር በመወሰን እርምጃ ለመውሰድ የምትፈልጉት ነገር በመግለጽ ተወያዩ?

***መደምደሚያ***

በመጽሐፍ ቅዱስ የዘመንና የነገሮች ጅማሬ እንዳለው ሁሉ የዘመንና የነገሮች ፍፃሜ እንዳለ መረዳት አስፈላጊ ነው። የተባረከው ተስፋ  የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መምጣት ነው። ጌታን አምነንና ተስፋ አድርገን የተከተልነው በዚህ ምድር ባለ ሳይሆን ለሚመጣው አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር መሆኑ ልባችንን ሊያበረታው ይገባል። የጌታ ዳግም መመለስ የዘወትር ናፍቆትና ጸሎት ሊሆንልን ይገባል።  የጌታን ዳግም ምጽአት ዘወትር በጽድቅና በትጋት በመዘጋጀት መጠበቅ ያስፈልጋል። እንዲሁም በዚህ ምድር እንደ እንግዳና ምጻተኛ በመሆን እንመላለስ እንዲሁም በሚገጥሙን ልዩ ልዩ ፈተናዎችና መልካም የሚመስሉ ዕድሎች ከጽድቅ መንገድ ሳያስወጡንና ዘላለሙን ሳያስረሱን  ይልቁንም ብድራታችንን ትኩር ብሎ በመመልከት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአቱን ለሌሎች ወንጌል በመስበክና ሌሎች እንዲሰብኩ ባለን አቅምና ችሎታ በመተባበር እንጠብቅ።

የአስተያየት መስጫ ገጽ/Evaluation-Feedback-በመሪዎ በኩል ያስተላልፉ

1. ______________________________

2. ______________________________

3. ______________________________

______________________________

4. ______________________________

5. ______________________________

6. ______________________________

______________________________

7. ______________________________

8. ______________________________

9. ______________________________

______________________________